ይህ ብያኔ በዚያን ጊዜ መላ አውሮፓን አስደንቆ ነበር። ከዚህም ሁኔታ በ1791 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) የወጣው አይሁድን ከሌላው ሕዝብ ጋር እኩል የሚያደርገው ህግ በወረቀት ላይ ብቻ የሠፈረ ሆኖ ቀረ። በድሬይፉዩስ ላይ በተበየነው ብያኔ ምክንያት መላ አውሮፓ እንደገና በአይሁዶች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዲኖራቸው አደረገ። ጥር 5 ቀን 1895 በፈረንሳይ ጦር አካዳሚ በተደረገው አሳዛኝ ሥነ ስርዓት ላይ ከድሬይፉዩስ ልብስ ላይ የመቶ አለቅነቱ ማዕረግ ተገፈፈ፣ ሰይፉ ለሁለት ተሰበረ። በዚህም አሳፋሪ ድርጊት ከጦሩ ተወገደ። እርሱ ከጦሩ በተወገደ ዕለት ከፈረንሳይ መኮንኖችና ተመልካቾች *«ሞት ለአይሁድ፣ ሞት ለከዳተኞች»* የሚል ጩኸት አስተጋባ ፡፡

በኦውስትሪያ ይኖር የነበረው ቴዎደር ሄርስል የተባለው አይሁዳዊ ጋዜጠኛ ስለዚህ ጩኸት መስክሯል። በቀንና በሌሊት እንቅልፍ እስከሚያጣ ድረስ በዚህ ነገር በጣም ተጨነቀ። «ሞት ለአይሁድ! ሞት ለከዳተኞች!» የሚለው ጩኸት ሕሊናውን ደግሞ ደጋግሞ የሚያስጨንቀው ሆነ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር ዕረፍት የነሳው ሆነ። ቴዎድር ኸርዝል ግንቦት 2 ቀን 1860 ዓ.ም. በቡዳፔስት የተወለደ አይሁዳዊ ነበር። በ1878 በቪያና የሕግ ትምህርት ማጥናት ጀመረ። በ1884 የዶክትሬቱን ዲግሪ ከተቀበለ በኋላ ደራሲና ጋዜጠኛ ሆነ። ትዳር የመሠረተና የሶስት ልጆች አባት ነበር። ከ1891-1895 በፐርሲ ላለው ለቪያናው ኒው ፍሪ ፕሬስ ተወካይ ሆነ። በድሬይፉስ ላይ በተፈረደው ፍርድ የዓይን ምስክርና ስለ እርሱ መልእክት (ሪፖርት) የሰጠ ነበር። ይህ ፍርድ ሕይወቱን ቀየረው። በኋላ «ይህ በድሬይፉስ ላይ የተፈረደው ፍርድ ወደ ጽዮናዊነት ቀየረኝ» ብሏል። ኸርዝል ምንም እንኳን አይሁዶች የእኩልነት መብት ቢኖራቸውም ባሉበት ቦታ የማይፈለጉና የተጠሉ እንደሆኑ ተገነዘበ። ይህ ሰው አንድ ዓላማ ነበረው ይኸውም ወደ አባቶቻቸው ምድር ወደ እስራኤል መመለስ የሚል ነበር። ወደ ቪያና በተመለሰ ጊዜ በአይሁድ እጅግ ተወዳጅ የሆነውን «የአይሁድ ግዛት» የሚለውን መጽሐፍ በጥር ወር በ1896 አሳተመ። ብዙዎች አስተያየታቸውን መቀየር ጀመሩ። ከኸርዝል ሌላ ሌሎች ግለሰቦች ጸሐፊዎች፣ ዶክተሮች የአይሁድ ሕዝብ ወደ ቅድስት ምድራቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማድረግ ጀመሩ።





## በእግዚአብሔር የሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት ጠቋሚዋ
## በድንገት ወደ ፊት ተራመደች
## 1897 የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ

*«እነሆ የእስራኤልን ልጆች ከሄዱባቸው ከአሕዛብ መካከል እወስዳለሁ፣ ከስፍራም ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ ወደ ገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ» (ሕዝ.37:21)።*

ቴዎደር ሄርስል የእርሱን ሀሳብ የሚደግፉ ብዙ ጓደኞችንና ደጋፊዎችን አፈራ። ከነሐሴ 29-31 ቀን በ1897 ለሚደረገው የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብስባ ጥሪ አደረገ። በዚህ ስብሰባ ላይ 199 የሚሆኑ ተመልከቾችና ሁኔታው ያጓጓቸው ሰዎች ተገኙ። ይህን ስብሰባ በትኩረት የተመለከቱት ብዙዎች ነበሩ። ቴዎደር ሄርስል የተከበረ ዝነኛ ሰው ሆነ። አጣዳፊ መልስ በሚያስፈልግ ሁኔታ በድሬይፉስ ላይ የተወሰደውን ፍርድና ፈረንሳዮች የመላ አይሁዶችን ጥፋት መመኘታቸውን ገለጹ። የአይሁድ ሕዝብ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የተቻላቸውን ነገር የማያደርጉ ከሆነ ይህ የመጨረሻ የዕድላቸው ጊዜ እንደሆነ ተነበየ። ቢሆንም ይህ ነገር ቀላል አልነበረም። የአይሁድ ሕዝብ በቀላሉ ወደ ቅድስት አገራቸው ለመመለስ የሚችሉ አልነበሩም። ምክንያቱም ከ1517 ጀምሮ ምድሪቷን ይገዙዓት የነበሩት ቱርኮች ያኔም እየገዟት ስለነበር ነው። ቱርክ በዓለም ኃያል መንግሥት ነበረች። የግዛቱ ስፋት ከዩጎዝላቪያ፣ በግሪክ በኩል በማለፍ እስከ ፐርሺያን ባሕረ ሰላጤ ድረስ ይደርስ ነበር። ሰሜን አፍሪካ፣ ግብፅና ሌሎች የአረብ አገሮች እንኳን የዚህ ታላቅ ግዛት ተገዢዎች ነበሩ። ቢሆንም አይሁድ በማንኛውም ሁኔታ መጡ። አይሁዶች ጥሪውን በግልፅ ሰሙት። በድብቅ ወደ ፓለስታይን በመግባት ባዶ የሆኑትን መሬቶች ከ500 የአረብ ቤተሰቦች ትንሽ በትንሽ መግዛት ጀመሩ። በዚያን ጊዜ ሀገሪቱ በሕዝብ የተሞላች አልነበረችም። ለመጀመሪያ ጊዜ ከ1000 እስከ 2000 አይሁዶች ነበሩ በየአመቱ ይገቡ የነበሩት። ነገር ግን ወዲያዉኑ በአስደናቂ ሁኔታ ቁጥራቸው እየጨመረ መሔድ ጀመረ።

ቴዎደር ሄርስል ያለ እረፍት አይሁዶች ወደ ጽዮን እንዲመለሱ በመምራት የተቻለውን ጥረት ሁሉ አደረገ። የአይሁድ ወደ ተስፋ ምድራቸው መመለስ «ብትፈልጉ ይህ ተረት አይደለም» በማለት ቴዎደር ሄርስል ጻፈ። በሕይወቱ ላለው ከፍተኛ ግብ ድጋፍ ለማግኘት በመላው ዓለም ዞረ። ዓላማውም ነፃ የሆነ የአይሁድን መንግሥት ማቋቋም ነበር። ሄርስል በፒትስበርግ ያለውን የሩሲያውን ቴሳር ተወካይ ጎብኝቷል።

በኢየሩሳሌም በጀርመናውያን በተሰራው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የምረቃ ስነ ስርዓት ላይ የመጣውን የጀርመኑን ንጉሥ ዳግማዊ ዊሊሁለም ጎበኝቷል:: የባዴኑን ልዑል፣ የኢጣሊያኑን ንጉሥና በሮም ይኖር የነበረውንም ጳጳስም ጎበኝቷል። ነገር ግን ሕዝቡን ሊመራ ያለበት የአስር ዓመት ዕድሜ ብቻ ቀርቶት ነበረው:: ዕረፍት ከማጣቱ ከትልቅ ድካም የተነሳ በተወለደ በ44 ዓመቱ በ1904 ዓ.ም. ሞተ:: ይረዳ የነበረው በእናቱ፣ በሚስቱ በጁሊያ፣ በሴት ልጆቹ በጳውሊንና ጌርትሩ እንደዚሁም በተወዳጅ ልጁ በህንስ ነበር። እርሱ ቢሞትም ታምራት መካሔድ ጀመረ:: የአይሁድ ሕዝብ ቀስበቀስ ወደ ቅድስት ምድራቸው መመለስ ቀጠሉ:: እግዚአብሔር ሕዝቡን ማሰባሰብ ጀመረ::

**በእግዚአብሔር የሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት**
**ጠቋሚዋ እንደ ገና ወደ ላይ መውጣት**
**በ1917 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) የባልፎሩ ውሳኔ**

*«ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:: ስለዚህ ደግሞ አደርግላቸው ዘንድ የእስራኤል ቤት ይሹኛል:: ቀን እንደሚሆኑ እንደ ኢየሩሳሌም በጎች እንዲሁ የፈረሱት ከተሞች በሰዎች መንጋ ይሞላሉ፣ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ» (ሕዝ. 36:37-38)*

ከ1914 - 1918 ዓ.ም. የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ሆነ በአውሮፓ ለብዙ ምዕተ ዓመታት ገንነው የነበሩት መንግሥታትና ግዛቶች ወደቁ:: በድንገት የቄሳሮችና የልዑሉች አገዛዝ አበቃለት:: በዚህ ጦርነት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ (1916/17) የእስራኤልን ሕዝብ የሚመለከት ውሳኔ ተወሰነ:: ቻይም ዊዝማን የሚባል ኬሚስት በኢንግላንድ ይኖር ነበር:: በሩሲያ የተወለደና አስራ አራት ወንድሞችና እህቶች ነበሩት:: በትውልዱ (በደም) አይሁዳዊ ነበር:: የታናሽ ወንድሙ ልጅ ኤዛር ዊዝማን የሚባለው በእስራኤል አየር ኃይል ውስጥ የተወደደ ጀኔራል፣ በኋላም የካቢኔ ሚኒስትርና፣ የእስራኤል መንግሥት ፕሬዝዳንት ነበር:: አይሁዶች በሩሲያ እንዲማሩ ያልተፈቀደ ከመሆኑ የተነሳና እንደዚሁም አይሁዶችን የማጥፋት ዕቅድ ስለነበረ ቻይም ዊዝማን ወደ ምዕራብ አውሮፓ በኦውስትሪያ በኩል በመሰደድ ወደ ኢንግላንድ መጣ። የእንግሊዝ መንግሥት በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በማንቸስተር ላለው የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች ለሚሠሩበት ኢንዱስትሪ የበላይ አስተዳዳሪ አድርጎ ሾመው:: የኬሚስትሪ ዶክተር እንደ መሆኑ አዲስና አስደናቂ ግኝት አገኘ::





ለኃይለኛ ፍንዳታ የሚውለውን አሲቶንን ከስንዴ ለመሥራት ቻለ:: በዚህ በተገኘው አዲስ ግኝት በመጠቀም እንግሊዝ ጀርመንን በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ድል ለማድረግ በቃች:: በ1916 ሁለቱም ክፍሎች ጦርነቱን ሊቀጥሉ አልቻሉም:: ወደ ፊት መግፋቱ ለጥቂት ጊዜ አቆሙ:: በዚህ ጦርነት ድንገተኛ ለውጥ መጣ:: ይኸውም በምዕራቦቹ ሕብረት የጀርመንን ጦር ድል የማድረጉ ነገር ነበር:: ጀርመን መቋቋም በማይችለው ሁኔታ የአሜሪካ መንግሥት ታንኮችን በማሰለፍ መዋጋት ጀመረች:: ቻይም ዊዝማን በማንቸስተር ከሎርድ ባልፎር ጋር እንዲተዋወቅ ተደረገ:: በሁለቱ መካከል የጠበቀ ጓደኝነት ተመሠረተ:: ባገኘውም ግኝት ምክንያት የታወቀ ሆነ:: የእንግሊዝ መንግሥት ባደረገው ታላቅ አገልግሎት ዶክተር ቻይም ዊዝማንን የከበረ ሰው አደረገው:: ከፓርላማ አባሎች ዘንድ በማቅረብ እንዲታወቅ ተደረገ:: በፓርላማውም ምን እንደሚፈልግ ተጠየቀ:: አይሁድ እንደመሆኑ መጠን ቻይም ዊዝማን የነበረው ምርጫና ጥያቄ አንድ ነበር:: የእንግሊዝን መንግሥትም የአይሁድ ሕዝብ ወደ ፓለስታይን ወደ ምድራቸው የሚመለሱበትን መንገድ እንዲያመቻቹለት ነበር የጠየቀው:: የእንግሊዝ መንግሥት በዚህ ተስማማ:: ፓለስታይን በምስራቅ እስያና በሕንድ ላለው ለእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ መሸጋገሪያ ድልድይ እንደምትሆን ታሰበ:: እንግሊዞች ፓለስታይንን በጥንቃቄ የተጠናከረ የአውሮፓ ሠራተኞች ቅኝ ግዛት ለማድረግ አሰቡ:: የእንግሊዙ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ጀምስ አርዘር ባልፎር የተባለው በታሪክ «የባልፎር መግለጫ» ተብሎ የታቀውን ጥቅምት 2 ቀን 1917 ዓ.ም. ታትሞ እንዲወጣ አደረገ:: ይህ አዋጅ ለእስራኤል ሕዝብ ወደ ገዛ ምድራቸው እንዲመለሱ ተስፋ ሰጠ::

ሕብረ ብሔሩ በጦርነቱ ጥሩ ውጤት ያስገኘ ሆነ:: ጀርመን ከቱርክ ጋር በመስማማት በቱርኩ ኦቶማን ኢምፓየር መንግሥት ምድር ላይ 25,000 የጀርመን ወታደሮች አሰፈረች:: ነገር ግን ቱርኮች በማንኛውም እቅጣጫ ድል ተመቱ፤ እንግሊዝ በዚያን ጊዜ በዓለም ኃያል መንግሥት ነበረች:: በአለንባዩ ጀኔራል ኢድሙንድ መሪነት በ1917/18 እንግሊዝ ቱርክን ድል በማድረግ ፓለስታይንን ያዘች:: በዚህም ለ400 ዓመታት ገንኖ የነበረው የቱርክ መንግሥት ወደቀ:: ቅድስቲቷን ምድር ለመያዝ በተደረገው ጦርነት 40,000 የእንግሊዝ ወታደሮች ሕይወታቸውን አጡ:: ጀኔራል አልንባይ በእግሩ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ገባ:: ጥቅምት 11 ቀን 1917 ዓ.ም. በዳዊት ምሽግ ደረጃዎች ላይ ሆኖ የቱርክ መንግሥት አገዛዝ ማክተሙን ተናገረ በኋላም በዚሁ ቦታ የባልፎሩ ውሳኔ ተነገረ::

በዚያን ቀን ሊነገር በማይቻል ሁኔት የአይሁድ ሕዝቦች ተደሰቱ ወደ ነጻነት የሚወስደው መንገድ የተቃረበ ሆነ። የምዕራቡ ዓለም ኃይል ለአይሁድ መንግሥት መቋቋሙን የሚደግፍ ሆነ። ሊግ ኦፍ ኔሽን የበላይ ሞግዚትነቱን ለእንግሊዝ ሰጠ። የመጀመሪያው የእንግሊዝ ከፍተኛው ኮሚሽነር በትውልዱ አይሁዳዊ ነበር። ስሙም ሰር ኸርበርት ሳሙኤል ይባል ነበር። እርሱ ደግሞ መላ አይሁድ ወደ ፓለስታይን እንዲመለሱ ጥሪ አደረገ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ አይሁዶች ወደ ቅድስቲቱ ምድር መመለስ ችለዋል። የአይሁድ ሰፋሪዎች የተጣለውን ምድር በመሥራታቸው የአረብ ሰደተኞች ከዚህ ከተሠራው ግንባታ ጥቅም ፈላጊዎች ሆኑ። ይህም ደም ወደ መፋሰስ ጠብ መራ። እነዚህ ፍልሚያዎች በቀጠሉ መጠን እንግሊዞች ደግሞ አረብ ጎን በመሆን የአይሁድን የመመለስን እንቅስቃሴን የሚያውኩ ሆኑ። ከምስራቅ በዩርዳኖስ በኩል የሚመጡት አረቦች ወደ ሀገሪቱ እንዲገቡ ተፈቀደላቸው።

**Tha "Balfour Declaration"**

**Foreign office,**
November 2nd,1917

Dear Lord Rothschild,

I have much pleasure in conveying to you, on behalf of his majesty's government, the following declaration of sympathy with jewish Zionist aspirations which has been submitted to, and approved by, the cabinet "His majesty's government view with favout the establishment in Palestine of a national home for the jewish people, and will use their best endeavourer to facilitate the achievement of this object, it being clearly understood that nothinmg shall be done which may prejudice the civil and religious rights of existing non- jewish communities in Palestine , or the rights and political status enjoyed by jews in any other country"
I should be greateful if you would bring this declaration to the knowledge og the Zionist federation.

በአንደኛው የዓለም ጦርነት እንግሊዝ ከቱርክ ጋር ባደረገችው ጦርነት አረብ ስለ ሰጠችው ድጋፍ እንግሊዝ ለመካው ሸሪፍ ሁሴን የአረብ ግዛት ለመስጠት ተስፋ ሰጥታው ነበር። በእንግሊዝና በአረብ መካከል የነበረው መካከለኛ ሰው (አገናኙ) በአረቢያ





ታዋቂ የሆነው ሰው ቶማስ ኤድዋርድ ላውሬንስ የተባለው ሰው ነበር። የአረብ መንግሥታት ነጻ የወጡት ከአንደኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ነበር። የሸሪፎቹ ወንዶች ልጆች በእነዚህ የአረብ መንግሥታት ላይ የበላይ ገዢነት ተሰጣቸው። በአይሁዶችና በአረቦች መካከል እንግሊዝ በምታካሄደው ፓለቲካ ምክንያት አይሁዶች በጣም ወደ ኋላ የተተው ሆኑ። በባልፎሩ ውሳኔ እንግሊዝ ለአይሁዶች ልትሰጣቸው የገባችውን የራሳቸውን ምድር በ1922 ዊንስተር ቸርችል ሰሁለት ከፈሉት። ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ በኩል ካለው ከሃገራቸው 76ኀቱ ለመካው ሸሪፍ ልጅ ለአሚር አብዱላሂ እንዲሰጥ ተደረገ። ይህ ሰው ግንቦት 25,1946 ዓ.ም የዮርዳኖስ ሀሽማይት መንግሥት መቋቋሙን አወጀ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነው ምድራቸው ቀሪው 24ኀ በእንግሊዞች ዌስት ባንክ ተብሎ የተጠራው ከዮርዳናስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በኩል ያለው ለጽዮናውያን እንቅስቃሴ መሪዎች ተሰጠ። ይህ 24ኀ ምድር እንደገና በተባበሩት መንግሥታት በሕዳር 29,1947 ዓ.ም. የተከፈለ ሆነ ይህም የመከፈል እቅድ ተብሎ ተጠራ። በዚህች ትንሽ በሆነች ምድር ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. ዳቪድ ቤን ጉርዮን የእስራኤልን መንግሥት አወጀ።

***የባልፎሩ ውሳኔ***

የውጭ ጉዳይ ቢሮ

ሕዳር 2 . 1917 ዓ.ም

የተከበሩ ሮትዝሺልድ!

በተከበረው ልዑል መንግሥት ስም ሆኜ ከአይሁድ ጽዮናውያን ብርቱ መሻት ጋር በመተባበር ለእርስዎ ካቢኔ የተሰጠውንና ተቀባይነት ያገኘውን የርኅራኄ አዋጅ ለእርስዎ በመግለጼ እጅግ በጣም ደስታ ይሰማኛል።

የተከበረ መንግሥቱም በመልካም ጎኑ የሚያየው ነገር ቢኖር

በፓለስታይን (በእስራኤል ምድር) የአይሁድ ብሔራዊ ቤት

መቋቋም ሲሆን የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ በማድረግ በተቀላጠፈ

ሁኔታ ይህ ዓላማ ግብ እንዲመታ ነው። እዚህ ላይ በግልጽ

ሊታወቅ የሚገባው በፓለስታይን (በእስራኤል) በሚኖሩ

አይሁድ ባልሆኑት ማኅበረ ሰብ በሲቪልና በሃይማኖት መብታቸው

ላይ እንዳችም ነገር የማይፈጸምባቸው መሆኑ ነው።

ይህም በየትኛውም አገር እንዳሉት በመብታቸውና በፖለቲካ ደረጃቸው እንደሚደሰቱት አይሁድ ማለት ነው። ይህን አዋጅ ጽዮናዊው (የእስራኤል) ፌዴሬሽን እንዲያውቁት ካደረጉልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

### በእግዚአብሔር የሰዓት ቆጠራ ላይ ያለችው ሰዓት ጠቋሚዋ እንደገና ወደ ፊት ተራመደች

### 1948 የእስራኤል መንግሥት ምስረታ

*«ለአባቶቻችሁም በሰጠኋት ምድር ትኖራላችሁ» (ሕዝ.36:28)*::

በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል እንግሊዝ ፖለቲካዎቿን በፈጣን መንገድ ለወጠች:: በአዶልፍ ሂትለር መንግሥት ጊዜ አይሁዶች አስቃቂ ስደት ውስጥ ቢወድቁም:: በፓለስታይን የነበረው የእንግሊዝ አስተዳደር ጥቂት የአይሁድ ስደተኞች ብቻ እንዲገቡ ፈቀደ:: ከ6 ሚሊዮን በላይ የሆኑ አይሁዶች አስቃቂ በሆነ (ጭከና በተሞላ) አገዳደል በአውሮፓ ተገደሉ:: ሂትለር ይህን ሕዝብ ጨርሶ ለመደምሰስ ፈለገ:: የእንግሊዝ ፖለቲከኞች ከጊዜ ወደጊዜ በአይሁድ ሕዝብ ላይ በተቃውሞ የሚነሱ ሆኑ:: ይህም ሆኖ ሳለ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካበቃ ከሦስት ዓመት በኋላ እጅግ አስደናቂ ሁኔታ ተፈጠረ:: ይኸውም ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. ከ4:00-4:32 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ከተማ ሙዝየም በተገኙት 200 እድምተኞች ፊት የእስራኤል መንግሥት ታወጀ:: ከሰዓት በኋላ በ4 ሰዓት (በ10 ሰዓት) በ1906 የተወለደውና ከፖላንድ ተሰድዶ የመጣው ዳቪድ ቤን ጉርዮን የነጻነቱን አዋጅ በአይሁድ ቋንቋ «አትማውዝ» የተባለውን አነበበው:: በ4:17 (10:17) 37ቱ የአይሁድ መንግሥት ከፍተኛ ባለ ስልጣኞች ይህን አዋጅ ፈረሙ:: በ4:30 (10:30) የተከበሩት እድምተኞች ተነስተው «ሀቲክቫ» (ተስፋው) የተባለውን ብሔራዊ መዝሙር ዘመሩ:: መዝሙሩም የሚከተለው ነው::

*በአይሁድ ነፍስ ውስጥ ስሜት እስካለ ድረስ*
*ጽዮንን የመመኘት ፍላጎት ይኖራል*
*በምድራችን በጽዮን በኢየሩሳሌም እንደገና በነጻነት*
*ለመኖር የነበረው ለሁለት ሺህ ዓመታት የቆየው*
*ተስፋችን አልጠፋም::*

በዚህ ጊዜ ከ600,000 የሚበልጡ አይሁዶች በቅድስቲቷ ምድር ነበሩ:: ይህ ቁጥር በሙሴ ጊዜ ከግብፅ ምድር የወጡትን የወንዶች ቁጥር የሚያህል ነበር:: በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ፣ ሬዲዮ ያዳምጡ የነበሩ ሕዝቦች ይህንን ታሪካዊ ሁኔታ አዳምጠውት ነበር:: እንደገና ከ2,000 ዓመታት በኋላ አይሁዶች የራሳቸው ምድር እንዳላቸው አዲስ ተስፋ ያገኙ ሆኑ:: የአይሁድ ሕዝብ ሊነገር በማይቻል ደስታ





ተሞሉ:: ሰዎች በደስታ ተሞልተው በየመንገዱ መጨፈር ጀመሩ:: ከቴዎድር ኸርዝል ጊዜ ጀምሮ ተረት መስሎ የታየው ነገር እውን ሆኖ ተገለጠ::

ስለ አይሁድ መንግሥት ምስረታ የሚናገረውን ጽሁፍ ለማንበብ የፈጀው ጊዜ 17 ደቂቃ ብቻ ነበር:: መስራች አባሎች ስማቸውን በፊርማ ለማስፈርና ከተከበሩት እድምተኞች ጋር ብሔራዊ መዝሙራቸውን ለመዘመር የፈጀባቸው ጊዜ 15 ደቂቃ ብቻ ነበር:: በ4:32 (10:32) ይህ ትልቁ ስነ-ሥርዓት አበቃ ከውስጥ የጦር ዩኒፎርሙን ለብሶ የነበረው ዳቪድ ቤን ጉርዮን ጥቁር ካፖርቱን በማውለቅ:

«ስነ ሥርዓቱ አበቃ፣ ጦርነቱ ይጀምራል» አለ::

### የነጻነቱ ጦርነት 1948 - 1949

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ አዲስ የተቋቋመችው የእስራኤል መንግሥት በአረቦች ተወጋች:: ጨቅላ የሆነችውን የእስራኤልን መንግሥትና ሕዝብ ተባብረው በአንድ ምሽት ለማጥፋት በማሰብ አምስት የአረብ መንግሥታት የነበራቸውን ብርቱ ጦር በማሰለፍ በእኩለ ሌሊት በእስራኤል ላይ ጦርነት ከፈቱ:: ዮርዳኖስ ከደብረ ዘይት ተራራ ተኩስ በመክፈት ለ26 ቀናት ሌሊትና ቀን ያለማቋረጥ ኢየሩሳሌምን ደበደቡ:: ግብፅ ከደቡብ ኢራቅ፣ ከምስራቅ ሶሪያና ሊባኖስ ከሰሜን እስራኤልን በጦር ከበቧት ነገር ግን ይህ ጦርነት ለብዙ ጊዜ አልቀጠለም:: ከአረብ ጋር ሊመጣጠን በማይችል ትንሽ ትጥቅ የታጠቀችው እስራኤል ከአስር ወራት በኋላ ድሉን ተቀዳጀች:: በተባበሩት መንግሥታት ጠያቂነት ጦርነቱ እንዲቆም ተደረገ:: በኋላም በሩዶስ ደሴት ውሉ ተፈረመ:: የዓይን ምስክሮች «እግዚአብሔር ባለፈው ጊዜ እንዳደረገው ለእስራኤል ሕዝብ ተዋጋላቸው» በማለት ተናግረዋል (*ኢያሱ.10:12-14*):: ቢሆንም እስራኤል ለዚህ ጦርነት ከፍተኛ ዋጋ ከፍላለች ስድስት ሺህ ወታደሮች ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ ከ9,000 በላይ ቆስለዋል::

እስራኤል በዚህ የነጻነት ጦርነት ድል በመቀዳጀት ብዙ መሬት ያዘች:: በዚህ የብዙ ሕይወት እልፊት በተደረገው ጦርነት ኢየሩሳሌምን ለመያዝ አልቻለችም:: በዮርዳኖሳውያን እጅ ወደቀች:: ኢየሩሳሌም ለቀጣዩ 19 ዓመታት እንደ ተከፋፈለች ቆየች:: እስራኤላውያን በልቅሶ አደባባይ ለመጸለይ አልቻሉም::

## የ1956ቱ የስዊዝ ቀውስ

እንደ ቀድሞው ሰላም አልነበረም፡፡ የተኩስ አቁሙ የቆየው ለሰባት ዓመታት ብቻ ነበር፡፡ «የስዊዙ ቀውስ» ተብሎ የተጠራው በጥቅምት ወር 1956 የተጀመረው አንባ ገነኑ የግብፁ መሪ ናስር በ1869 በፈረንሳዮች የተሠራውን የስዊዝ ካናልን በግብፅ እጅ እንዲሆን ባደረጉበት ጊዜ ነበረ፡፡ የፈረንሳዩ፣ የእንግሊዙና የእስራዔሉ የታንክ ብርጌድ ግብፅን በመውጋት ጉዞአቸውን ወደ ስዊዝ ካናል አመሩ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የሲና ባሕረ ሰላጤ በእስራኤል ተወሰደ፡፡ ወዲያውኑ የአረብ መንግሥታት ይህንን የፖለቲካ ጉዳይ በማድረግና የእስራኤልን ድል ማድረግ በመቃወም የተባበሩት መንግሥታት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲያደርግ ጥሪ አደረጉ፡፡ የዚህም ውጤት እስራኤል ከሲና ወጥታ እንድትሔድ ሆነ፡፡ እስራኤል የ170 ሰዎች ሕይወት እጣች 700 ቆስሉባት፡፡

**በእግዚአብሔር ሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት**

**ጠቋሚ እንደ ገና ወደ ላይ ወጣች**

**የ1967ቱ የስድስቱ ቀናት ጦርነት**

***«እስራኤል በኃይል ያደርጋል» (ዘኁ.24:18)***

አምባ ገነኑ የግብፅ ገዢ ናስር ከስዊዙ ቀውስ ከሰባት ዓመት በኋላ በእስራኤል ላይ ሌላ ጦርነት ከፈቱ፡፡ ይህ ጦርነት በታሪክ «የስድስቱ ቀን ጦርነት» ተብሎ የተጠራው ነው፡፡ የአረብ መንግሥታት የ1948 ዓ.ም. ድል ሲቋቋሙትና ሲረሱት አልቻሉም ነበር፡፡ ስለዚህም በሩሲያ ደጋፊነት የጦር ኃይላቸውን አጠናከሩ፡፡ ግብፅ፣ ሶርያ፣ ኢራቅና ዮርዳኖስ እስራኤልን ድል ለማድረግ የሚችሉ አድርገው ራሳቸውን ገመቱ፡፡ በግንቦት መጨረሻ በ1967 ዓ.ም. እነዚህ አገሮች ሙሉ የጦር ኃይላቸውን አንቀሳቀሱ፡፡ ከእስራኤል ጎን ያሰው አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ የፖለቲካ ጥረት ውጤተ ቢስ ሆነ፡፡ የአሜሪካ፣ የፈረንሳይና የጀርመን ሕዝቦች እስራኤልን በመደገፍ በየመንገዱ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ፡፡ የስድስቱ ቀን ጦርነት ሰኔ 5 ቀን 1967 በ7:55 ሰዓት (1:55 ምሽት ላይ) ተጀምሮ በጎላን ኮረብታ ላይ በኩኒትራ የሚገኘው የሶርያ ከፍለ ጦር በመሸነፍ ሰኔ 10 ቀን 1967 ዓ.ም በ2:30 ሰዓት (8:30) ላይ አበቃ፡፡ በዚህ ጦርነት እስራኤል የሲናን ባሕረ ሰላጤ፣ ይሁዳን፣ ሰማርያን ጋዛንና የጎላንን ተራራ እንደገና ለመያዝ ቻለች፡፡ ሰኔ 7 ቀን 1967 ዓ.ም. የሚቀጥለው እርምጃ ወደ ኢየሩሳሌም ማምራት ሆነ፡፡ በ55 ሰዓት ውስጥ የእስራኤል ፓራትሩፐና የታንኩ ብርጌድ የጥንቷን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነችውን





ከተማ ኢየሩሳሌምን ያዙ፡፡ የአረቦችን መስኪዶችና የከርስቲያኖችን ቤተ ክርስቲያንን ለማዳን ሲሉ እስራኤላውያን ከባድ መሳሪያ አልተጠቀሙም ነበር፡፡ በዚህ ጦርነት ጠባብ በሆኑት በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ምርጥ ከሆኑት ወታደሮቹ 183 ወጣቶቿን አጣች፡፡ ቢሆንም እስራኤል ግቧ ላይ ደረሰች፡፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ መላ የኢየሩሳሌም ከተማ፣ የቤተ መቅደሱ ተራራና የልቅሶ አደባባይ ጭምር ለእስራኤል መንግሥት ሆነ፡፡ በዚህ ታምራዊ በሆነው ሁኔታ ጊዜ ታላቁ ራቢ (መምህር) ሻሎም ጎሬን ቀንደ መለከትን በመንፋት «እኛ ወደ መሲሁ ዘመን ገብተናል» ብለው ትንቢታዊ ቃል ተናገሩ፡፡ የዕብራውያን ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ጆሹዋ (ኢያሱ) ፕራውር በመጨመር «የመሲሁን መምጣት መቅረብ በሰሚ ጆሮዎች ለመስማት ይህ ሕዝብ ለ2000 ዓመታት ያህል ነጻነቱን መጠበቅ ነበረበት» በማለት ተናግረዋል፡፡

እስራኤል 800 ወታደሮች ሞተውና 2600 ሲቆስሉባትም እግዚአብሔር እንደገና ለዚህ ሕዝብ ድልን ሰጠ፡፡ እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ እንደ ኪዳኑ እስከ ቤርሳቤህ፣ ከሜድትራንያን ባሕር እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ያለውን መላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምድራቸውንና ኢየሩሳሌምን ጭምር ሰጣቸው፡፡

## የ1973ቱ ዓ.ም የዮም ኪፑሩ ጦርነት

ጥቅምት 6 ቀን 1973 ዓ.ም ዮም ኪፑር በተባለው የአይሁዶች የስርየት በዓል ዕለት የአረቦች ጦርነት በእስራኤል ላይ እንደገና እንደ አዲስ ተጀመረ፡፡ ዮምኪፑር ተብሎ በተጠራው ጦርነት ጊዜ ግብፅ ከደቡብ በሲና ካናል በኩል፣ ሶሪያ በጎላን ኮረብታ በኩል ከሰሜን በእስራኤል ላይ ጦርነት ከፈቱ፡፡ ይህም ቢሆን እስራኤል በጥሩ ውጤት ተቋቋመቻቸው፡፡ ከሦስት ሳምንታት በኋላ የእስራኤል ወታደሮች ከካይሮ 100 ኪሎ ሜትር ከደማስቆ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነበሩ፡፡ እስራኤል 2650 ወታደሮች ሲያልቁባት 7500 ደግሞ ቆስለውባታል፡፡ ነገር ግን እንደገና ለዚህ ድል ፍሬ እንድትቋረጥ ተደረገ፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ጣልቃ በመግባት ይህን የእስራኤልን የድል ጉዞ እንዲቆም አደረገው፡፡ ድንገት ሳይታሰብ ሕዳር 19 ቀን 1977 ዓ.ም የግብፁ ፕሬዝዳንት ሳዳት ሲና ባሕረ ሰላጤ የሚመለስበትን መንገድ ከእስራኤል ጋር ለመስማማት ወደ ኢየሩስሌም መጡ፡፡ በተባበሩት መንግሥት ጣልቃ ገብነት ሁለቱ ሀገሮች «ካምፕ ዴቪድ አኮርድ» የተባለውን ውል መጋቢት 26 ቀን 1979ዓ.ም ተፈራረሙ፡ሚያዝያ25ቀን1982 ዓ.ም. እስራኤል ሙሉ በሙሉ ከሲና ወጣች፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእስራኤልና በግብፅ መካከል ሰላም ሰፈነ፡፡

## የ1982ቱ የሊባኖስ ጦር ዘመቻ

እስራኤል ሰኔ 6 ቀን 1982 ዓ.ም በፒ.ኤል.ኦ (PLO) የያሲር አረፋት ሽብርተኞች ላይ እርምጃ እንድትወስድ ተገደደች። ምክንያቱም አስደንጋጭ በሆነው ካቲዩሻ ሮኬት በመደገፍ በመደጋገም በገሊላ በስተ ሰሜን በሚገኙት ከተማዎችና መንደሮች ላይ ጥቃት ይፈጽሙ ነበር። እስራኤል እስከ ቤይሩት ድረስ ዘልቆ በመግባት 36,000 የአረፋት ሽብርተኞች ሊባኖስን ለቅቀው እንዲሸሹ አደረገች። ይህ ጦርነት አሳዛኝ (ልብ የሚሰብር) የሆነ ጥፋትን በእስራኤል ላይ አስከተለ። እንደገና እስራኤል በዚህ ጦርነት የ547 አባቶችንና የወንዶች ልጆቿን ሕይወት አጣች።

## እስራኤል ሕያው ተዓምር

እስራኤል መንግስቷን ከመሰረተችበት ከ1948 ዓ.ም ወዲህ በተደረጉት አምስት ጦርነቶች የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ድልን አቀዳጅቷል። በብዛትና በጥንካሬ ይበልጧት የነበሩት ጠላቶቿ የሆኑት አረቦች ይህችን አዲስ የተቋቋመችውን መንግሥት ሊቋቋሟት አልቻሉም። በተቀራኒው ግን እስራኤል ከቶ ባልታየ ሁኔታ ማደግ ጀመረች። በአስርት ዓመታት ውስጥ ለብዙ ዓመታት በረሀ ሆነው የቆዩት ቦታዎች በልምላሜ የተሞሉ ገነቶች ሆኑ። እስራኤል በየዓመቱ ብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ምግብ ወደ ውጭ የምትልክ ሀገር ሆነች። ከሙቶ ሰባው እጅ የአልማዝ ማዕድን የሚቀረፀው በእስራኤል ነው። የሙት ባህር አካባቢ በዓለም ከፍተኛው የብሮማይን፣ የፖታሽ፣ የማግኔዚየምና የሌሎች የኬሚካል ማዕድኖች ክምችት የሚገኝበት ቦታ ነው። ማንኛውም ነገር በአስገራሚ ሁኔታ ከትልቁ ኤሌክትሮኒክ እስከ አነስተኛው የመኪና ጎማ ድረስ በእስራኤል ምድር ይመረታል። ሀገሪቱ ለጦር የሚያስፈልጉት ከምችቶችና በሕዋ ውስጥ የራሷ ሳተላይትና አውቶማቲክ ቦምቦች አሏት። እስራኤል ከሌሎቹ ሀገሮች ጋር ስትወዳደር አነስተኛ ሆና ብትታይም በዓለም በጦር ኃይል አራተኛዋ ጠንካራ መንግሥት እንደሆነች ይገመታል።


ከ2000 የስቃይና የስደት ዓመታት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ መሰባሰብ በአሁን ጊዜ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ተአምር ነው።

- በቱርኮች ተደምስሳ በነበረችው ምድር የመጀመሪያዎቹ የእስራኤል ሰፋሪዎች በ1870 ዓ.ም ወደ ፓለስታይን ተመልሰው ምድሪቱን መርገጣቸው *ተአምር* ነበር።





- እስከ 1948 ዓ.ም ድረስ በፓለስታይን የነበሩት አይሁዶች 600,000 ነበሩ። ይህም *ተአምር* ነበር። በሙሉ ጊዜ ከግብፅ ከወጡት የጦር መሣሪያ መታጠቅ ከሚችሉት ጋር በቁጥር ተመጣጣኝ ነበሩ።
- አሰቃቂ የሆነውን የሂትለርን አገዛዝ ተቋቁመው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ከሦስት ዓመት በኋላ ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም የእስራኤል መንግሥት መመስረቱ *ተአምር ነበር።*
- ለእስራኤል መንግሥት ምስረታ ሁኔታን በማመቻቸት የተባበሩት መንግሥታት በ1947 እስራኤልን ለመከፈል ያደረገው ስምምነት ተአምር ነበር።
- የእስራኤል መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ ከእርሷ በኃይል በሚበልጡት ጠላቶቿ በአምስቱም ጦርነቶች አሰመሸነፏ ተአምር ነበር።
- በ1991 ዓ.ም. በባህረገልፉ ሰላጤው ጦርነት ከእስራኤል 74 ሰዎች መሞታቸው ተአምር ነበር። ምክንያቱም 39 የኢራቅ ስከድ ሚሳኤሎች ከተማዋን መትተዋል። ሁለት ሚሳይኤሎች ቴልአቪቭን በመምታት 7000 ቤቶችን፣ አፓርታማዎችን ደምስሰዋል።




በቅድስቲቱ ምድር ተአምር በተአምር ላይ ታይተዋል። ይህንን ዘገባ እስከቻልንበትና እስከወደድንበት ድረስ ልንመዘግብ እንችላለን። እግዚአብሔር ከዚህ ሕዝብ ጋር እንደ ገና መሥራቱ አስደናቂ ነገር ነው። ማንኛውም የዓለም ኃይል እስራኤልን ሊያጠፋ አልቻለም፣ አይችልም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ግንብና የእሳት ቅጥር ስለሆነ ነው (*ዘካ.2:5*)፣ «እርሱ ራሱ ሰቤቱ ይቆማል» (ዘካ. 9:8)።

1897፣ 1917፣ 1948 እና 1967 ዓ.ም በእስራኤል የደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራን የያዙ ዓመታት ናቸው። እነዚህ ዓመታት ዝግ ያለውንና የማይነቃነቀውን የእስራኤልን መንግሥት ትንሳኤን ያሳያሉ።

### የ1982ቱ የሊባኖስ ጦር ዘመቻ

እስራኤል ሰኔ 6 ቀን 1982 ዓ.ም በፒ.ኤል.ኦ (PLO) የያሲር አረፋት ሽብርተኞች ላይ እርምጃ እንድትወስድ ተገደደች። ምክንያቱም አስደንጋጭ በሆነው ካቲዩሻ ሮኬት በመደገፍ በመደጋገም በገሊላ በስተ ሰሜን በሚገኙት ከተማዎችና መንደሮች ላይ ጥቃት ይፈጽሙ ነበር። እስራኤል እስከ ቤይሩት ድረስ ዘልቆ በመግባት 36,000 የአረፋት ሽብርተኞች ሊባኖስን ለቅቀው እንዲሸሹ አደረገች። ይህ ጦርነት አሳዛኝ (ልብ የሚሰብር) የሆነ ጥፋትን በእስራኤል ላይ አስከተለ። እንደገና እስራኤል በዚህ ጦርነት የ547 አባቶችንና የወንዶች ልጆቿን ሕይወት አጣች።

### እስራኤል ሕያው ተዓምር

እስራኤል መንግስቷን ከመሰረተችበት ከ1948 ዓ.ም ወዲህ በተደረጉት አምስት ጦርነቶች የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ድልን አቀዳጅቷል። በብዛትና በጥንካሬ ይበልጧት የነበሩት ጠላቶቿ የሆኑት አረቦች ይህችን አዲስ የተቋቋመችውን መንግሥት ሊቋቋሟት አልቻሉም። በተቃራኒው ግን እስራኤል ከቶ ባልታየ ሁኔታ ማደግ ጀመረች። በአስርት ዓመታት ውስጥ ለብዙ ዓመታት በረሀ ሆነው የቆዩት ቦታዎች በልምላሜ የተሞሉ ገነቶች ሆኑ። እስራኤል በየዓመቱ ብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ምግብ ወደ ውጭ የምትልክ ሀገር ሆነች። ከመቶ ሰባው እጅ የአልማዝ ማዕድን የሚቀረፀው በእስራኤል ነው። የሙት ባህር አካባቢ በዓለም ከፍተኛው የብሮማይን፣ የፖታሽ፣ የማግኔዚየምና የሌሎች የኬሚካል ማዕድኖች ክምችት የሚገኝበት ቦታ ነው። ማንኛውም ነገር በአስገራሚ ሁኔታ ከትልቁ ኤሌክትሮኒክ እስከ አነስተኛው የመኪና ጎማ ድረስ በእስራኤል ምድር ይመረታል። ሀገሪቱ ለጦር የሚያስፈልጉት ክምችቶችና በሕዋ ውስጥ የራሷ ሳተላይትና አውቶሚክ ቦምቦች አሏት። እስራኤል ከሌሎቹ ሀገሮች ጋር ስትወዳደር አነስተኛ ሆና ብትታይም በዓለም በጦር ኃይል አራተኛዋ ጠንካራ መንግሥት እንደሆነች ይገመታል።

ከ2000 የስቃይና የስደት ዓመታት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ መሰባሰብ በአሁን ጊዜ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ተአምር ነው።

- በቱርኮች ተደምስሳ በነበረችው ምድር የመጀመሪያዎቹ የእስራኤል ሰፋሪዎች በ1870 ዓ.ም ወደ ፓለስታይን ተመልሰው ምድሪቱን መርገጣቸው ተአምር ነበር።





- እስከ 1948 ዓ.ም ድረስ በፓለስታይን የነበሩት አይሁዶች 600,000 ነበሩ። ይህም ተአምር ነበር። በሙሴ ጊዜ ከግብፅ ከወጡት የጦር መሣሪያ መታጠቅ ከሚችሉት ጋር በቁጥር ተመጣጣኝ ነበሩ።
- አስቃቂ የሆነውን የሂትለርን አገዛዝ ተቋቁመው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ከሦስት ዓመት በኋላ ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም የእስራኤል መንግሥት መመስረቱ ተአምር ነበር።
- ለእስራኤል መንግሥት ምስረታ ሁኔታን በማመቻቸት የተባበሩት መንግሥታት በ1947 እስራኤልን ለመከፋፈል ያደረገው ስምምነት ተአምር ነበር።
- የእስራኤል መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ ከእርሷ በኃይል በሚበልጡት ጠላቶቿ በአምስቱም ጦርነቶች አለመሸነፏ ተአምር ነበር።
- በ1991 ዓ.ም. በባህረገልፉ ሰላጤው ጦርነት ከእስራኤል 74 ሰዎች መሞታቸው ተአምር ነበር። ምክንያቱም 39 የኢራቅ ስከድ ሚሳኤሎች ከተማዋን መትተዋል። ሁለት ሚሳይሌሎች ቴልአቪብን በመምታት 7000 ቤቶችንና አፓርታማዎችን ደምስሰዋል።

**የ100 ዓመት የእስራኤል ስደት**

**33 ዓ.ም - የኢየሱስ መስቀል**

**70 ዓ.ም - የቤተ መቅደሱ መደምሰስ**

**135 ዓ.ም - የባር ኮቺባ አመጽ**

በቅድስቲቱ ምድር ተአምር በተአምር ላይ ታይተዋል። ይህንን ዘገባ እስከቻልንበትና እስከወደድንበት ድረስ ልንመዘግብ እንችላለን። እግዚአብሔር ከዚህ ሕዝብ ጋር እንደ ገና መሥራቱ አስደናቂ ነገር ነው። ማንኛውም የዓለም ኃይል እስራኤልን ሊያጠፋ አልቻለም፣ አይችልም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ግንብና የእሳት ቅጥር ስለሆነ ነው (ዘካ.2:5)፣ «እርሱ ራሱ ሰቤቱ ይቆማል» (ዘካ. 9:8)።

**1897፣ 1917፣ 1948** እና **1967** ዓ.ም በእስራኤል የደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራን የያዙ ዓመታት ናቸው። እነዚህ ዓመታት ገሃ ያለውንና የማይነቃነቀውን የእስራኤልን መንግሥት ትንሳኤ ያሳያሉ።

*የእግዚአብሔር ጥሪ ለመቶ ዓመታት የእስራኤልን ልጆች ወደ ቅድስት ምድር የሚሰባቸው ሆነ፡፡*

- ከ1870 ዓ.ም የመጀመሪያ የእስራኤል ሰፋሪዎች ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1976 ዓ.ም መሳው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ምድራቸው በእስራኤል ግዛት ስር እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ መቶ ዓመታት አልፈዋል፡፡

*እንደገና ለመቶ ዓመታት ያህል የእስራኤል ታሪክ ወደ ፊት የቀጠለ ነበር፡፡*

*በአሁኑ ጊዜ በእስራኤል እንደዚህ ያለውን እድገት የምንገነዘበው ለምንድን ነው?*

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የእስራኤል ደህንነት ግልጽ ከሆነ ከመሰባሰባቸው «ከመመለሳቸውና እንደ ገና ከመመስረታቸው ሁኔታ» የሚጀምር ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል በመንፈስ ቅዱስ በሆነ የውስጥ መታደስ ይቀጥላል፡፡ አስቀድሞ እንዳየነው የእስራኤል መሰባሰብ ቀጠለ፡፡ ለዚህም አንድ መግለጫ አለ፡፡ ይኸውም ጌታ ሕዝቡን ወደ ቅድስት ምድር እየመለሰ ነው፡፡ የማዳን ዕቅድ ካርታ ይህን በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከስደት ዘመናቸው በኋላ ከተበታተኑበት ቦታ ወደ ቅድስት ምድር መመለሳቸውና የእስራኤል ሕዝብ መነሳት እንደገና ወደ መሲሁ (ክርስቶስ) ይመራናል፡፡ መሲሁ (ክርስቶስ) በሚመለስበት ጊዜ ሕዝቡ በእስራኤል ምድር ይሰባሰባሉ *(ሕዝ.37፡1-14)* ፣*(ሕዝ.39፡28)*፡፡

**የ100 ዓመታት የእስራኤል መመለስ**

**1897 ዓ.ም - የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ**

**1917 ዓ.ም - የባልፎሩ ውሳኔ**

**1948 ዓ.ም - የእስራኤል መንግሥት ምስረታ**

**1967 ዓ.ም - የስድስቱ ቀን ጦርነት**

*ፖርስትሮይካና ግላስኖስት ስለምን ታየ?*

ይህን የምስራቁ ብሎክ (የምስራቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕብረት) ተብሎ የሚጠራውን መሠረት በማድረግ ይህን ለመረዳት ቀላል ሊሆን ቻለ፡፡ በፖርስትሮይካና ግላስኖስት በተደረገው የተሃድሶ ትግል በ19 ኛው ምዕት ዓመት ጅማሬ ላይ በሶቪየት





መንግስት ላይ ውድቀትን አስከተለ፡፡ ይህም ተአምር 850,000 የሩሲያ አይሁዶች ወደ ቅድስት አገር ለመመለስ የሚያስችላቸውን የመጀመሪያውን ሁኔታ አመቻቸ፡፡

ዳግም ልደት ያገኙ (ክርስቲያን) የክርስቶስን መምጣት በየቀኑ የሚጠባበቀውን ያህል ማንኛውም እውነተኛ አይሁድ በእስራኤል የመሲሁን መምጣት በየቀኑ ይጠባበቃል፡፡ ባለፉት 40 ዓመታት እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ታሪካዊ ማዳን የመጨረሻው ቀናት ምልክትና «ጌታ ፈጥኖ ሊመጣ ነው» የሚለውን የእኩለ ሌሊቱን ጩኸት መቃረቡን ያለ አንዳች ስህተት የሚያመለክት ምልክት ነው *(ማቴ.25፡6)* ፡፡

**ጌታ ቶሎ ይመጣል!**

## 4. እስራኤል በመጨረሻዎቹ ቀናት

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ ከአለም ወደ አባቶቻቸው ምድር ቢመለሱም እስራኤል ባለማመኑ ያለችበት እውነት ወደ ጎን የሚባል አይደለም *(ሮሜ.11፡20-23፡፡)* ስለመሲሁ መምጣት የማይቋረጥ ጥበቃ ቢኖራቸውም እስከዚህ ቀን ድረስ ምንም ለውጥ አልሆነም፡፡ በአሁኑ ጊዜ አይሁዶች እውነተኛው አዳኝ የሆነውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አልተገነዘቡትም፡፡ ይህም ቢሆን ነገሮች እንደዚሁ የሚቀሩ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤል መሲሁን ባለመቀበሏ ምክንያት መውደቋን ወደ አሕዛብ ሁሉ መበታተኗንና የተቀደሰችው ምድር በአሕዛብ እንደምትደመሰስ ቢናገርም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ እንዳላቸውም ይናገራል፡፡ ከታች በማነጻጸር በተጻፈው «እስከ» የሚለው ይህን ያመለክታል፡፡ በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ «የእስራኤል ሕዝብ መበታተንን» ከሚያሳየው ቀይ መስመር ስር በመጨረሻው ቀናት በአስደናቂ ሁኔታ የእስራኤልን ሕዝብ መመለስ የሚያመለክቱ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ፡፡ በቅርቡ እግዚአብሔር ራሱ ወደ ሕዝቡ ይመጣል፣ ምክንያቱም «መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፣ ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል» ተብሎ ተጽፏልና *(ሮሜ.11፡26)*፡፡ በበለጠ ለመረዳት ከዚህ በመቀጠል ስለዚህ ከሚናገሩት ጥቅሶች ጥቂቶቹን በማነጻጸር እንመለከታለን፡፡


*የእግዚአብሔር ጥሪ ለመቶ ዓመታት የእስራኤልን ልጆች ወደ ቅድስት ምድር የሚሰባቸው ሆነ::*

- **ከ1870 ዓ.ም የመጀመሪያ የእስራኤል ሰፋሪዎች ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1976 ዓ.ም መላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ምድራቸው በእስራኤል ግዛት ስር እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ መቶ ዓመታት አልፈዋል::**

*እንደገና ለመቶ ዓመታት ያህል የእስራኤል ታሪክ ወደ ፊት የቀጠለ ነበር::*

*በአሁኑ ጊዜ በእስራኤል እንደዚህ ያለውን እድገት የምንገነዘበው ለምንድን ነው?*

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የእስራኤል ደህንነት ግልጽ ከሆነ ከመሰባሰባቸው «ከመመለሳቸውና እንደ ገና ከመመስረታቸው ሁኔታ» የሚጀምር ነው:: ከዚህ በመቀጠል በመንፈስ ቅዱስ በሆነ የውስጥ መታደስ ይቀጥላል:: አስቀድሞ እንዳየነው የእስራኤል መሰባሰብ ቀጠለ:: ለዚህም አንድ መግለጫ አለ:: ይኸውም ጌታ ሕዝቡን ወደ ቅድስት ምድር እየመለሰ ነው:: የማዳን ዕቅድ ካርታ ይህን በግልጽ ያመለክታል:: ከስደት ዘመናቸው በኋላ ከተበታተኑበት ቦታ ወደ ቅድስት ምድር መመለሳቸውና የእስራኤል ሕዝብ መነሳት እንደገና ወደ መሲሁ (ክርስቶስ) ይመራናል:: መሲሁ (ክርስቶስ) በሚመለስበት ጊዜ ሕዝቡ በእስራኤል ምድር ይሰባሰባሉ *(ሕዝ.37:1-14) ፣(ሕዝ.39:28)*::



*ፖርስትሮይካና ግላስኖስት ለምን ታየ?*

ይህን የምስራቁ ብሎክ (የምስራቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕብረት) ተብሎ የሚጠራውን መሠረት በማድረግ ይህን ለመረዳት ቀላል ሊሆን ቻለ:: በፖርስትሮይካና ግላስኖስት በተደረገው የተሃድሶ ትግል በ19 ኛው ምዕት ዓመት ጅማሬ ላይ በሶቪየት





መንግስት ላይ ውድቀትን አስከተለ:: ይህም ተአምር 850,000 የሩሲያ አይሁዶች ወደ ቅድስት አገር ለመመለስ የሚያስችላቸውን የመጀመሪያውን ሁኔታ አመቻቸ::

ዳግም ልደት ያገኙ (ክርስቲያን) የክርስቶስን መምጣት በየቀኑ የሚጠባበቀውን ያህል ማንኛውም እውነተኛ አይሁድ በእስራኤል የመሲሁን መምጣት በየቀኑ ይጠባበቃል:: ባለፉት 40 ዓመታት እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ታሪካዊ ማዳን የመጨረሻው ቀናት ምልክትና «ጌታ ፈጥኖ ሊመጣ ነው» የሚለውን የእኩለ ሌሊቱን ጩኸት መቃረቡን ያለ አንዳች ስህተት የሚያመለክት ምልክት ነው *(ማቴ.25:6)* ::

## ጌታ ቶሎ ይመጣል!

## 4. እስራኤል በመጨረሻዎቹ ቀናት

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ ከአለም ወደ አባቶቻቸው ምድር ቢመለሱም እስራኤል ባለማመን ያለችበት እውነት ወደ ጎን የሚባል አይደለም *(ሮሜ.11:20-23:)* ስለመሲሁ መምጣት የማይቋረጥ ጥበቃ ቢኖራቸውም እስከዚህ ቀን ድረስ ምንም ለውጥ አልሆነም:: በአሁኑ ጊዜ አይሁዶች እውነተኛው አዳኝ የሆነውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አልተገነዘቡትም:: ይህም ቢሆን ነገሮች እንደዚሁ የሚቀሩ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤል መሲሁን ባለመቀበሏ ምክንያት መውደቋን ወደ አሕዛብ ሁሉ መበታተኗንና የተቀደሰችው ምድር በአሕዛብ እንደምትደመሰስ ቢናገርም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ እንዳላቸውም ይናገራል:: ከታች በማነጻጸር በተጻፈው «እስከ» የሚለው ይህን ያመለክታል:: በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ «የእስራኤል ሕዝብ መበታተንን» ከሚያሳየው ቀይ መስመር ስር በመጨረሻው ቀናት በአስደናቂ ሁኔታ የእስራኤልን ሕዝብ መመለስ የሚያመለክቱ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ:: በቅርቡ እግዚአብሔር ራሱ ወደ ሕዝቡ ይመጣል፣ ምክንያቱም «መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፣ ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል» ተብሎ ተጽፏልና *(ሮሜ.11:26)*:: በበለጠ ለመረዳት ከዚህ በመቀጠል ስለዚህ ከሚናገሩት ጥቅሶች ጥቂቶቹን በማነጻጸር እንመለከታለን::

**የእስራኤል ውድቀት** — **ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ**

**እስከ**

« ....በእነርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ (ሮሜ.11:11) — « ... የአሕዛብ ሙላት እስኪ መጣ ድረስ (ሮሜ.11:25)

**የእስራኤል መረገጥ** — **የዓለም መንግሥታት ፍጻሜ**

**እስከ**

« ... ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች» (ሉቃ.21:24) — «የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ» (ሉቃ. 21:24)

**የእስራኤል መፈታት** — **መሲሁን መጥራት**

**እስከ**

«...እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ሆና ይቀርላችኋል::» (ማቴ.23:38) — «እስክትሉ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው» (ማቴ.23:39) ([illegible])

**የእስራኤል መታወር** — **የእስራኤል መመለስ**

**እስከ**

« ... እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው » (ሮሜ. 11:8) — «ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ መጽሐፍት በተነበቡ ጊዜ ሁሉ [illegible] መጋረጃ በልባቸው ይኖራል» (2ቆሮ. 3:15-16)





## ጥቂቱ የመዋጀት ታሪክ መስመር

# የአሕዛብ ዘመን

በዚህ ምዕራፍ የአሁኑን የመጨረሻውን ቀን ሁኔታ ለመገምገም ወደሚያስችለንና እጅግ አስፈላጊ ወደ ሆነው የመዋጀት ታሪክ ትኩረታችንን መልሰ ማድረግ ይኖርብናል:: ይህ ጊዜ በግምት ከ2600 ዓመታት ይጀመርና እስከ አሁን ድረስ እንደቀጠለ ያለ ነው:: በመዋጀት ዕቅድ ካርታ ላይ ዝቅ ብሎ ቀጭን በሆነ ሰማያዊ መስመር የተመለከተ (የተሰመረ) ነው:: ይህም «የአሕዛብ ዘመን» በመባል ተሰይሟል::

እንደምናውቀው ሁሉ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን የእስራኤል ሕዝብ በጣዖት አምልኮ ተጠምደው ነበር:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር በመራቅ የአሕዛብ ጣዖታትን አምላኪ ሆኑ:: የእስራኤል ህዝብ «እንደ አሕዛብ ያለ ርኩሰት ሁሉ መተላለፍን አበዙ፣ በኢየሩስሌምም የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ቤት» በማርከስ ለብዙ ዓመታት ኃጢዓት በመሥራት ቀጠሉ (*2ዜና.36:14*):: እግዚአብሔር ነቢያቱን በመላክ ቢያስጠነቅቃቸውም ንስሐ ለመግባት እንቢተኞች ሆኑ:: የእስራኤል ሕዝብ ግን «የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ እስኪወጣ ድረስ» ወደ እነርሱ በተላኩት ነቢያት ላይ የሚያሾፉ፣ የሚያላግጡና የሚንቋቸው ሆኑ:: (*2ዜና.36:16*):: በ606 ከ.ክ.ል.በፊት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ግብጻውያንን በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ባለው በከርከሚሽ ድል በማድረጉ (ኤር. 46:2) ባቢሎን በዓለም ገናና መንግሥት መሆን ጀመረ:: በዚሁ ጊዜ እስራኤል በባቢሎናውያን በመሸነፍ ምርኮኛ ሆና ወደ ባቢሎን ተወሰደች:: በኢየሩሳሌም የነበረው ካህኑ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር እንዴት ከቤተ መቅደሱ እንደተለየ መስክሯል (*ሕዝ.11:23*):: ከዚህ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በ586 ክ.ል.በፊት ባቢሎናውያን ቅድስቲቱን ከተማ ድል በማድረግ ቤተ መቅደሱን እንዳለ ደመሰሱት:: በዚያም የእግዚአብሔር አገዛዝ ከእስራኤል እንዳበቃ በግልጽ ለመታየት ቻለ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር እስራኤልንም ሆነ በእስራኤል በኩል ዓለምን አልመራም:: ይልቁንም ለው ለእግዚአብሔር ባለመሆኑና በሰይጣን ቁጥጥር ስር በመሆን ዓለምን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ የሚፈልግ ሆነ:: በ606 ክ.ል.በፊት በዓለምና በመዋጀት ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ተጀመረ::

| የእስራኤል ውድቀት | ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ |
|---|---|
| | እስከ |
| « ...በእነርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ (ሮሜ11:11) | « ... የአሕዛብ ሙላት እስኪ መጣ ድረስ (ሮሜ.11:25) |

| የእስራኤል መረገጥ | የዓለም መንግሥታት ፍጻሜ |
|---|---|
| | እስከ |
| « ... ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች» (ሉቃ.21:24) | «የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ» (ሉቃ. 21:24) |

| የእስራኤል መፈታት | መሲሁን መጥራት |
|---|---|
| | እስከ |
| «...እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ሆኖ ይቀርላችኋል።» (ማቴ.23:38) | «እላችኋለሁ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው» (ማቴ.23:39) (... ዳን.9:26) |

| የእስራኤል መታወር | የእስራኤል መመለስ |
|---|---|
| | እስከ |
| « ... እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው » (ሮሜ. 11:8) | «ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ መጽሐፍት በተነበቡ ጊዜ ሁሉ ያ መጋረጃ በልባቸው ይኖራል» (2ቆሮ. 3:15-16) |





## ጥቂሩ የመዋጀት ታሪክ መስመር

## የአሕዛብ ዘመን

በዚህ ምዕራፍ የአሁኑን የመጨረሻውን ቀን ሁኔታ ለመገምገም ወደሚያስችለንና እጅግ አስፈላጊ ወደ ሆነው የመዋጀት ታሪክ ትኩረታችንን መለስ ማድረግ ይኖርብናል። ይህ ጊዜ በግምት ከ2600 ዓመታት ይጀመርና እስከ አሁን ድረስ እንደቀጠለ ያለ ነው። በመዋጀት ዕቅድ ካርታ ላይ ዝቅ ብሎ ቀጭን በሆነ ሰማያዊ መስመር የተመለከተ (የተሰመረ) ነው። ይህም «የአሕዛብ ዘመን» በመባል ተሰይሟል።

እንደምናውቀው ሁሉ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን የእስራኤል ሕዝብ በጣዖት አምልኮ ተጠምደው ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር በመራቅ የአሕዛብ ጣዖታትን አምላኪ ሆኑ። የእስራኤል ህዝብ «እንደ አሕዛብ ያለ ርኩሰት ሁሉ መተላለፍን አበዙ፣ በኢየሩሰሊምም የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ቤት» በማርከስ ለብዙ ዓመታት ኃጢዓት በመሥራት ቀጠሉ (2ዜና.36:14)። እግዚአብሔር ነቢያቱን በመላክ ቢያስጠነቅቃቸውም ንስሐ ለመግባት እንቢተኞች ሆኑ። የእስራኤል ሕዝብ ግን «የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ እስኪወጣ ድረስ» ወደ እነርሱ በተላኩት ነቢያት ላይ የሚያሾፉ፣ የሚያላግጡና የሚንቋቸው ሆኑ። (2ዜና.36:16)። በ606 ክ.ክ.ል.በፊት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ግብጻውያንን በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ባለው በከርከሚሽ ድል በማድረጉ (ኤር. 46:2) ባቢሎን በዓለም ገናና መንግሥት መሆን ጀመረ። በዚሁ ጊዜ እስራኤል በባቢሎናውያን በመሸነፍ ምርኮኛ ሆና ወደ ባቢሎን ተወሰደች። በኢየሩሳሌም የነበረው ካህኑ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር እንዴት ከቤተ መቅደሱ እንደተለየ መስክሯል (ሕዝ.11:23)። ከዚህ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በ586 ክ.ል.በፊት ባቢሎናውያን ቅድስቲቱን ከተማ ድል በማድረግ ቤተ መቅደሱን እንዳለ ደመሰሱት። በዚያም የእግዚአብሔር አገዛዝ ከእስራኤል እንዳበቃ በግልጽ ለመታየት ቻለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር እስራኤልንም ሆነ በእስራኤል በኩል ዓለምን አልመራም። ይልቁንም ሰው ለእግዚአብሔር ባለመሆኑና በሰይጣን ቁጥጥር ስር በመሆን ዓለምን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ የሚፈልግ ሆነ። በ606 ክ.ል.በፊት በዓለምና በመዋጀት ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ተጀመረ።

## 1. የአራቱ ዓለም ኃያላን መንግሥታት መነሳት

ስለ አራቱ ታላላቅ ሰው ገዛሽ መንግሥታት መነሳት የሚናገረው የትንቢት ዕንብርት የሚገኘው በትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ነው። በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ እነዚህን መንግሥታት በሁለት ክፍሎ ያሳያል። በዳንኤል ምዕራፍ 2 ያለው የናቡከደነጾር ሕልም የእነዚህን አራት ውጫዊ ገጽታና በዓለም ከፍ ብለው መግነናቸውን የሚያሳይ ነው። ምዕራፍ ሰባት ደግሞ የእነዚህን አራት ነገሥታት ሰይጣናዊ ሲሆኑ ክፋትን የተሞላ ውስጣዊ ባሕርያቸውን ያሳያል። ስለመንግሥታቱ መነሳት የበለጠ ለመረዳት እንዲያስችለን በመጀመሪያ ዳንኤል ምዕ. 2 እና 7ትን እንመለከታለን።

### የናቡከደነጾር ሕልም

በባቢሎን ምርኮ ዘመን ነቢዩ ዳንኤል በንጉሡ ናቡከደነጾር አደባባይ ያገለግል ነበር። በዚህ አገልግሎቱ ላይ ሳለ ዳንኤል ከእግዚአብሔር የተለየ ስጦታ ሕልምን የመተርጎም ስጦታን አገኘ። ንጉሡ ናቡከደነጾር ከእንቅልፋ በነቃ ጊዜ መንፈሱን ያስጨነቀውን ሕልም ለንጉሡ ለመፍታት የተቻለው ነበር። *(ዳን.2:1)*

ንጉሡ ናቡከደነጾር በሰው አምሳል የሆነውን ግዙፍና የሚያንጸባርቅ ምስል አይቶ ነበር። ይህ ምስል ራሱ ወርቅ፣ ደረትና ክንዱ ብር፣ ሆድና ወገቡ ነሐስ፣ ሁለቱ ጭኖቹ ብረት፣ እግሮቹና ጣቶቹ ብረትና ሸክላ የተደባለቁ ነበር። የሰው እጅ ሳይነካው ድንጋይ ከተራራ ተፈንቅሎ በዚህ ምስል ላይ በመውደቅ ምስሉን ምንም ሳያስቀርለት እንደ አውድማ ዕብቅ ፈጨው። ከተራራ የተፈነቀለው ድንጋይ ምድርን የሚሞላ ታላቅ ተራራ ሆነ *(ዳን.2:31-35)* ።

ይህ ምን ማለት እንደሆነ ለንጉሡ ሊነግረው የቻለ ማንም አልነበረም። «በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ያሳየውን የዚህን ሕልም ትርጉም ሊፈታ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር» *(ዳን.2:36)*።

የናቡከደነጾር ሕልም በማከታተል በምድር ላይ የሚነሱትንና የሚወድቁትን አራት ታላላቅ መንግሥታትን የሚያሳይ ነበር። በዚህ ራዕይ የተመለካቹ ትኩረት በእነዚህ በሚነሱት ነገሥታት ላይ በሚታየው አንጸባራቂ በሆነው ውጫዊ ገጽታ ላይ ነበር። ከወርቁ፣ ከብሩና ወ.ዘ.ተ. ተጨማሪ በሳይ ናቡከደነጾር እጅግ ግዙፍና አንጸባራቂ ምስል ነበር የተመለከተው። (ዳን.2:31)





እነዚህ ባሕርያት የእነዚህ የአራቱን መንግሥታት ውጫዊ ገጽታና እንደዚሁም በመንግሥታቸው ከፍታና ገናንነት ፍጻሜ ሳይ መውደቃቸውን ያሳያሉ።

### የወርቁ ራስ

*«አንተ ንጉሥ ሆይ ! የሰማይ አምላክ መንግሥትንና ኃይል፣ ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ ነህ። በሚቀመጡበትም ሰፍራ ሁሉ የሰው ልጆችንና የምድር አራዊትን የሰማይ ወፎችንም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል፣ ለሁሉም ገዥ አድርጎሃል አንተ የወርቁ ራስ ነህ። (ዳን.2:37-38)*

ከአራቱ የዓለም መንግሥታት የመጀመሪያው በወርቁ ራስ የተመሰለው ከ606-538 ክ.ል.በፊት ድረስ የነበረው ባቤል ወይም ባቢሎን በመባል የሚጠራው የናቡከደናጾር መንግሥት ነበር። የመጀመሪያው ገዢ በመሆን እስከ 562 ክ.ል.በፊት ድረስ ገዛ። ከእርሱ በኋላ እስከ 560 ክ.ል.በፊት ዮርማሮዲክ ነገሠ። ቀጥሎም ኒሪማሊሶር እስከ 556 ክ.ል.በፊት ድረስ ገዛ። ከእርሱ ቀጥሎ ደግሞ እስከ 539 ክ.ል.በፊት ድረስ ናቦኒዱስ ገዛ። የመጨረሻው የባቢሎን መንግስት ንጉሥ በአሸናፊዎቹ በፋርስ መንግሥት የተገደለው ብልጣሶር ነበር። ሞቱም በዳንኤል ተመስከረ *(ዳን.5:30)*።

### የብሩ ደረት

*«ካንተ በኋላ ካንተ የሚያንስ ሌላ መንግሥት ይነሳል» (ዳን. 2:39)* ።

ሁለተኛው የዓለም መንግሥት የሜዶንና የፋርስ መንግሥት ሲሆን *(ዳን.6:1)* የተነሳው ከባቢሎን መንግሥት መውደቅ በኋላ በ536 ክ.ል.በፊት ነበር። ቢሆንም ይህ መንግሥት እንደ ባቢሎን የገነነ አልነበረም። ምክንያቱም በትንቢት በብር የተመሰለ ስለነበር ነው። የሜዶንና የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ የዓለም ገዢ ሆነ። በ536 ክ.ል.በፊት አይሁዶች ወደ እስራኤል ምድር እንዲመለሱ ፈቀደ (መጽሐፈ ዕዝራንና ነህምያን ይመልከቱ)። ከዚያም የሜዶንና የፋርስ መንግሥት ለ200 ዓመታት ያህል ቀጥሎአል።

## ሆድና ወገቡ ነሐስ የሆነው መንግሥት

*«ከዚያም በኋላ በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛ ሌላ ሦስተኛ የነሐስ መንግሥት ይነሳል»* (ዳን. 2:39)::

በ333 ክ.ል.በፊት የሜዶንና የፋርስን መንግሥት የተካው ሦስተኛው የዓለም መንግስት የግሪክ መንግስት ነበር:: ይህ መንግስት በሃይል ገንኖ የተነሳው የመቄዶንያው ንጉሥ ትልቁ እስክንድር የሜዶንና የፋርስን ንጉሥ ሳልሳዊ ዳርዮስን

በትንሿ እስያ በምትገኘው በቂሊቂያ በተደረገው በኢሱስ ጦርነት ላይ ድል ባደረገበት ጊዜ ነበር:: በሚቀጥሉት አስርት ዓመታት ውስጥ ትልቁ እስክንድር የግሪክን መንግሥት እስከ ሕንድና አፍጋኒስታን ድረስ አስፋፋ:: በ328 ክ.ል.በፊት ትልቁ እስክንድር የባክትሪያን ንጉስ ሴት ልጅን ሮክሳኒን አገባ:: ሆድና ወገቡ ናስ የሆነው የዚህን ወጣት መሪ ግዛት መስፋፋትን ያሳያል::


ትልቁ እስክንድር ሰኔ. 13 ቀን በ323 ክ.ል.በፊት በወባ በሽታ በባቢሎን ሞተ:: ሲሞት እድሜው ሰላሳ ሦስት አመት ነበር:: በእርሱ ሞት ምክንያት የዲአዶኪ ጦርነቶች ፈነዱ:: አራቱ ቅርብ ጓደኞቹና የጦር መኮንኖቹ የነበሩት ድል በማድረግ ትልቁን የግሪክን መንግሥት በመያዝ ለአራት ተከፋፈሉት:: ዲአዶኬ በመባል የሚታወቁ አራት መንግሥታት ተመሠረቱ:: ካሳንደር ግሪክን፣ ሊስማከስ ትሬስንና በትንሿ እስያ ያሉትን ሴሉከስ ሶርያንና ባቢሎንን፣ በጥሊሞስ ግብፅን በመያዝ ነገሡ:: እነዚህ አራቱ መንግሥታት ለብዙ ጊዜ አልቀጠሉም:: አንድ በአንድ በሮማውያን ድል ተመቱ::





### ናቡከደነጾር ያየው የአራቱ መንግሥታት ሕልም

ዳን. 2:1-49



**የወርቁ ራስ** — አንደኛው የዓለም መንግሥት የባቢሎን- መንግሥት 606-536 ክ.ክ.ል.በ

**የብር ደረት የሆነው** — ሁለተኛው የዓለም መንግስት የሜዶንና የፋርስ መንግሥት 536-333 ክ.ክ.ል.በ

**የነሐስ ወገብ የሆነው** — ሦስተኛው የዓለም መንግሥት የግሪክ መንግሥት 333-31 ክ.ክ.ል.በ

**ጭኖቹ የብረት የሆነው** — አራተኛው የዓለም መንግሥት የሮም መንግሥት 31 ክ.ክ.ል.በ.


ንጉሡ ናቡከደነጾር ያየው ምስል በሰው ምስል የተመሰሰ ነበር:: ይህም የሰው አገዛዝ በምድር ላይ መመስረቱን ያመለክታል:: በባቢሎን መንግሥት መመስረት የሰው አገዛዝ ተመሰረተ::

## ጭኖቹ ብረት የሆነው መንግስት

*«አራተኛውም መንግሥት ሁሉን እንደሚቀጠቅጥና እንደሚያደቅቅ ብረት ይበረታል እነዚህንም ሁሉ እንደሚፈጭ ብረት ይቀጠቅጥማል ይፈጭማል» (ዳን.2:40)::*

በዳንኤል ትንቢት አራተኛው የዓለም መንግስት የሮም መንግስት ነበር:: ሮማውያን ዓለምን ለመቆጣጠር እንደ ብረት ባለ ጥንካሬ ተዋግተዋል:: የዓለም ኃይል አገዛዝ መውደቅ የጀመረው የሮሙ ቄሳር አታቪያን መስከረም 2 ቀን 31 አ.ክ.ል.በ. የመጨረሻው የዲአዶካውያንን መንግሥት ታዋቂ በሆነው በአድቲዩም የባሕር ጦር ድል ባደረገበት ጊዜ ነበር:: ይህ መንግሥት በግብጿ ንግስት በክሌኦፓትራ ቁጥጥር ስር ነበር:: ክሌኦፓትራ የእስክንድር ጀኔራል የነበረው የጰጥሌምስ ተወላጅ ነበረች:: ቀሪው የግሪክ መንግሥት ከእርሷ መውደቅ ጋር ጠፋ:: ሮም በዚያን ጊዜ ለነበረው የዓለም መንግስት የበላይ ገዢ ሆነች:: አውግስጦስ ተብሎ የተጠራው ጁሊየስ አክታቪያን ከ27 ክ.ል.በ. ጀምሮ የሮም ገዢ ሆነ:: በእርሱ ዘመን የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ተወለደ (*ሉቃ.2:1-7*):: ጌታ ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ጢባርዮስ ቄሳር የሮም ገዢ ነበር (*ዮሐ.19:13-19*):: ለብዙ ምዕተ ዓመታት የሮም መንግሥት የዓለምን መንግስት ታሪክ ተቆጣጠረች:: በ395 ዓ.ም የሮም መንግስት የዓለምን መንግሥት የምስራቁ የሮም መንግሥትና የምዕራቡ የሮም መንግስት በመባል ተከፋፈለ:: በዳንኤል ትንቢት በብረት የተመሰሉት ሁለቱ ጭኖች እነዚህን መንግስታት የሚያመለክቱ ነበሩ:: (*ዳን.2:33፣40-43*)

ከዚህ በታች ያለው ማፕ የሚያሳየው በ395 ዓመት የሮም ግዛት መከፋፈል
1. የምዕራቡ የሮም መንግስት
2. የምስራቁ የሮም መንግስት




- ይህ ስዕል የሚያሳየው የሰውን ግማሽ የታችኛውን የአካል ክፍል ነው:: እግሮቹ የሚያሳዩት የሮምን በሁለት ክፍሎች መከፈልን ነው::
- እነኚህ በሁለቱ መንግስታት ስር የነበሩ አገሮች በሙሉ አንድነት ሆነው በአሁኑ ዘመን የዓለም አቀፍ የሆነውን ፀረ ክርስቶስ መንግስት በመገንባት ላይ ናቸው::





ይህ የብረቱ መንግሥት ወደ ፍጻሜ መጥቷል:: የምዕራቡ የሮም መንግሥት በ476 ዓ.ም. ወደቀ:: የምስራቁ የሮም መንግሥት ከ1000 ዓመታት በኋላ በ1453 ዓ.ም. ወደቀ::

አራቱ የዓለም ኃያላን መንግስት ዛሬ ታሪክ ሆነው ቀርተዋል:: በትንቢት እንደተነገረው ተነስተው ወድቀዋል:: እጅ ሳይነካው ተፈንቅሎ ስለ ወረደው ድንጋይ ወደ ፊት በስፋት እንመለከታለን:: (ዳን.2:34)

## የአራቱ አራዊት ገጽታ

ብልጣሶር የባቢሎን ንጉሥ ሆኖ በሚገዛበት ዘመን ነቢዩ ዳንኤል ሌላ ራዕይ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ነበር:: ዳንኤልም ተናገረ እንዲህም አለ:-

*«በሌሊት በራዕይ አየሁ እነሆም አራቱ የሰማይ ነፋሳት በታላቁ ባሕር ላይ ይጋጩ ነበር:: አራትም ታላላቅ አራዊት ከባሕር ወጡ:: እያንዳንዲቷም ልዩ ልዩ ነበረች» (ዳን.7:2-3)::*

ጥቂት ጥቅሶች አለፍ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ አራቱ አራዊት ምን እንደሆኑ እንዲህ በማለት ይገልጻል::

*«እነዚህ አራቱ ታላላቅ አራዊት ከምድር የሚነሱ አራት ነገሥታት ናቸው» (ዳን.7:17)::*

እነዚህ መንግስታት ማን እንደሆኑ ቀደም ብለን አውቀናቸዋል:: ቀደም ብሎ ናቡከደነጾር በሕልም ያያቸው አራቱ የዓለም መንግሥታት ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም ናቸው:: በመጀመሪያ ግዙፍ በሆነው በሰው ምስል የታዩ ነበር (ዳን.2:31-45):: አሁን ደግሞ በአራት ታላላቅ አራዊት አምሳያ ተገልጸዋል:: እኛ የምንነጋገረው ስለእነዚሁ የዓለም መንግስታት ነው:: ምክንያቱም የመዋጀት ታሪክ ከእነዚህ አራቱ መንግስታት ውጪ የሚሰራ አይደለም:: ጠለቅ ብለን የዳንኤልን ምዕራፍ ስባት ስንመለከት እነዚህ አራዊት በተፈጥሮ ከሚታዩት አራዊት የተለዩ አስፈሪ ግዙፍ የሆኑ አራዊት ናቸው:: ምክንያቱም የመጀመሪያው አውሬ እንደ ንስር ክንፍ ባለው አንበሳ (ዳን.7:4)፣ ሁለተኛው አውሬ በድብ የተመሰለው «ተነስተህ እጅግ ሥጋ ብላ» የሚል ትዕዛዝ ተቀባይ በሆኑ (ዳን.7:5)፣ ሦስተኛው አራት ክንፎች ባሉት ነብር የተመሰለው (ዳን. 7:6)፣ አራተኛው አውሬ ደግሞ አስር ቀንዶች ባለው አስፈሪ ሁሉን በሚያደቅ፣ ተመስለው የተገለጹ ናቸው (ዳን.7:7):: በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ እንደነዚህ ያሉ አስፈሪና ታላቅ አራዊት የትም

አይገኙም። ዳንኤል «ሕልሙን ጻፈ ዋነኛውንም ነገር ተናገረ» በማለት ጌታ የገለጠለትን በትክክል መመስከሩ ተጽፎ ይገኛል (ዳን.7:1)። ስለዚህም የእነዚህ ራዕይ ፍቺ ምን እንደሆነ መጠየቅ ይኖርብናል። በመጀመሪያ እንደዚህ አይነቱን ገለጻ ለመጽሐፍ ቅዱስ እንግዳ ነገር እንዳይደለ ልንገነዘብ ያስፈልገናል። ብዙ ጊዜ በአይን የማይታዩትን መንፈሳዊ እውነቶችን ለመግለጽ ይጠቅማል። ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ የማይታየውን የሰይጣንን ኃይላት «በእባብና በጊንጥ» በመምሰል ገልጾታል (ሉቃ.10:19)። እነዚህን ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከእግራቸው በታች እንዲረግጧቸው ስልጣን ሰጥቷቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ በብሉይ ኪዳን «በአንበሳና ዘንዶ» በራዕይ ዮሐንስ ደግሞ ሰይጣን በ «ታላቅ ቀይ ዘንዶ» ተመስሎ ተገልጿል (መዝ.(91):13፤ ራዕ.12:3፤9)። የዳንኤል አዲሱ ራዕይ ከዚህ በላይ ከተገለጹት ምሳሌዎች ጋር ተመሳሳይ ነው። በዳንኤል ምዕራፍ ሁለት ላይ ከታዩት አራቱ የዓለም ኃያላን መንግስታት ጋር እነዚህ ታላላቅ አራዊት የተመሳሰሉ መንግስታት ናቸው በአራት ንጽጽር ተመድበዋል። ባቢሎን በአንበሳ፣ ሜዶንና ፋርስ በድብ፣ ግሪክ አራት ራሶች ባለው ነብርና ሮም አስር ቀንዶች ባለው አስፈሪ አውሬ ተመስለዋል። በዳንኤል ምዕራፍ ሰባት የሚነሱት መንግስታት አራዊት ናቸው ማለቱ ሳይሆን ውስጣዊ የሆነ የአውሬ ባሕርይ እንዳላቸው ሲያሳይ በዳንኤል ምዕራፍ ሁለት ያለው ደግሞ ውጫዊ አስደናቂ ሁኔታቸውን ያሳያል። የዳንኤል ምዕራፍ ሰባት የአራቱ አራዊት ራዕይ ድብቅ ሰይጣናዊና አጥፊ የሆነውን የአውሬነት ባሕርያቸውን ያሳያል።

## «ሰው ያለ እግዚአብሔር አውሬ መሆኑ»

ባቢሎን፣ ሜዶንና-ፋርስ፣ ግሪክና ሮም እግዚአብሔር የለሽ መንግስት ነበሩ። ያለ እግዚአብሔር መግዛታቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን በመቃረን (በእግዚአብሔር ምትክ) ይገዙ ነበር።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ጊዜ በዚህች ምድር ላይ የመግዛትን ስልጣን ሰጠው (ዘፍ.1:28)። እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ቃል ኪዳን አደረገ (ሆሴ. 6:7)። ሰውም ይህችን ውብ ዓለም በእግዚአብሔር ስልጣን ስጪነት እንዲገዛ አድርጎ ሾመው። ሰው በመውደቁ የሰይጣንና የሞት ተገዢ ሆነ።





«እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» (ዘፍ.3:5) ለሚለው የሰይጣን ሹክሹክታ የሚታዘዝ ሆነ። ሰው ራሱን የራሱ አምላክ በማድረግ በእግዚአብሔር ላይ መመካቱን ትቶ ዓለምን ለመግዛት ፈለገ። እግዚአብሔር ከኖህ ጥፋት በኋላ ሰዎችን በምድር ላይ ለመበተን ተገድዶ ነበር፣ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚቃረን መንግስት ለመመስረት አስበው ስለነበር ነው (ዘፍ.11:1-9)።

ይህች መንግስት በዓለም ከፍተኛ የሆነችው ባቢሎን ነበረች። ሆኖም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለመመስረት አብርሃምንና የእስራኤልን ነገድ መረጠ። ኢየሩሳሌምን የእርሱ ማደሪያ ቦታ፣ መካከለኛና፣ የዓለም ዋና ከተማ እንድትሆን አደረጋት። እስራኤል ከዓላማዋ በመውደቋና ጣዖት አምላኪ በመሆኗ ለአራቱ ታላላቅ የዓለም መንግስታት መነሳት በር ተከፈተ። በ606 ከ.ል.በፊት ከአራቱ ኃያላን መንግስታት ባቢሎን የመጀመሪያዋ በመሆን ተነሳች።

ዳንኤል ምዕራፍ አራት ከእነዚህ አራቱ የዓለም መንግስታት ውስጥ የመጀመሪያውን መንግስትና ገዢ የባቢሎንን ንጉስ የናቡከደነጾርን ትዕቢትና ውድቀት ይገልጻል።

*«ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት፣ ለግርማዬ ክብር፣ የመንግሥቴ መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን?»* በማለት በትዕቢት ቃል ራሱን ሲያከብር ይታያል (ዳን. 4:30)።

ይህ ባሕርይ በኃጢዓት የተሞላውንና አመጸኛ የሆነውን የሰውን ባሕርይ ይገልጻል። ናቡከደናጾር ራሱን አምላክ አደረገና ራሱን አምላኪ ሆነ። ወደፊት እንደምናየው የክርስቶስ ተቃዋሚም ባሕርይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተመሰለ ነው። እርሱም አንድ ቀን ራሱን አምላክ በማድረግ ያውጃል። (2ተሰ.2:4)

## ዳንኤል ያየው የአራቱ አራዊት ምስል

ዳን. 7:1-28



**የአንበሳ ምስል**

አንደኛው የዓለም መንግሥት
**የባቢሎን- መንግሥት**
**606-536 ከ.ክ.ል.በ**



**የድብ ምስል**

ሁለተኛው የዓለም መንግስት
**የሜዶንና የፋርስ መንግሥት**
**536-333 ከ.ክ.ል.በ**



**ባለ አራቱ ራስ ነብር**

ሦስተኛው የዓለም መንግሥት
**የግሪክ መንግሥት**
**333-31 ከ.ክ.ል.በ**



**አስር ቀንድ ያለው አውሬ**

አራተኛው የዓለም መንግሥት
**የሮም መንግሥት**
**31 ከ.ክ.ል.በ.**

**እነዚህ አስፈሪ እንስሶች ለዳንኤል የታዩት ከውጭ ያማረና ያሸበረቀው የአራቱ መንግስታት መልክ ሳይሆን በውስጣቸው ያለው አስቀያሚ የአጋንንታዊውን እውነተኛ ጠባይ ነው።**





የባቢሎናውያን ንጉስ ትዕቢት አስደንጋጭ ወደ ሆነው ውድቀት መራው። ለሰባት ዓመታት እግዚአብሔር መንግስቱን ወሰደበት። «በዚያም ሰዓት ነገሩ በናቡከደነጾር ላይ ደረሰ፣ ጠጉሩም እንደ ንስር፣ ጥፍሩም እንደ ወፎች፣ እስኪረዝም ድረስ ከሰዎች ተሰይቶ ተሰደደ፣ እንደ በሬም ሣር በላ፣ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ» (*ዳን.4:33*)። የወርቁ ራስ የሆነ ናቡከደነጾር ንስሃ እስኪገባ ድረስ እንደ እንስሳ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ አስደናቂ የሆነው የሰው ውጫዊ ባሕርይ የውስጡ የአውሬነቱ ባሕርይ መሆኑን በግልጽ ያስረዳል። አመጸኛ የሆነው ንጉስ እንደ እንስሳ በምድረ በዳ የሚኖር ሆነ (ዳን. 2:38)። በዚህም እንደ አራዊት በሆነ ባሕርዩ ለዓለም ተገለጸ።

*«ሰብዕና ያለ እግዚአብሔር እንደ እንስሳ ይሆናል»* ወይም በቀላሉ *«ሰው ያለ እግዚአብሔር ሲሆን እንስሳ ይሆናል ማለት ነው።»*

ብዙ ጊዜ የዓለም መሪዎች ፣ ኃያላንና ነገስታት በሚያጠፋ እንስሳ ይመሰላሉ። የዓለምን ሰዎች ይጨቁናሉ፣ ለራሳቸው መጠቀሚያ ያደርጋሉ፣ ጦርነቶችን ያስነሱና ደም ያፋስሳሉ። እግዚአብሔርን በመቃረን ራሳቸውን በእግዚአብሔር ምትክ በማድረግ የሚገዙ አመጸኛ መሪዎች ራሳቸው አውሬ ከመሆናቸው ሌላ በእነርሱ የሚገዙትም ሰዎች ደግሞ እንደ አውሬዎች ይሆናሉ። አመጸኛውና ሰይጣናዊው ዓለምን የሚያስጨንቀው የመጨረሻው አውሬ ፀረ ክርስቶስ ይሆናል።

## 2. ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ

ወደ ፍጻሜው ዘመን እየተጠጋን በሄድን ቁጥር ግልጽ ሆኖ የሚታየው ነገር ፀረ ክርስቶስ መንግስት እንዴት እንደሚመሠረትና ፀረ ክርስቶስ እንዴት ፈጥኖ እንደሚገለጽ ነው። የአዲስ ኪዳን አማኞች እንደመሆናችን መጠን በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለ ፀረ ክርስቶስ የመንግስቱ መገለጥ እንዴት እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛውን ገለጻ ልናውቅ ይገባናል።

ፀረ ክርስቶስ መንግስት በድንገት ከሰማያት የሚወርድ አይደለም። ነገር ግን ደህንነትን ባላገኙ በብዙ ቢሊዮን በሚቆጠሩ በዚህች ምድር ላይ በሚኖሩ ሰዎች ሕብረት የሚመሰረት ነው። እነሳሉ ከማንኛውም ነገድ፣ ባሕል፣ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና የሃይማኖት ክፍል ቢሆን ልዩነት የሚያመጣ አይደለም። የክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት የሰዎች (ኃጢዓተኝነት) እየጨመረ የመሔዱ ውጤት ነው።

ፀረ ክርስቶስ በዓለም የሚገለጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይልና በክብር ከመመለሱ በፊት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (2ተሰ.2:1-12) :: በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ የሚኖሩት ሕዝቦች «ይድኑ ዘንድ የእውነትን ቃል ስላልተቀበሉ» በእርሱ እጅ ይወድቃሉ:: (2ተሰ.2:10)

የእውነተኛው ንጉስ እውነተኛው ወንጌል ለሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ በመላው ዓለም ተሰብኳል (ዮሐ.14:6፣18:37):: አውሮፓ የክርስቲያን አምብርት በመባል ተገልጾ ነበር:: ምክንያቱም ወንጌል በስፋት በዚያ ተሰብኮ ስለነበር ነው:: ከጊዜ በኋላ ሁኔታዎች ሁሉ ተለዋወጡ:: ከሁለት ሺህ የጸጋና የደህንነት ዓመታት የመጨረሻ ፀረ ክርስቶስ ሲነሳ ወንጌልን በተቃወሙትና በናቁት እምነታቸውንም በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባላደረጉት ላይ ፍርድ ይሆናል:: ስለሆነም ፀረ ክርስቶስ መነሳት የሚሆነው ወንጌልን ሰምተው ለመቀበል ባልፈለጉት ሕዝብ መካከል ነው:: ፀረ ክርስቶስ መነሳት በምድር ላይ ከሰዎች አመጸኝነትና ክርስቶስን ከመቃወም ጽዋ መሙላት የተነሳ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ የሚናገሩ ስምንት ምዕራፎች አሉ:: እነርሱም:-

1. ዳንኤል 2:1-49
2. ዳንኤል 4:1-34
3. ዳንኤል 7:1-28
4. ዳንኤል 9:1-27
5. ማቴዎስ 24:1-31
6. 2ተሰሎንቄ 2:1-12
7. 1ዮሐንስ 2:18-22 ፣4:3
8. ራዕይ 11:1-19፣21

ስለዚህ ትምህርት ጥናት ስናደርግ የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች መዘንጋት የለብንም::

## 1. ፀረ ክርስቶስ ሰው ነው

ሰዎች የሚያከብሩት፣ የመጨረሻው አስተዳዳሪና መሪ በኃጢዓት የተሞላው የመጨረሻው ሰው ነው:: በሰዎች ላይ ከፍተኛውን ክፋት የሚያሰራጭ ነው:: ፀረ ክርስቶስ ሰዎች የሚጠብቁት ከፍተኛና የተአምራት ሰው ነው:: በሰዎች መካከል ሰላምን የሚመሰርት መስሎ የሚታይ ብቻ ሳይሆን የዓለምን የኢኮኖሚ ችግርና ዓመጽ እንደሚያስወግድም ተስፋ የሚሰጥ ነው::





## 2. ፀረ ክረስቶስ መንግስት አለው

ዛሬ ይህ ጨለማ መንግስት ጥላውን በዓለም ላይ እያጠላ ነው:: ጠቅላላ ዓለምም ወደዚሁ እየደረሰ ነው:: በሚቀጥለው ጥናታችን የፀረ ክርስቶስ መንግስት መሠረቱ የት እንደሆነ እንመለከታለን::

### የፀረ ክርስቶስ መንግስት እና አራቱ- የጥንቱ ዓለም መንግስታት መታደስ

የፀረ ክርስቶስ መንግስት ከጥንቱ ከአራቱ የዓለም ኃያላን መንግስታት ከነበሩት ከባቢሎን፣ ከሜዶንና ፋርስ፣ ከግሪክና ከሮም አዋሳኝ አገሮች፣ ባሕሎችና መንፈሳዊ ኃይላት የሚመሠረት ነው:: አዲስ ኪዳን ይህን ግልጽ በሆነ መንገድ እንደሚከተለው ያሳያል::

*«አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፣ አስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፣ በቀንዶቹም ላይ አስር ዘውዶች፣ በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበር:: ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፣ እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች፣ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበር:: ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው» (ራዕ.13:1-2)::*

በዚህ በራዕይ የታየውና የሚነሳው አውሬ ፀረ ክርስቶስ ነው:: ባሕሩ እንደ (መዝ.(65):7፤ ኢሳ.17:12-13) የውሃ ባሕር ሳይሆን ሰዎችና አሕዛብ ናቸው::


ይህንን ትንቢት ለመረዳት መለስ ብለን በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን አንድ ጊዜ መቃኘት ይኖርብናል:: ነቢዩ ዳንኤል በራዕዩ በአራት አራዊት የተመሰሉትን አራቱን የዓለም መንግሥታት (ባቢሎንን፣ ፋርስን፣ ግሪክንና ሮምን) አይቷል (ዳን.1:18):: እነዚህ አራዊት የወጡት ከባሕር ውስጥ ነበር:: ባሕሩም ሕዝብን የሚያመለክት ነበር:: ዳን.7:1-28 ከራዕ.13:1-2 ጋር ስናወዳድር ብሉይና አዲስ ኪዳን ትንቢታዊ ግንኙነት እንዳላቸው በግልጽ እንረዳለን:: ዳንኤል አራቱ የዓለም መንግስታት ከሕዝብ እንደሚወጡ እንዳየው ሁሉ ዮሐንስ ደግሞ ፀረ ክርስቶስ ከሕዝብ መካከል እንደሚነሳ ገልጿል:: ስለዚህ አውሬ ጠለቅ ብለን ስንመለከት የአራቱ አራዊት ጥምር ሆኖ እናገኘዋለን ምክንያቱም:-

1. አፉ አንበሳ
2. እግሮቹ የድብ
3. መልኩ የነብርና
4. አስር የብረት ቀንዶች ነበሩት

በዚህ ገለጻ የጥንቶቹን የዓለም መንግስታት ለመረዳት የሚያስቸግር አይደለም። ወደ ፊት እነዚህ ነገስታት የሚነሱት ተራ በተራ ሳይሆን በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ ነው። በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚነሳው ፀረ ክርስቶስ የእነዚህ የአራቱ መንግስት መታደስ ነው እንጂ ሌላ አለመሆኑ ግልጽ ሊሆን ያሻል። በደህንነት ዕቅድ ካርታ ላይ ያለው ጥቁሩ ቀስት ወደዚህ ሀብረት የሚያመለክት ነው።

አራቱ የጥንቱ መንግስታት ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ ግሪክና ሮም ተራ በተራ እየከሰሙ የሔዱ ቢሆንም በፍጻሜ ዘመን እንደገና ተመልሰው ይታያሉ። የሚከተለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስዕላዊ መግለጫ መመልከት ይቻላል።

1. «አፉ የአንበሳ» የሆነው በዳን.7:4 በአንበሳ ከተመሰለው ከባቢሎን የሚመጣ ነው።
2. «እግሮቹ በድብ» የተመሰለው በዳን.7:5 በድብ ከተመሰለው ከሜዶንና ፋርስ የሚመጣ ነው።
3. «በነብር መልክ» የተመሰለው በዳን7:6 አራት ራሶችና አራት ክንፎች ባለው በግሪክ መንግሥት የተመሰለውን ያመለክተናል።
4. በ «አስር የብረት ቀንዶች» የተመሰለው በዳን.7:7-8 አስር ቀንዶችና ብረት ጥርሶች ባሉት የተመሰለውን የሮምን መንግሥት ያስታውሰናል።








በአራቱ በወደቁት መንግሥታት የነበሩት ባሕርያት በመጨረሻው ቀናት በሚነሳው ፀረ ክርስቶስ በአንድነት ተጣምረው የሚታዩ ይሆናሉ። የዚህ አስፈሪ የሆነው መንግስት የግዛቱ እምብርት በባቢሎን፣ በሜዶንና ፋርስ፣ በግሪክና በሮም ድንበሮች ላይ ይሆናል። ስለሆነም የዚህ ፀረ ክርስቶስ መነሳት ከእነዚህ መንግስታት ከአንዱ ነው ብሎ መጠበቁ የማያስኬድ ነው። ለምሳሌ ከሮም መንግስት ብቻ ይነሳል ስለዚህ በተሰጠው ትንቢታዊ ቃል ግልጽ የሆነ ነገር ነው። ልክ አስፈሪ የሆነው «አውሬ ከባሕር እንደ ወጣ» (ራዕ. 13:1) አራቱ ታላላቅ አውሬዎች (ዳን. 7: 3-17) አራቱ የጥንቱ መንግስታት አንድ ሆነው በመታደስ ፀረ ክርስቶስ መንግስት ይገለጻሉ።

| የፀረ ክርስቶስ መንግስት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዳን.2:1-49 | | ዳን.7:1-28 | የዓለም መንግሥታት | ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ |
| ራሱ የወርቅ |  | አንበሳ | ባቢሎን | የአንበሳ አፍ |
| ደረቱ የብር | | ድብ | ሜዶንና ፋርስ | እግሮቹ የድብ |
| ወገቡ የነሐስ | | ባለ አራቱ ራስ ነብር | ግሪክ | አካሉ የነብር |
| ጭኖቹ የብረት | | ባለ አራቱ ቀንድ አስፈሪው አውሬ | ሮም | የአስፈሪው አውሬ አስሩ ቀንዶች |

## የፀረ ክርስቶስ መንግስት - የሰይጣን አምሳያ

እንደተለመከትነው የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ መንግስት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአስፈሪ አውሬ ተመስሏል:: ከተጠቀሱት አስር ቀንዶች ሌላ ይህ አውሬ ሰባት ራሶች አሉት (ራዕ.13:1):: ቀጥሎ በምናደርገው ጥናት የዚህን አውሬ የኋላ ታሪኩንና ፍቺውን ስንመረምር ይህን ትንቢት በትክክል ልንረዳ እንችላለን::

ይህ አውሬ ለምን ሰባት ራሶች ኖሩት ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደገና ስለ አራቱ መንግስታት (ስለ ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም) በዳንኤል መጽሐፍ በአራት ታላላቅ አራዊት የተመሰሉትን መመልከት ይኖርብናል (ዳን.7:1-28):: በአውሬው ላይ ስላሉት ራሶች ጠለቅ ብለን ገለጻውን ስንመረምር የሚከተለውን እንረዳለን::

| | | |
|---|---|---|
| ባቢሎን | በአንበሳ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ሜዶንና ፋርስ | በድብ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ግሪክ | በነብር የተመሰለው | አራት ራስ |
| ሮም | በአስፈሪው አውሬ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| | *በጠቅላላ ድምር* | ሰባት ራስ |

### ተምሳሌተ ሰይጣን

ከላይ በተመለከትነው ንጽጽር *በራዕ.13:1* ባለው ፀረ ክርስቶስ መንግስት ላይ ያሉት ሰባቱ ራሶች *በዳንኤል 7* የተጠቀሱት የአራቱ የዓለም መንግስት ራሶች ጠቅላላ ድምር ነው:: ይህ እንደገና የሚያረጋግጥልን ነገር በመጨረሻዎቹ ቀናት ባቢሎን ሜዶንና ፋርስ፣ በግሪክና ሮም ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ጋር በማበር ተሐድሶ እንደሚያደርጉ ነው:: ሆኖም በዚህ ነጥብ ላይ አንድ እርምጃ ወደፊት መሔድ ይኖርብናል:: እየተነጋገርን ያለው የሰባቱ ራሶች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ::

*«ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ፣ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶችም ነበሩት፣ በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ» (ራዕ.12:3)*

ይህ ትልቁ ዘንዶ ማን ነው? ዘንዶው «የቀደመው እባብ ዲያብሎስና ሰይጣን» እንደሆነ ተገልጾአል (*ራዕ.12:9*):: ፀረ ክርስቶስ መንግስት ሰባት ራሶች የተመሰለው የሰይጣን ተምሳሌት ናቸው:: ሰይጣን ራሱ ደግሞ በሰባት ራሶች ባሉት ዘንዶ ተመስሏል:: ስለሆነም ሰይጣን ዋናው ተምሳሌት ነው::





*ምሳሌ:- አራቱ የዓለም መንግስታት*

ሰይጣን በዓለም ላይ ስልጣን የተሰጠው ስለሆነና *(ሉቃ.4:6)* እስራኤልም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመሆን በመውደቁ (እግዚአብሔር በሕዝቡ በኩል መለኮታዊ አገዛዙን ያላደረገበት ምክንያት) በ606 ክ.ል.በፊት የዓለም ስልጣን ላልዳኑት ሕዝብ የተሰጠ ሆነ:: ይህን የአሕዛብ ዘመን ጅማሬ ብለን እንጠራዋለን:: *(ሉቃ.21:24)* ሰይጣን ሳይከለከል በእነዚህ አሕዛብ ስልጣኑን ሊለማመድ ቻለ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው በጠቅላላው በራሱ የተመሰሉትን ሰባት ታላላቅ ራሶች ከእነዚህ የዓለም አሕዛብ እንዲወጡ አድርጓል::

| | |
|---|---|
| **1ኛው ራስ: የባቢሎን አገዛዝ** | **ናቡከደነፆርና ተከታዮቹ(ወራሾች)** |
| **2ኛው ራስ: የሜዶንና ፋርስ አገዛዝ** | **ቂርስና ተከታዮቹ (ወራሾቹ)** |
| **የግሪክ አገዛዝ** | **ትልቁ እስክንድርና አራቱ ተከታዮቹ** |
| **3ኛው ራስ: ግሪክ፣ሶርያ ፣ባቢሎን** | **ሴሉከስና ወራሾቹ** |
| **4ኛው ራስ: ግሪክ፣ግብፅ** | **በጥሊሞስና ወራሾቹ** |
| **5ኛው ራስ: ግሪክ፣ትሬስና ትንሹ እስያ** | **ሊስማከስና ወራሾቹ** |
| **6ኛው ራስ: ግርክ፣ሜቄዶን** | **ካሳንደርና ወራሾቹ** |
| **7ኛው ራስ: የሮም አገዛዝ** | **አውግስጦስና ወራሾቹ** |

በገሃዱ ዓለም እነዚህ ሰባቱ ራሶች የአራቱ የጥንቱ መንግስታት አመጸኛ በሆኑት ሰባት መንግስታት ተመስለዋል:: ገሃድ ባልሆነው ዓለም ግን ከእነዚህ መንግስታት በስተኋላ ሆኖ የሚገዛውን ሰይጣንን ይወክላሉ:: ሆኖም አራቱ የዓለም መንግስታት ከመንግስቶቻቸው (ሰባት ራሶች) ጋር ጠፍተዋል:: ስለዚህ ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት ሰይጣናዊ ምሳሌ ሆነዋል::

### ምስሉ: ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ

በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን መግለጫ እንመልከት:: ሰባቱም ራሶች በመልክዓ ምድር አቀማመጥ የሚያገኙት በዓለም የእግዚአብሔር ዋና ከተማ በሆነችው በኢየሩሳሌም አጠገብ (አካባቢ) ነው:: በመግለጫው ላይ ያሉት ሰባቱ ጥቋቁር ነጠብጣብ የሰባቱ ሰይጣናዊ ራሶች የኃይላቸው እምብርት ናቸው:: ሰባቱ ዋና ከተማዎች በአራቱ የዓለም መንግሥታት ውስጥ የተመሰከቱት ናቸው:: ሦስቱ በእስያ፣ ሦስቱ በአውሮፓና አንዷ በአፍሪካ ነው የሚገኙት::

## የፀረ ክርስቶስ መንግስት - የሰይጣን አምሳያ

እንደተለመከትነው የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ መንግስት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአስፈሪ አውሬ ተመስሏል:: ከተጠቀሱት አስር ቀንዶች ሌላ ይህ አውሬ ሰባት ራሶች አሉት (ራዕ.13:1):: ቀጥሎ በምናደርገው ጥናት የዚህን አውሬ የኋላ ታሪኩንና ፍቺውን ስንመረምር ይህን ትንቢት በትክክል ልንረዳ እንችላለን::

ይህ አውሬ ለምን ሰባት ራሶች ኖሩት ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደገና ስለ አራቱ መንግስታት (ስለ ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም) በዳንኤል መጽሐፍ በአራት ታላላቅ አራዊት የተመሰሉትን መመልከት ይኖርብናል (ዳን.7:1-28):: በአውሬው ላይ ስላሉት ራሶች ጠለቅ ብለን ገለጻውን ስንመረምር የሚከተለውን እንረዳለን::

| | | |
|---|---|---|
| ባቢሎን | በአንበሳ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ሜዶንና ፋርስ | በድብ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ግሪክ | በነብር የተመሰለው | አራት ራስ |
| ሮም | በአስፈሪው አውሬ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| | *በጠቅላላ ድምር* | ሰባት ራስ |

## ተምሳሌተ ሰይጣን

ከላይ በተመለከትነው ንጽጽር *በራዕ.13:1* ባለው ፀረ ክርስቶስ መንግስት ላይ ያሉት ሰባቱ ራሶች *በዳንኤል 7* የተጠቀሱት የአራቱ የዓለም መንግስት ራሶች ጠቅላላ ድምር ነው:: ይህ እንደገና የሚያረጋግጥልን ነገር በመጨረሻዎቹ ቀናት ባቢሎን ሜዶንና ፋርስ፣ በግሪክና ሮም ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ጋር በማበር ተሐድሶ እንደሚያደርጉ ነው:: ሆኖም በዚህ ነጥብ ላይ አንድ እርምጃ ወደፊት መሔድ ይኖርብናል:: እየተነጋገርን ያለው የሰባቱ ራሶች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ::

*«ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ፣ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶችም ነበሩት፣ በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ» (ራዕ.12:3)*

ይህ ትልቁ ዘንዶ ማን ነው? ዘንዶው «የቀደመው እባብ ዲያብሎስና ሰይጣን» እንደሆነ ተገልጾአል (*ራዕ.12:9*):: ፀረ ክርስቶስ መንግስት ሰባት ራሶች የተመሰለው የሰይጣን ተምሳሌት ናቸው:: ሰይጣን ራሱ ደግሞ በሰባት ራሶች ባሉት ዘንዶ ተመስሏል:: ስለሆነም ሰይጣን ዋናው ተምሳሌት ነው::





*ምሳሌ:- አራቱ የዓለም መንግስታት*

ሰይጣን በዓለም ላይ ስልጣን የተሰጠው ስለሆነና *(ሉቃ.4:6)* እስራኤልም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመሆን በመውደቋ (እግዚአብሔር በሕዝቡ በኩል መለኮታዊ አገዛዙን ያላደረገበት ምክንያት) በ606 ክ.ል.በፊት የዓለም ስልጣን ላልዳኑት ሕዝብ የተሰጠ ሆነ:: ይህን የአሕዛብ ዘመን ጅማሬ ብለን እንጠራዋለን:: *(ሉቃ.21:24)* ሰይጣን ሳይከለክል በእነዚህ አሕዛብ ስልጣኑን ሊለማመድ ቻለ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው በጠቅላላው በራሱ የተመሰሉትን ሰባት ታላላቅ ራሶች ከእነዚህ የዓለም አሕዛብ እንዲወጡ አድርጓል::

| | |
|---|---|
| 1ኛው ራስ: የባቢሎን አገዛዝ | ናቡከደነፆርና ተከታዮቹ(ወራሾች) |
| 2ኛው ራስ: የሜዶንና ፋርስ አገዛዝ | ቂሮስና ተከታዮቹ (ወራሾቹ) |
| የግሪክ አገዛዝ | ትልቁ እስክንድርና አራቱ ተከታዮቹ |
| 3ኛው ራስ: ግሪክ፣ሶርያ ፣ባቢሎን | ሴሉከስና ወራሾቹ |
| 4ኛው ራስ: ግሪክ፣ግብፅ | በጥሊሞስና ወራሾቹ |
| 5ኛው ራስ: ግሪክ፣ትሬስና ትንሹ እስያ | ሊስማኩስና ወራሾቹ |
| 6ኛው ራስ: ግርክ፣ሜቄዶን | ካሳንደርና ወራሾቹ |
| 7ኛው ራስ: የሮም አገዛዝ | አውግስጦስና ወራሾቹ |


በገሃዱ ዓለም እነዚህ ሰባቱ ራሶች የአራቱ የጥንቱ መንግስታት አመጸኛ በሆኑት ሰባት መንግስታት ተመስለዋል:: ገሃድ ባልሆነው ዓለም ግን ከእነዚህ መንግስታት በስተኋላ ሆኖ የሚገዛውን ሰይጣንን ይወክላሉ:: ሆኖም አራቱ የዓለም መንግስታት ከመንግስቶቻቸው (ሰባት ራሶች) ጋር ጠፍተዋል:: ስለዚህ ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት ሰይጣናዊ ምሳሌ ሆነዋል::

### ምስሉ: ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ

በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን መግለጫ እንመልከት:: ሰባቱም ራሶች በመልክዓ ምድር አቀማመጥ የሚያገኙት በዓለም የእግዚአብሔር ዋና ከተማ በሆነችው በኢየሩሳሌም አጠገብ (አካባቢ) ነው:: በመግለጫው ላይ ያሉት ሰባቱ ጥቋቁር ነጠብጣብ የሰባቱ ሰይጣናዊ ራሶች የኃይላቸው እምብርት ናቸው:: ሰባቱ ዋና ከተማዎች በአራቱ የዓለም መንግሥታት ውስጥ የተመለከቱት ናቸው:: ሦስቱ በእስያ፣ ሦስቱ በአውሮፓና አንዷ በአፍሪካ ነው የሚገኙት::

በመጨረሻው ቀናት ይህ በትክክል በድጋሚ ይከናወናል፡፡ የጥንቱ አራቱ መንግስታት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በአጠቃላይ ተሣድሶ በማድረግ እንደሚገለጹ ሁሉ ሰባቱም ራሶች በ(ራዕ.13:1-2) እንደተገለጸው በድጋሚ ይታያሉ፡፡ እነዚህ ሰባት ራሶች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ተቀምጠው የሚገዙት ስውር የሆነው የሰይጣናዊ ኃይሳት ናቸው (ዳን.10:13፣20)፡፡ እነዚህ አጭር የሆኑት አስተያየቶች ሰይጣን ከራሱ ሌላ ምስል እንደማያመጣ ይገልጻሉ፡፡ እንዳለፈው የጥንቱ ዘመን ምስያ በመጨረሻው ቀናት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በተመሳሳይ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡

የአራቱ የዓለም መንግስታት በአንድ ጊዜ በድጋሚ የመታየቱ እውነት ዓለም ከዚህ በፊት ያላየችው የተጠናከረ ኃይል መታየቱን ያመለክታል፡፡ የሰው ዘር ከዚህ ከተጠናከረው ኃይል ውጤት ማንኛውም አስቸጋሪ የሆነውን ነገር የሚጋፈጥ ይሆናል፡፡ ያለፉት የአራቱ መንግስታት መሪዎች ድል ባደረጓቸው በአዋሳኝ ሀገሮች ላይ ስልጣናቸውን ተለማምደው ነበር፡፡ ሆኖም በቅርቡ አስፈሪ የሆነው መንግስት መካከለኛ (እምብርት) ቦታውን በጥንቱ መንግስታት ድንበሮች ላይ ይመሠርታል፡፡ ከዚህ ጠንካራ የሆነው ኃይላቸው በዓለም ሁሉ የሚሠራጭ ይሆናል፡፡ አንድ ሰው በማይገመት ሁኔታ በአመጸኝነቱ ሁሉን ከስሩ በማድረግ ይህን መንግስት ይመራል፡፡ ስለ መሪነቱ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ካሉት ሰዎች የአምላክነት ክብርና ሙገሳ ይሰጠዋል፡፡ ይህ ሰው ተራ ሰው ሳሆን አውሬ የሆነ፣ ጨካኝ ሰው ነው፡፡ አዲስ ኪዳን ይህን መሪ በሚገባቸው በአውሬ በመምሰል ይገልጸዋል፡፡ *(ራዕ.11:7፣13:1፣2፣12፣ 14፣15፣17፣18፣ 14:9፣11፣ 15:2፣ 16:13 17:3፣7፣8፣11፣13፣16፣17፣ 19:19-20፣ 20:10)*፡፡ ስለዚህ ያለው ገለጻ «የክርስቶስ ተቃዋሚ» የሚለው ለእኛ የተለመደ ገለጻ ነው፡፡ *(1ዮሐ.2:18፣ 22፣ 4:3፣ 2ዮሐ.7)*









**እነዚህ በእንግሊዘኛው 121 ላይ ያለው ካርታ ማንም ሳይሆን ሰይጣን ራሱ ነው ይህን መንግስትና የክርስቶስ ተቃዋሚውን ሰው የሚቆጣጠረው፡፡ ከሁለቱም ሰይጣናዊ ምሳሌውን እናገኛለን፡፡**

| ተምሳሌት | አምሳያና | ተመሳሳይነት |
|---|---|---|
| ሰይጣን | አራቱ የዓለም መንግሥታት | የፀረ ክርስቶስ መንግሥት |
| ራዕ.12:3-9 | ዳን.7:1-28 | ራዕ.13-19 |
| ሰይጣን በማይታየው ዓለም ውስጥ ሰባት ራሶችና አስር ቀንድ ባለው ዘንዶ በመመሰል ይታያል፡፡ እርሱ የኃጢአትና የክፋት ምንጭና መነሻ፣ ለዚህ ለወደቀ ዓለም በሚታየውና በማይታየው ላይ ገዢ ነው፡፡ | በብሉይ ኪዳን አራቱ የዓለም መንግስታት በሚስፈሩ አራዊት ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ባላቸው ተመስለዋል፡፡ የማይታየውን የሰይጣንን ተምሳሌት በሚታየው ዓለም ይፈጥራሉ፡፡<br>• ባቢሎን<br>• ሜዶንና፣ፋርስ<br>• ግሪክ<br>• ሮም | በአዲስ ኪዳን የፀረ ክርስቶስና መንግስቱ ከጥልቁ በሚወጣ አስፈሪ አውሬ በመመሰል ይታያል፡፡ ይህ አውሬ በሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ተመስሏል፡፡ የሰይጣን ተምሳሌነትና የዳን.7 መንግስታት በመምሰል ይታያል፡፡ |

በመጨረሻው ቀናት ይህ በትክክል በድጋሚ ይከናወናል:: የጥንቱ አራቱ መንግስታት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በአጠቃላይ ተሃድሶ በማድረግ እንደሚገለጹ ሁሉ ሰባቱም ራሶች *በ(ራዕ.13:1-2)* እንደተገለጸው በድጋሚ ይታያሉ:: እነዚህ ሰባት ራሶች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ተቀምጠው የሚገዙት ስውር የሆነው የሰይጣናዊ ኃይላት ናቸው *(ዳን.10:13፤20)*:: እነዚህ አጭር የሆኑት አስተያየቶች ሰይጣን ከራሱ ሌላ ምስል እንደማያመጣ ይገልጻሉ:: እንዳለፈው የጥንቱ ዘመን ምስያ በመጨረሻው ቀናት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በተመሳሳይ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ግልጽ ሆኖ ይታያል::

የአራቱ የዓለም መንግስታት በአንድ ጊዜ በድጋሚ የመታየቱ እውነት ዓለም ከዚህ በፊት ያላየችው የተጠናከረ ኃይል መታየቱን ያመለክታል:: የሰው ዘር ከዚህ ከተጠናከረው ኃይል ውጤት ማንኛውም አስቸጋሪ የሆነውን ነገር የሚጋፈጥ ይሆናል:: ያለፉት የአራቱ መንግስታት መሪዎች ድል ባደረጓቸው በአዋሳኝ ህገሮች ላይ ስልጣናቸውን ተለማምደው ነበር:: ሆኖም በቅርቡ አስፈሪ የሆነው መንግስት መካከለኛ (ኢምብርት) ቦታውን በጥንቱ መንግስታት ድንበሮች ላይ ይመሠርታል:: ከዚህ ጠንካራ የሆነው ኃይላቸው በዓለም ሁሉ የሚሠራጭ ይሆናል:: አንድ ሰው በማይገመት ሁኔታ በአመጸኝነቱ ሁሉን ከስሩ በማድረግ ይህን መንግስት ይመራል:: ስለ መሪነቱ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ካሉት ሰዎች የአምላክነት ክብርና ሙገሳ ይሰጠዋል:: ይህ ሰው ተራ ሰው ሳሆን አውሬ የሆነ፣ ጨካኝ ሰው ነው:: አዲስ ኪዳን ይህን መሪ በሚገዛቸው በአውሬ በመምሰል ይገልጸዋል:: *(ራዕ.11:7፣13:1፣2፣12፣ 14፣15፣17፣18፤ 14:9፣11፤ 15:2፣ 16:13 17:3፣7፣8፣11፣13፣16፣17፣ 19:19-20፣ 20:10)*:: ስለዚህ ያለው ገለጻ «የክርስቶስ ተቃዋሚ» የሚለው ለእኛ የተለመደ ገለጸ ነው:: *(1ዮሐ.2:18፤ 22፣ 4:3፣ 2ዮሐ.7)*








**እነዚህ በእንግሊዘኛው 121 ላይ ያለው ካርታ ማንም ሳይሆን ሰይጣን ራሱ ነው ይህን መንግስትና የክርስቶስ ተቃዋሚውን ሰው የሚቆጣጠረው:: ከሁሉቱም ሰይጣናዊ ምሳሌውን እናገኛለን::**

| ተምሳሌት | አምሳያና | ተመሳሳይነት |
|---|---|---|
| ሰይጣን | አራቱ የዓለም መንግሥታት | የፀረ ክርስቶስ መንግሥት |
| ራዕ.12:3-9 | ዳን.7:1-28 | ራዕ.13-19 |
| ሰይጣን በማይታየው ዓለም ውስጥ ሰባት ራሶችና አስር ቀንድ ባለው ዘንዶ በመመሰል ይታያል:: እርሱ የኃጢአትና የክፋት ምንጭና መነሻ፤ ለዚህ ለወደቀ ዓለም በሚታየውና በማይታየው ላይ ገዢ ነው:: | በብሉይ ኪዳን አራቱ የዓለም መንግስታት በሚስፈሩ አራዊት ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ባላቸው ተመስለዋል:: የማይታየውን የሰይጣንን ተምሳሌት በሚታየው ዓለም ይፈጥራሉ::<br>• ባቢሎን<br>• ሜዶንና፣ፋርስ<br>• ግሪክ<br>• ሮም | በአዲስ ኪዳን የፀረ ክርስቶስና መንግስቱ ከጥልቁ በሚወጣ አስፈሪ አውሬ በመመሰል ይታያል:: ይህ አውሬ በሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ተመስሏል:: የሰይጣን ተምሳሌነትና የዳን.7 መንግስታት በመምሰል ይታያል:: |

## ፀረ ክርስቶስ – የመጨረሻው የዓለም ገገር

የሚለው በግሪኩ ቋንቋ «አንቲ-ክሪስቱስ» ማለት ሲሆን «የክርስቶስ ምትክ (ተቃዋሚ) ማለት ነው:: አንቲ ማለት ምትክ /ተቃራኒ/ «ክርስቶስ» ማለት ደግሞ «የተቀባ» ማለት ነው:: በዕብራይስጡ ደግሞ «መሲሀ» የሚለው ቃል የተቀባ ማለት ነው:: መሲሁ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በእግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ የተቀባውና የእስራኤል ሕዝብ ንጉስ ነው(*ማቴ.3:16-17፤ ሉቃ.1:31-35*) በስይጣን የተቀባው ፀረ ክርስቶስ የሚያታልል በአመጽ የተሞላና ተቃዋሚው የእስራኤል ንጉሥ ይሆናል::

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የሰው ዘር እንደ ፀረ ክርስቶስ ዓለም ከአሁን በፊት ከቶ አይታው የማታውቀው መንግስት ይሆናል:: አንድ ቀን መላው ዓለም ከቁጥጥሩ ስር ይሆናል::

*«ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው:: በነገድና በወገን፣ በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው» (ራዕ.13:7)::*

በተመሳሳይ ሁኔታ ይህችን ዓለም ለመግዛት የመጨረሻው መሪ ይሆናል፤ ክርስቶስ በክብር በሚገለጥበት ጊዜ በእርሱ ላይ በመፍረድ ያጠፋዋል::

*«በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል» (2ተሰ.2:8)::*

## የፀረ ክርስቶስ ስሞች

ፀረ ክርስቶስ የሆነውን የአመፅ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የተለያዩ ስሞችን በመስጠት ይገልጸዋል:: በዮሐንስ መፅሐፍ አራት ጊዜ ብቻ « ፀረ ክርስቶስ» በመባል ተገልጿል (*1ዮሐ.2:18-22፤4:3፤2ዮሐ.7*):: በሌሎች ቦታዎች ደግሞ በሚከተሉት ሁኔታ ተገልጿል::

| | |
|---|---|
| «ኃጢያተኛ ሰው» | (2ተሰ.2:3) |
| የእግዚአብሔር «ተቃዋሚ» | (2ተሰ.2:4) |
| «አመጸኛ» | (2ተሰ.2:3-4) |
| «በስሙ የሚመጣ» | (ዮሐ.5:43) |
| «አውሬው» | (ራዕ.11:7፤13:1፤14:11፤17:8) |

እነዚህ መግለጫዎች መጽሐፍ ቅዱስ ፀረ ክርስቶስን ብቻ ለመግለጽ የተጠቀመባቸውና በተጨማሪም በመጨረሻው የዓለም መሪ ውስጥ ያለውን ሰይጣናዊ ባሕርይ የሚገልጹ ናቸው:: በዓለም ግን የታወቀ ስብአዊ መጠሪያ ስም ይኖረዋል::





## የፀረ ክርስቶስ ተፈጥሮ

እንደ ዓለም ገገር ፀረ ክርስቶስ ሰይጣናዊ የሆነ ሥጋ የለበሰ ሰው ነው:: ይህም ማለት ከዚህ በፊት በዓለም ላይ ከቶ ታይቶ የማይታወቅ ሥጋ ለበስ ሰይጣን ነው:: ካለፉት ነገስታት ወይም መሪዎች መካከል በኃይል በመግዛት ይህን መሪ የሚስተካከል አይኖርም:: ፀረ ክርስቶስ የሚነሳው ከሕዝብ መካከል ነው፣ የሚወለደውም ከሴት ነው:: እዚህ ሊገለጽ የሚያስፈልገው ነጥብ ቢኖር አባት ያለውና ከሰው ከፍ ባለ ሁኔታ የሚወለድ መሆኑ ነው:: ምክንያቱም ሰይጣን የእግዚአብሔርን ነገር ቅጅ የሚያደርግ ስለሆነ የክርስቶስን ከድንግል መወለድ ቅጅ ያደርጋል:: ማርቲን ሉተር «ሰይጣን እንደ ጦጣ የእግዚአብሔር ነገር ቅጂ የሚያደርግ ነው»: ብሎታል:: ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር አባቱ እግዚአብሔር የሆነና ምድራዊ አባት የሌለው፣ ከሰው በተለየ መንገድ የተወለደ ነው (*ማቴ.1:18-23፤ ሉቃ.1:31-35*) ዮሴፍ አሳዳጊው ሞግዚት አባቱ ነበር:: ሰይጣንም ፀረ ክርስቶስ ምድራዊ አባት የሌለው በማስመሰል ከተፈጥሮ በተለየ ሁኔታ በሰይጣናዊ መንገድ ከስጋ እንዲወለድ ያደርገዋል::

| መለኮታዊና ስላሴና ሰይጣናዊ ሦስትዮሽ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አቃጅ<br>እግዚአብሔር ለሰው ደህንነት አቀደ | እግዚ. አብሔር አብ | | ሰይጣን<br>አቃጅ | ፀረ እግዚአብሔር | ሰይጣን በሰው ውስጥ | የሰው ዘር በፖለቲካ ሕብረት ማድረግ |
| አስፈጻሚ<br>ጌታ ኢየሱስ መዋጀት ፈጸመ | እግዚ. አብሔር ወልድ | | ፀረ ክርስቶስ አስፈጻሚ ነው | ፀረ ወልድ | ሰይጣን በሥጋ | የሰው ዘር በኢኮኖሚ ሕብረት ማድረግ |
| ፈጻሚ<br>መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ደህንነትን ይፈጽማል:: | እግዚ. አብሔር መንፈስ ቅዱስ | | ሀሰተኛው ነቢይ ፈጻሚው ይሆናል | የመንፈስ ቅዱስ ተቃራኒ | ሰይጣን በመንፈስ | የሰው ዘር በሃይማኖት ሕብረት ማድረግ |

መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን እንደዚህ አይነት ነገር ሲደረግ እንደሚቻል አመልክቷል:: *በዘፍ.6:4* ከጥፋት ውሀ በፊት ቁመታቸው ረጃጅም የሆኑ (በእብራይስጡ ኔፍሊም) ተብለው የሚጠሩ እንደነበሩ እናነባለን:: እነዚህ ረጃጅም ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ልጆች ግንኙነት ውጤት ነበሩ:: በሌላ አነጋገር ሰዎች በአጋንንት የተያዙበትና መናፍስት ስጋ በመልበስ ከሴቶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግ የቻሉበት ጊዜ ነበረ ማለት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ተፈጥሮአዊ ባልሆነ መንገድ ውጤት የተገኙትን «ኔፍሊም» ብሎ

ይጠራቸዋል:: ይህም ማለት በህገወጥ የተረገዙ፣ በመጥፎ መንገድና ተፈጥሮአዊ ባልሆነ መንገድ የተወለዱ ማለት ነው:: እነዚህ ሰይጣናዊ ዝርያዎች በጥፋት ውሀ ጊዜ ጠፍተዋል:: በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ሞገስ ያገኙት የኖህ ቤተሰብ የሆኑት ስምንት ሰዎች ብቻ በመርከብ ተጠብቀው ዳኑ (*ዘፍ.6:8*)::

በሚሊዮን መስከ በአረማውያን ከተማዎች እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንደተከሰቱ ያስተምሩናል:: ወደ ቻይና ሔዶ የነበረው ትልቁ ሚስዮናዊ ህድሰን ቴይለር ሰለ ቀበሮ ምስል አማልክቶችና በእነዚህ ቀበሮ መሰል አጋንንታዊ መያዝ በቻይና ብዙ አስከፊ ስራ እንደሚሰራ ሪፖርት አድርጓል:: የቻይና ሴቶች የቀበሮ ራስ ባላቸው ፍጥረታት በመያዝ ሌሊት በሥጋቸው መከራ እንደሚቀበሉ ተናግሯል:: እነዚህ ሴቶች ግልጽ የሆነ ውሳኔ ወስነው ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኛ ቸው አድርገው ሲቀበሉ በራዕይ ይታዩ የነበሩት ይጠፉና ሴቶቹም ነጻ ይወጡ ነበር:: ለምሳሌ:- የግሪክ ጥንታዊ ታሪክ አማልክት ከሴቶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት በማድረግ ግማሽ አማልክት የሆኑ ወንዶች ልጆችን እንደወለዱ ይናገራል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ከመምጣቱ በፊት እንደ ኖህ ዘመን እንደሚሆን ሲናገር ይህን ነገር በድጋሚ እንደሚሆን ማመልከቱም ጭምር ነበር (*ማቴ.24:37-39*):: ዛሬም እንኳን ሴቶች እንዴት ከሰይጣንና ከመንፈሳዊ ሠራዊቱ ጋር እንደሚደነሱ የሚገልጹ አስፈሪ ፊልሞች እየተሠሩ ናቸው:: እነዚህ ፊልሞች ወንዶች ልጆች እንዴት ሰይጣናዊ ኃይል እንደሚኖራቸው ይገልጻሉ:: ፀረ-ክርስቶስ በሰይጣን አባትነት በሰይጣናዊ አሠራር ከተፈጥሮ አሰራር ውጪ በሆነ ርኩሰት ድርጊት የሚወሰድ ፍጡር ነው:: ግልጽ በሆነ ቃል «የሰይጣን ልጅ» ነው ማለት ነው:: ፀረ ክርስቶስ የሚገሰጥና በተቃራኒው የጌታ ኢየሱስን ቦታ በዓለም የሚይዝ ከሆነ ሰይጣናዊ ባህሪ ይኖረዋል ማለት ነው:: ምክንያቱም ቀደም ብለን እንደጠቀስነው በሥጋ የተገለጠ ሰይጣን ነውና:: በዚህም የሰው ዘር የሚታለል ይሆናል:: ጌታ ኢየሱስ ከሰማያዊ አባቱ ጋር ፍጹም የሆነ ሕብረት ያለውና ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆነ ነው (*ዮሐ.10:30*):: በተቃራኒው ደግሞ ፀረ ክርስቶስ ከሰይጣን ጋር ፍጹም የሆነ ሕብረት ያለውና ከእርሱም ጋር አንድ የሆነ ነው:: ቀጥሎ ያለው አጭር አስተዋፅዖ መለኮታዊ ስላሴን የሚቃረን ሰይጣናዊ ሶስትዮሽ መኖሩን የሚያሳይ ነው::





## የፀረ ክርስቶስ መነሻ

የክርስቲያኖች ተቃዋሚ መንግስት መሪ የሆነው ፀረ ክርስቶስ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ «ራሱን አምላክ» በማድረግ እንደሚቀመጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ቀደም ብሎ ጽፎላቸዋል (2ተሰ.2:4):: ይህ ዐረፍተ ነገር ፀረ ክርስቶስ መሠረቱ የት እንደሆነ ለማወቅ የሚጠየቀውን ጥያቄ ለማገናዘብ እጅግ አስፈላጊ ነው:: የጥንቱ የአራቱ የዓለም መንግስታት የባቢሎን፣ የሜዶንና ፋርስ፣ የግሪክና የሮም መንግስታት በመታደስ የሚነሳ መሆኑን ተመልክተናል:: በመታደሱ ቀድሞ የነበረው ብቻ ነው ተመልሶ የሚታደሰው:: ስለዚህ መጪው ፀረ ክርስቶስ መንግስት በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ ራሱን አምላክ አድርጎ በማስቀመጥ አምልኮን የሚጠይቅ ከሆነ ከቀደሙት (ከጥንት) አራት የዓለም መንግስታት መካከል አንድ መሪ በተመሳሳይ ይህን ያደረገ መኖር አለበት::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል አስፈላጊ የሆነ ጥቆማ ይሰጠናል:: እርሱም ከብዙ ምዕተ ዓመታት በፊት በነቢዩ ዳንኤል «የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ...» የተባለውን ትንቢት በመጥቀስ ተናግሯል (*ማቴ.24:15*):: በተመሳሳይም ንባብ በብሉይ ኪዳን ትንቢት ውስጥ ፍርሃተ እግዚአብሔር ፀባይ በሌለው ሰው መምጣት በጣም ከፍ ያለ ውድመት በተቀደሰው ስፍራ ላይ እንደሚያስከትል ይናገራል (*ዳን.9:27፤ 11:31*):: «የተቀደሰችው ስፍራና» «መቅደስ» በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል:: ይህም በብሉይ ኪዳን ዘመን በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ ያፈረሰ መሪ ነበር ወይ? ወደሚለው ጥያቄ ያመጣናል ይህ ከሆነ ትንሽ ግልጽ የሆነ መረጃ አግኝተናል ማለት ነው:: ምክንያቱም ፀረ ክርስቶስ በተመሳሳይ መንገድ ይህን ያከናውናል:: በርግጥ የጥንቱ የዓለም መንግስታት አልፈዋል:: ሆኖም ለሰባቱ ራሶች ስውር የሆነውን ሰይጣናዊ አመራር የሰጣቸው ዛሬም ከበስተኋላ (ከበስተጀርባ) አለ ማለት ነው:: ይህ ሰይጣናዊ አገዛዝ (መንግስት) በክርስቶስ ተቃዋሚ መንግሥት እንደገና በዓለም መድረክ ላይ አንድ ጊዜ ይታያል:: በአራቱ የጥንቱ የዓለም መንግሥታት ዘመን ወደገዙት ነገሥታትና ወራሾቻቸው ትኩረት ሰጥተን ስንመለከት የሚከተሉትን ግንዛቤዎች እናገኛለን:: የመጀመሪያው ራስ ባቢሎን ይህን አይወክልም ምክንያቱም ባቢሎናውያን በ586 ከ.ክ.ል.በ. ቤተ መቅደሱን አፈረሱት እንጂ አንድም የባቢሎን ንጉሥ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አልተቀመጡም፣ ሁለተኛው ራስ ደግሞ ሜዶንና ፋርስ ይህን አይወክልም

ምክንያቱም ሜዶንና ፋርስ ቤተ መቅደሱ ተመልሶ እንዲሠራ ፈቀዱ እንጂ አንድም ንጉሥ ከእነርሱ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አልተቀመጠምና አራተኛ ራስ በጳጥሊሞሳውያን የተመራው ግብጽና አምስተኛ በትሬስና በትንሹ እስያ የገዛው ሊስማከስ ቤተ መቅደሱን ከቶ አልነኩም። በካሳንደርና በወራሾቹ የተመራው ስድስተኛ ራስ ሜቄዶንያ ከቤተ መቅደሱ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረውም። ሰባተኛው ራስ የዓለም መንግሥት የሆነው ሮም ማንም ማርሻል ወይም ንጉሥ ወደ ቤተ መቅደሱ ሳይገባ ነሐሴ 10 ቀን 70 ዓ.ም. ከክ.ል.በኋላ ቤተ መቅደሱን በጠቅላላው እጠፋው። በ63 ክ.ል.በፊት ኢየሩሳሌምን ድል ያደረገው የሮሙ ንጉሥ ፓምፔ ብቻ ነበር ወደ ቤተ መቅደሱ የገባው። ሆኖም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያሉትን ነገሮች አልነካም ነበር ይህ ቤተ መቅደስ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ነበር። በ70 ዓ.ም. ሮማያውያን የደመሰሱት ቤተ መቅደስ ሄሮድስ መንግሥቱን በገነባበት ዘመን (40-4 ከክ.ል.በፊት) የተሠራው ሦስተኛው ቤተ መቅደስ ነበር። ስለዚህም ነው (በዮሐ.2:20) ላይ ያለው ቤተ መቅደሱ በአርባ ስድስት አመት መሠራቱን የሚናገረው። የሮም መንግሥት መሪ ከሆኑት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ራሱን ያስቀመጠ እልነበረም።

*ታዲያ የሚቀረው የትኛው ራስ ነው ?*

ሦስተኛው ራስ አስፈሪ በሆነው በአራተኛው ንጉስ በአንቲዎኮስ ኢፒፋነስ የሚመራው ሶርያ ብቻ ይቀራል። በ168-165 ከክ.ል.በፊት በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ እንደ ዚውስ ልጅ (የግሪክ ጣዖት) አምላክ በመባል ተመልኳል። በእግዚአብሔር ቤት መሰዊያ ላይ አሳማ ሰውቷል። የአስራኤልንም ሕዝብ ሰማጥፋት ሞክሯል። ፀረ ክርስቶስም የሚሠራው እንደዚሁ ነው። እንደ ሶሪያዊው የሚታይ ሰይጣናዊ ራስ ይነሳል። በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ራሱን ያስቀምጥና የጥፋት ርኩሰቱን ይመሠርታል።

*ፀረ ክርስቶስ የሚነሳው ከእስራኤል ሕዝብ ወይስ ከዓለም ሕዝብ ነው ?*

ፀረ ክርስቶስ ከየት ይመጣል ለሚለው ጥያቄ ራሱ ሌላ ሁለተኛ ጥያቄ ይወልዳል። ይህንንም እኛ ማጣራት አለብን። ጌታ ኢየሱስ በዘመኑ ለነበሩት አይሁዶች እንዲህ ብሎ ነበር።

*«እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፣ አልተቀበላችሁኝም፣ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ» በማለት ተናግሯቸዋል (ዮሐ.5:43)።*





እነዚህ ቃሎች አይሁዶች ከእውነተኛው መሲህ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ ፀረ ክርስቶስ የሆነውን ሀሰተኛውን ክርስቶስ መሲህ አድርገው እንደሚቀበሉት ግልጽ ያደረጉታል። በአራተኛው ምዕተ ዓመት ላይ ይኖሩ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች እነ ኢራኑስ፣ ሂፓላይት፣ አምብሩስ ፀረ ክርስቶስ ከእስራኤል ሕዝብ መካከል የሚነሳ ሰው እንደሆነ የሚጠቁመውን ሀሳብ ይደግፉ ነበር። አይሁዶች ከእነርሱ ሕዝብ ውጭ የሚመጣውን መሲህ አድርገው እንደማይቀበሉት ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው። ሰእነርሱ ብሉይ ኪዳን ከፍተኛ ስልጣን ያለው ነውና። ተስፋ የተገባው መሲህ:-

1. *የንግሥና ነገድ ካለው ከይሁዳ ነገድ እንደሚመጣ (ዘፍ.49:8-12)።*
2. *መንግሥቱ ትልቅ እንደሚሆንና በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥና ሰሰላሙና ለመንግሥቱ ፍጻሜ እደሌሰው ይናገራል (ኢሳ.9:7)።*

በመጽሐፍት ትርጉም የአይሁድ ሕዝብ እንደ ንጉሳቸው አድርገው የሚቀበሉት አንድን መሲህ ብቻ ነው። ይህ መሲህ ከእስራኤል ከይሁዳ ነገድ የሚመጣው «የዳዊት ልጅ ነው» ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መሲሁና ንጉሳቸው አድርገው ስላልተገነዘቡና ስላልተቀበሉት በፀረ ክርስቶስ እጅ ይወድቃሉ። ምክንያቱም መሲሁ በሥጋ ይገሰጣል ብለው እስከ አሁን ድረስ እየጠበቁ ስላሉ ነው። የአዲስ ኪዳን አማኞች እንደ መሆናችን መጠን የንጉስ ልጅ የሆነችው ማርያም የእግዚአብሔርን ልጅ እንደወለደችና እርሱም እንደገና በሥጋ እንደማይመጣ እናውቃለን። ስለዚህ ምክንያት ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቶስን በሥጋ የምናውቀው አይደለንም ብሎ የጻፈላቸው። (*2ቆሮ.5:16*)። መሲሁ በሥጋ ይገሰጣል ብለው ስለሚጠብቁት በዚህ ምክንያት የአይሁድ ሕዝቦች በክርስቶስ ተቃዋሚ ይታለላሉ።

ፀረ ክርስቶስ የዚህ ዓለም ሕዝቦች ታላቅ መሪ ይሆናል። በሌላው ጎን ደግሞ በአይሁዶች ሰመከበር በደም ሀረግ አይሁዳዊ መሆን አለበት። ከዓለም ታሪክ ልምምድ እንደታየው ይህ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አልበርት አንስታይን፣ ካርል ማርክስ፣ ዋልተር ራዜናው ወይም ሄነሪ ኪሲንጀር (የዓለም መሪዎች የነበሩት) በደም አይሁዳዊ ነበሩ። ታሪኩ አሳዛኝ የሆነው የእስራኤል ትልቁ ሰላይ ኤሊ ኮሄን ጥሩ ምሳሌ ነው። ኮሄን ሳይታወቅ በሶርያ እያለ ሰብዙ ዓመታት የእስራኤል ስውር አገልጋይ ነበር። ይህ ሰው ለሶርያ ፕሬዚደንት ቢሮ የቀረበና ከፍተኛ ስፍራ የተሰጠው ግለሰብ ነበር። እንድ ቀን በስለላ ላይ እንዳለ እጅ ከፍንጅ ተይዞ ያለ ምህረት በደማስቆ ከተማ በግንቦት ወር 1965 ዓ.ም. ተሰቀለ። በደም አይሁዳዊ ሆኖ ሳለ በመንግስት ሥራ

ከፍተኛ ስፍራ የመያዙ ነገር ችግር አይፈጥርም:: ተራ ለሆኑ ሰዎች ይህ የተቻለ ከሆነ ለፀረ ክርስቶስማ እንዴት አይቻልም?

## የፀረ ክርስቶስ አገዛዝ ጊዜ

ፀረ ክርስቶስ ሲነሳ «... ከዓለም መጀመሪያ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ ከእንግዲህም ከቶ የማይሆን» ጊዜ ይሆናል:: *(ማቴ.24.21)* አዳኛችን «እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር» ብሏል:: *(ማቴ.24:22)* ይህ ጊዜ ዓለም በዘመናት ሁሉ አይታ የማታውቀው አስጨናቂ ጊዜ ይሆናል:: ይህ ጊዜ ፍትህ የሚጠፋበትና አመጽ (ክፋት) እየበዛ የሚታይበት ጊዜ ነው*(ማቴ.24:12)*:: በማይገመት ሁኔታ አመጽ እየበዛ ይሔዳል:: ወደ ፊት እንደምንመለከተው እግዚአብሔር የማይታሰፍ ውስን ጊዜ እንዳደረገ እንመለከታለን:: ያለ መከልከል «ለሁሉም ዘመን አለው» (መክ. 3:1) ለማለት ይቻላል:: እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ አስቸጋሪ ጊዜያትን በእጁ ውስጥ በማድረግ ለመቆጣጠር የሚችል መሆኑ ግልጽ ነው:: እግዚአብሔር በዓለም ሁኔታዎች ጣልቃ በመግባትና በመምራት የመዋጀትን እቅድና ታሪክ እንዲቀጥል ያደርጋል:: የፀረ ክርስቶስ አገዛዝ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሰ ለሚከተለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንችላለን::

*ፀረ ክርስቶስ በምድር ላይ የሚገዛው ለምን ያህል ጊዜ ነው?*

ቀደም ብሎ ብዙ ጊዜ እንደተጠቀሰው ፀረ ክርስቶስ በጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ የተመሰለ ሰይጣናዊ ቅጅ ነው:: ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት መሲሁ አዳኛችን የመዋጀትን ሥራ ለመፈጸም የፈጀበትን ጊዜያት ያህል የፀረ ክርስቶስም አጥፊ የሆነውን ሥራውን በምድር ላይ ለመሥራት ተመሳሳይ ጊዜ ይወስድበታል::

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል እንደገለጸው በግምት ከ3 እስከ 3 ተኩል ዓመታት አገልግሎቱን በአደባባይ እንደሰጠ ለማየት ይቻላል:: ሥራውን በግልጽ ከጀመረበት እስከ መስቀል ሞቱ ድረስ ሶስት የፋሲካ በዓላትን (ሦስት ዓመታት) በኢየሩሳሌም አክብሯል *(ዮሐ.2:13፤ 6:4፤ 12:1)*:: ፋሲካ በዓመት አንድ ጊዜ የሚመጣና ጌታ በመጀመሪያው ፋሲካ ከመታየቱ በፊት ጥቂት ጊዜያት ቀደም ያለ ሲሆን፣ ከዚህ በመነሳት በህዝቡ መካከል ከሦስት ዓመታት በላይ እንዳገለገለ ግልጽ ይሆናል:: እንዲሁም ፀረ ክርስቶስ የክርስቶስ ኢየሱስን ቅጂ በማድረግ ለሦስት ዓመታት ተኩል የማታለል ሥራውን ያከናውናል::

እግዚአብሔር ሁልጊዜ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚዋጅ አድርጎ የሚናገር ከሆነ፣ እስራኤል በመጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ዓይን





የሚጣልባት ከተማ ናት ማለት ነው:: እግዚአብሔር ታማኝ ለሆነው አገልጋዩ በእስራኤል ላይ የተወሰነውን የፍርድና የጸጋን ጊዜ በግልጽ በማሳየት:-

«አመፃን ለማስቆም ኃጢአትን ለማስወገድ በደልን ለማስተሰረይ ዘላለማዊ ጽድቅን ለማምጣት ራዕይና ትንቢትን ለማተምና እጅግ ቅዱስ የሆነውን ለመቀባት ስለ ህዝብህና ስለተቀደሰችው ከተማህ ሰባ ሱባዔ ታውጆአል:: *(ዳን. 9:24)*::

እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የሰባው የባቢሎን ምርኮ ዘመን ፍርድን ብቻ የወሰነ ሳይሆን ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ:: (ዳንኤል ይህን ራዕይ በተቀበለበት ጊዜ ይኖር የነበረው በዚህ ጊዜ ውስጥ ነበር) ይህ ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ሳምንት ሰባት ቀናት እንዳሉት ሁሉ ሰባት የሚለው ሰባት ዓመታትን የያዘ ነው:: የእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን እንዲሰልሉ ሰላዮችን ለአርባ ቀናት ልከው ነበር:: በዚህም ለአርባ ዓመታት ወደ ተስፋይቱ ምድር ሳይገቡ በምድረ በዳ ቆይተዋል:: በዚህም በእስራኤል ላይ የሰባ ዓመት ፍርድ ብቻ የተወሰደ ሳይሆን ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ፣ ይህም ማለት እነዚህ ሰባቱ ሳምንታት በጠቅላላው የሰባት ዓመታት ጊዜያት ይሆናሉ ማለት ነው::

በማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ ሰባ ጊዜ ሰባትን የሚያመለክተው መስመር ከአራቱ የዓለም መንግስታት ስር ይታያል:: በመዋጀት ታሪክ ሂደት ውስጥ እነዚህን «ሰባቶች» የሚገልጸው (በዳንኤል ምዕ. 9: 25-26)

*«ይህን ልብ ብለህ አስተውል፣ ኢየሩሳሌም እንድትታደስ ትዕዛዝ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ መሲሁ እስከሚመጣበት ድረስ ሰባት ሳምንትና ስልሳ ሁለት ሳምንት ናቸው» በሚል ተገልጿል::*

የኢየሩሳሌም ቅጥር ተመልሶ መሠራት የጀመረው በፋርሱ ንጉሥ በአርጤክስስ ከ20ኛው ዓመት ላይ ነበር *(ነህ.1:1፤2:1)*:: የጥንቱ ታሪክ ግኝት እንደሚነግረን ይህ ጊዜ ከ445 ወይም ከ451 ከክ.ል.በፊት እንደሆነ ነው ትንቢቱ ቆጠራውን የሚያደርገው:: በእነዚህ ታሪካዊ ቀናት ላይ ተመስርቶ ነው (ዳን. 9:24-27)::

**7 ሰባቶች ( ሳምንቶች ) :- 7 × 7 = 49 ዓመታት**

**<u>62 ሰባቶች ( ሳምንቶች ) :- 62 × 7 = 434 ዓመታት</u>**


**ጠቅላላ ድምር = 483 ዓመታት**

ኢየሩሳሌም ተመልሶ መሠራት ትዕዛዙ የተሰጠበት 451 ከክ.ል.በፊት ነው ብለን ከተቀበልንና በዚህ ላይ 483 ዓመታትን ብንደምር ይህ ቆጠራ በቀጥታ ወደ 32 ከክ.ል.በኋላ ዓመት ያመጣናል:: በ 0 ላይ አንድ ዓመት መጨመር አለብን:: ይህም ወደ 33 ከክ.ል.በኋላ ዓመት ይወስደናል:: ዳንኤል ስለዚህ:-

*«ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሲሕ ይገደላል፣ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም»* በማለት ተናግሯል (*ዳን.9:26*)::

ይህ መሲህ ወይም «የተቀባው» ሰብዙ ጊዜ ይጠበቅ የነበረው ከእስራኤሉ መሲህ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አልነበረም:: እርሱ በመጣ ጊዜ ግን የራሱ ሕዝቦች አልተቀበሉትም ነበር (*ዮሐ.1:10-11*) በተቃራኒው ግን ሰቀሉት (*ዳን.9:26*)::

የመጀመሪያዎቹ ስድሳ ዘጠኙ ሳምንታት (ሰባቶች) በመሲሁ መምጣት ጊዜ ተፈጽመዋል:: ሰባኛው ሱባኤ (ሳምንት) ግን ሳይፈፀም ቀርቷል:: ይህ ሰባኛው ሰባት ገና አልተጀመረም:: ምክንያቱም እስራኤል መሲኋን ስላልተቀበለች እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የነበረውን የማዳን ሥራ ጣልቃ በመግባት ሰጊዜው ስላቆመ ነው:: ባሰፈው ምዕራፍ እንዳየነው አግዚአብሔር በወንጌል ሥራው ትኩረቱን ወደ አሕዛብ አደረገ:: አይሁዶች በጌታ እስከ ተወሰነላቸው ጊዜና ተመልሰው የእስራኤል ሕዝብ ሆነው እስከሚሰበሰቡበት ጊዜ ድረስ ከአባቶቻቸው ምድር ወጥተው በአሕዛብ መካከል እንዲበታተኑ ተደርጓል (*ሉቃ.21:24*)፡ እስከዚያ ድረስ ቅድስቲቷ ምድር የተፈታች ሆና ትቆያለች:: (ዳን. 9:26፣ ማቴ. 23:38) ሰብዙ ምዕተ ዓመታት በእስራኤል ምድር ላይ የውጭ ሕዝቦች ገዙ፣ አሰቃቂም ውጊያዎችን ተዋጉባት ምድሪቱንም አጠፏት:: በእነዚህ ጊዜያት በዓለም ዚሪያ ብዙ አይሁዶች አሰቃቂ ስደቶችን ተቀበሉ:: በመጨረሻዎቹ ቀናት እግዚአብሔር ትኩረቱን እንደ ገና ወደ ራሱ ሕዝብ ይመልሳል:: ሰብዙ አሰርት ዓመታት አይሁዶች ወደ አባቶቻቸው ምድር እየተመለሱ ናቸው:: ይህ ተአምራት በመላው ዓለም ዓይን ፊት እየተከናወነ ነው:: ዋናው ነገር፣ የእስራኤል ከፉ ጠላቶች እንኳን ቢሆኑ ይህን መሰባሰባቸውን ሊያቆሙ አለመቻላቸው ነው:: ከዚህ በስተጀርባ ያሰውን የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው:: እስራኤል እንደገና ወደ ፊት ወደ ትንቢቱ ፍፃሜ እየተጠጋች ነው:: ምክንያቱም መሲሁ ሊመጣ ስለሆነ ነው::









ወንጌል ለሁለት ሺህ ዓመታት በመላ አለም ተሰብኳል:: በቁጥር ያልተወሰኑ ሰዎችም በጌታ ኢየሱስ ላይ ወዳለው እውነተኛና ሕያው እምነት መጥተዋል:: ዛሬም ጌታ የዳኑትን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እየሰበሰበና በየቀኑም በእነርሱ ላይ እየጨመረ ነው:: (*ሐሥ.2:47*) «የአሕዛብ ሙላት» (*ሮሜ.11:25*) ሲሞላና ቤተ ክርስቲያን በክብር በተነጠቀች ጊዜ በቀጥታ ጌታ ከእስራኤል ጋር ያሰውን የመዋጀት ታሪክ ይቀጥላል:: በዚያን ጊዜ *የ(ዳን.9:24)* ትንቢት ይፈጸምና የመጨረሻው «ሱባኤ» ይቀጥላል::

በእስራኤል ላይ ሰባ ጊዜ ሰባት ወይም 490 ዓመታት እንደተቀጠረ እናስታውስ:: ስድሳ ዘጠኙ ሰባቶች (ሳምንታት) ወይም 483 ዓመታት ተፈጽመዋል:: ሰባቱ ዓመታት ወይም አንዱ ሳምንት ብቻ ቀርቷል:: ይህ የዳንኤል ሰባኛውና የመጨረሻው ሰባት የሆነው ሱባዔ ጌታ «በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና» ሆኖ ከመምጣቱ በፊት ይፈጸማል (ማቴ.24:30):: አምላክ የለሹም (አመጸኛው) የእስራኤል ሕዝብ ወደዚህ የፍርድ ጊዜ እየደረሰ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት አልተቀበሉትም (ተቃውመውታል) (1ኛዮሐ. 5:10) ስለዚህም የሰይጣን ልጅ በሆነው በክርስቶስ ተቃዋሚ እጅ ይወድቃሉ::

ይህ የአመጽ ሰው (*2ተሰ.2:3*) ከእስራኤል ጋር የተሰየ ሕብረት ይመሠርታል:: ከዚህ ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን ለመመስረት ይታገላል፣ እስራኤልም በቃል ኪዳኑ ትያዛለች:: ምክንያቱም በመሳሳት ንጉሳቸውና መሲሁ አድርገው ስለሚቀበሉት ነው::

በብሉይ ኪዳን ዘመናት እስራኤል ከእዳዲስ ከሚነግሱት ነገሥታት ጋር ቃል ኪዳን ታደርግ ነበር:: ከዳዊት ጋር (*2ሳሙ.2:4፣5:3)፣* ከሰሎሞን ጋር *(1ነገ.1:32-40)፣* ከሮብአም ጋር *(1ነገ.12:1)፣* ከኢዩ ጋር *(2ነገ.9:1-13)፣* ከኢዩኤል



*ጋር(2ነገ.11:4፣ 12፣17)* ቃል ኪዳን እንዳደረጉ ተጽፏል:: አንድ ጊዜ እስራኤል «በራሱ ስም የሚመጣውን» (ዮሐ. 5:43) ስትቀበል ይህ ድርጊት እንደገና በድጋሚ ይከናወናል:: የዳንኤል የመጨረሻው ሰባት ዓመት በዚህ እጥፉ የሆነው ቃልኪዳን በእስራኤልና በሐሰተኛው ንጉስ መካከል ይጀምራል:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ቃል ኪዳን ከሀሰተኛው ንጉስ ከፀረ ክርስቶስ ጋር በማያያዝ:-

*«እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃልኪዳን ለአንድ ሱባኤ (ሰባት አመታት) ያደርጋል» (ዳን.9:27)* ይላል::

በዳንኤል 9:24-27 ያለው ጠቅላላ ትንቢት እንደሚያሳየው ይህ አንዱ ሳምንት ያለ ጥርጥር ያልተፈጸመው ሳምንት ነው:: በሰባትና በስድሳ ሁለት ሳይ ሰባት ሲደመርበት ሰባው ሳምንት (ሰባው ሱባኤ) ይሆናል:: በኋላ እንደምናየው ፀረ ክርስቶስ በዚህ በሰባኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ ፍርድ ይከናወንበታል::

ፀረ ክርስቶስ ምን ያህል ጊዜ እንደሚገዛ ይህ ግልጽ ያደርገዋል:: በጠቅላላው ለሰባት ዓመት ይገዛል:: ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያለው የሰባት ዓመት የቃል ኪዳን ቆይታ ጊዜ ጋር እኩል ይሆናል:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የሚገዛበት ጊዜ በሁለት የ3 ዓመት ተኩል ዓመታት ይከፈላል::

### የመጀመሪያዎቹ የ$3^{1/2}$ ዓመታት «ሰላም ሰላም ሰላም»

በእነዚህ በመጀመሪዎቹ ሶስት ተኩል ዓመታት አገዛዙ ጊዜ ፀረ ክርስቶስ የሰውን ዘር በሰላምና በብልጽግና ይባርካል:: በአስቸጋሪው ጊዜ እንደ ተጠበቀው መሲህ፣ ከሰው አዕምሮ አስቸጋሪ የሆኑትን ነገሮችን ሊፈታ የሚችል መስሎ ይገለጣል:: በተሰያዩ መስኮች በማህበራዊና በኢኮኖሚ መስክ ሊታመን በማይቻል መልኩ በሚያደርገው እድገት የተነሳ መላ አለም በእርሱ ይደነቅና ያከብረዋል::

አይሁዶች ፀረ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር በሚያደርገው ቃል ኪዳን በኢየሩሳሌም አዲስ በተሠራው ቤተ መቅደሱ የብሉይ ኪዳን መስዋዕት እንደሚሰዋ ያረጋግጥላቸዋል:: ያለ ጥርጥር በዚህ ጊዜ ከሚታዩት ምክንያቶች አንዱ ሕዝቦች «ሰላምና ደህንነት» ነው ማለታቸው ነው (*1ተሰ.5:3*)::

ዛሬም እንኳን «ሰላምና ደህንነት» ነው የሚለው በዓለም ፖለቲካ ዋናው የመወያያ ጉዳይ ነው:: የታወቀው መግለጫ «ሰላም እናድርግ» የሚለው ነው:: ከዚህ ጋር ጎን ለጎን የሚመሳሰለው የአይሁዶች ትምህርት መሲሁ ከመምጣቱና ይህን ሰላም ከመመስረቱ በፊት የሰው ዘር በመጀመሪያ ወደ ሰላም መድረስ አለበት የሚል ነው:: እዚህ ላይ የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ ስለ ሰላም ያለውን መፈክር ልንገነዘብ እንችላለን::





ፀረ ክርስቶስ በዚህ ብሩህ በሆነ የሰላም መልእክት ዓለምን ያስደንቃል:: በዚህም የዚህ ችግር መፍትሔ እንደተገኘለት መስሎ ይታያል:: ሆኖም አጭሩ «የሰላም» ጊዜና ውጫዊ የሆነው ብልጽግናና ጠቅላላው ደህንነት አደገኛ ሕልሞች ብቻ ናቸው::ሰዎችን እስራኤልንና መላ አለምን የሚያታልል (የሚያስት) ሆኖ ይቀራል:: ፍጹም የሆነውን ሰላም ያለ እግዚአብሔር ለማግኘት መጣሩ ፍጹም የማይቻልና ሕልም ብቻ ነው:: በተለይም በአመጸኛውና (*2ተሰ.2:8*) እግዚአብሔርን በሚቃወመው ግዛት (*2ተሰ.2:4*) እኛ ወደዚህ የመታለል ዘመን እየተጠጋን ያለን ሐዋርያው ጳውሎስ ለሰጠው ማስጠንቀቂያ ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጠው ይገባናል:: ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በጻፈው በመጀመሪያ መልእክቱ ሐዋርያው ጳውሎስ በሚመጣው በፀረ ክርስቶስ መንግስት ስላለው ሀሰተኛ ስለሆነው አጭር ሰላም በትንቢት እይታው:-

*«ሰላምና ደህንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል»* በማለት ጽፎላቸዋል (1ተሰ.5:3)::

በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳን ነብዩ ኤርምያስ የእስራኤል ልጆች *«ሰላም ሳይሆን:- ሰላም ሰላም ይላሉ»* ስለሚለው ስለ ሀሰት አላማቸውና አካሄዳቸው ጩኸት ዘልፏቸዋል (ኤር.6:14) ::

### የመጨረሻዎቹ የ$3^{1/2}$ ዓመታት፣ ታላቁ መከራ


የሰባተኛው ሳምንት አጋማሽ ከተፈጸመ በኋላ በፀረ ክርስቶስ መንግስት በአይሁድ ላይ አሉታዊ ለውጥ ያሳያል:: በነቢዩ ዳንኤል:-

*«በሱባኤውም እኩሌታ መሰዋዕትንና ቁርባንን ያስቀራል» (ዳን.9:27)* ተብሏልና::

ይህም ማለት ከ3-1/2 ዓመታት በኋላ ፀረ ክርስቶስ ከእስራኤል ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን በድንገት ያፈርስና ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የብሉይ ኪዳን መስዋዕትንና ቁርባንን ያስቀራል:: በዚህ ምትክ ራሱን አምላክ አድርጎ በማወጅ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ራሱን ያስቀምጣል (*2ተሰ.2:4*): በመጀመሪያ ራሳቸውን በአማልክት ደረጃ ያስቀመጡት የሮማውያን ነገሥታት ነበሩ:: የፀረ ክርስቶስ ከዚህ በበለጠ ራሱን አምላክ በማድረግ ይሠራል:: ከዚህም ትዕቢቱ የተነሳ አምላካዊ አክብሮትን ከሕዝብ ይጠይቃል:: ይህን ጥያቄውን በሰዎች ላይ እንዴት በኃይል እንደሚያከናውን ያውቃል (*ራዕ.* 13:15):: ሆኖም አይሁዶች ለጥያቄው ድጋፍ ባለመስጠት ሀሳቡን ይቃወሙታል:: ይህም የሚሆነው በአንድ አምላክ ላይ ካላቸው እምነት የተነሳ ለሰው መስገድ የማይቻላቸው ስለሆነ ነው:: በዚህም ምክንያት ማንንም ሰው፣ ፀረ ክርስቶስን እንኳን ቢሆን አያመልኩም:: በዚህ ምትክ እግዚአብሔርን ብቻ ያመልኩታል::

እይሁዶች ጥያቄውን በመቃወምና ባለመታዘዛቸው ምክንያት ፀረ ክርስቶስ በመጨረሻ ትክክለኛ ባሕርዩን ይገልጣል። በዓለም ታሪክ ታይቶ የማይታወቀውን ስደት በእይሁዶች ላይ ያካሄዳል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ስለዚህ ጊዜ «ታላቁ መከራ» እንደ ሆነና ከዚያ በፊት በዓለም ያልታየና ወደፊትም ደግሞ የማይታይ እንደሆነ ተናግሯል (ማቴ. 24:21)። በተመሳሳይ ሁኔታ በብሉይና በአዲስ ኪዳን «የያዕቆብ የመከራ ዘመን» (*ኤር.30:7*) ወይም ደግሞ «ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ፡- እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል።» *(ዳን.12:1)* በማለት ተተንብዮአል።

በአሁኑ ዘመን ባለው ስነ መለኮታዊ መግለጫ «ታላቁ መከራ» በማለት ይጠቀማል። ሆኖም በከፍተኛ ደረጃ ልንገነዘበው የሚያስፈልገው እውነት «ታላቁ መከራ» የሚመለከተው የእስራኤልን ምድርና ሕዝብ ነው። ይህ ግልጽ ሊሆን የሚችለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ የተናገረውን በጥንቃቄ ስናጠና ነው። እርሱም ያለው :-








1. «በተቀደሰችው ስፍር» (ማለትም በኢየሩሳሌም ያለው ቤተ መቅደስ) ቁ.15
2. «ከይሁዳ መሬት» ቁ.16
3. «በሰገነት ላይ» ስላሉ ሰዎች (በአብዛኛው የእስራኤላውያን ቤቶች ዝርግ የሆነ ጣራ አላቸው) ቁ.17
4. «ሽሽታችሁ በሰንበት እንዳይሆን» ቁ.20 (እስራኤላውያን ብቻ ናቸው ሰንበት የሚጠብቁት)
5. «ሽሽታችሁ በክረምት እንዳይሆን» ቁ.20 (እስራኤላውያን 300 ያህል ፀሐያማና ሞቃት ቀናት አሏቸው።)

ኢየሱስ በግልጽ ስለ እስራኤል ወይም በይሁዳ ስለሚኖሩት አይሁዳውያን ነበር የተናገረው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለተጠቀሰውና አስቃቂ ስለሆነው መከራ ስናስብ «የያዕቆብ የመከራ ዘመን» የሚለው በእስራኤል ላይ የሚደርስ ፍርድ እንደሆነ እንገነዘባለን። በሚከተሉት የንባብ ክፍሎች *(ዳን. 7:25፤12:7፤ራዕ.11:2-3፤ 12.6-14፤ 13:5)* ውስጥ «1260 ቀናት»፣ «42 ወራት»፣ «ዘመን ዘመናትና የዘመን እኩሌታ» በማለት ይናገራሉ። እያንዳንዱ ጊዜያት 3-1/2 ዓመታት ወይም የሶስት ሳምንትና ተኩል ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ጊዜያት *በ ዳን.9:27* የተጠቀሰውን የሰባኛውን ሳምንት እኩሌታ እንደሆነ ያመለክታሉ። ምክንያቱም ታላቁ መከራ የሚሆነው በእነዚህ 3-1/2 ዓመታት ጊዜ ነው። ይህም እስራኤል በእግዚአብሔር ፍርድ ስር የምትቆይበት ጊዜ ነው። ሰባው ሱባኤ የዳንኤልን ሕዝብ የሚመለከት ከሆነና (*ዳን.9:24*) በሕዝብህ ላይ ስለሚል የዳንኤል ሕዝብ የእስራኤል ሕዝብ ከሆነ አስቃቂ የሆነው ታላቁ መከራ እስራኤልን የሚመለከት እንደሆነ ልንገነዘብ እንችላለን።

*ታላቁ መከራ ለእስራኤል ምን ማለት እንደሆነ?*

ቀደም ብለን እንደተናገርነው የፀረ ክርስቶስ እስራኤል በዘመናት ሁሉ ካየችው የበለጠ ታላቅ የአይሁድ የመከራ ስደት እንድትቀበል ያደርጋታል። ነብዩ ዘካርያስ ስለዚህ፡-

*«በምድር ሁሉ ላይ ሁለት ክፍል ተቆርጠው ይሞታሉ ይላል እግዚአብሔር፣ ሦስተኛውም ክፍል በእርስዋ ውስጥ ይቀራል። ሦስተኛውንም ክፍል ወደ እሳት አገባለሁ፣ ብርም እንደሚነጥር አነጥራቸዋለሁ። ወርቅም እንደሚፈተን እፈትናቸዋለሁ፣ እነርሱም ስሜን ይጠራሉ፣ እኔም እሰማቸዋለሁ፣ እኔም ይህ ሕዝቤ ነው እላለሁ። እርሱም እግዚአብሔር አምላኬ ነው ይላል» በማለት ተናግሯል (ዘካ. 13:8-9)።*

እንደዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቃል አነጋገር ከእስራኤል የሚቀረው ሲሰው ሕዝብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ስለ ቅሬታው ሕዝብ ብዙ ጊዜ ይናገራል። አዲስ ኪዳን እነዚህን ሕዝቦች *በ ማቴ.24:22፤24፤31፤* ሮሜ.11:7 እና በሌሎችም ቦታዎች «የተመረጡ ሕዝብ» በማለት ይጠቅሳቸዋል። ከአይሁድ ሕዝብ በዚህ በታላቁ መከራ ሁለት ሦስተኛው የሚጠፋ ከሆነ፣ ይህ ጊዜ ለእስራኤል የተሀድሶና በፍርድ (በቅጣት) የማለፍ ጊዜ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

ይህ የእሳትና የመከራ ፍርድ (ቅጣት) እውነተኛውን መሲህ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚፈልጉ አይሁዶች ከታላቁ መከራ ፍጻሜ ላይ እንዲገለጡ (እንዲታዩ) የሚያደርጋቸው ዕቅድ ነው። እነዚህ ቅሬታዎች መላ እስራኤል የተባሉት ይሆናሉ (*ሮሜ.11:26*)። እነዚህን በሙሉ ልብ በመጠበቅ፣ በመቀበልና በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው በማለት ወደ እርሱ ይጮሃሉ (ባሩክ ሀባ ዊ በኪም አዶናይ) (*ማቴ.23:39*)።

ዛሬ ጥቂት የአይሁድ የሃይማኖት ክፍሎች መሲሁ የሚመጣው ሁለት ጊዜ ነው የሚለውን አስተያየት ይደግፋሉ። ይህም እንደ ቤን ጆሴፍ (የዮሴፍ ልጅ) ከዚያ በኋላ እንደ ቤን ዳቪድ (የዳዊት ልጅ) ሆኖ ይመጣል የሚሉት ናቸው። ቤን ጆሴፍ (የዮሴፍ ልጅ) ሀሰተኛው ነው ቤን ዳቪድ (የዳዊት ልጅ) እውነተኛው ነው። ወደዚህ መደምደሚያ እንዴት መጣችሁ? ለሚለው ጥያቄ ብዙ የአይሁድ መምህራን የሚሉት እውነተኛውን መሲህ ማወቅ የሚቻለው ከሀሰተኛው መሲህ ስህተቶችና ማታለል የተነሳ ነው ይላሉ።

በመከራው ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ የዮሴፍ አስር ወንድሞች ወደ ግብፅ በመጡ ጊዜ የሆኑትን ይሆናሉ። ዮሴፍን አላወቁትም ነበር። በዚህ በእርሱ ተፈተኑና ተጣሩ በመጨረሻ ከራሳቸው የሕሊና ወቀሳ ግፊት የተነሳ «በእውነት ወንድማችንን በድለናል፣ እኛን በመማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውምና ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን» በማለት እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ (*ዘፍ.42:21*)። በመከራቸው ዘመን አስሩ ወንድማማች ስለ ሰሩት ኃጢአት ሕሊናቸው ወቀሳቸው። በዮሴፍ ፊት በደለኞች መሆናቸውን ተገነዘቡ። ከውስጥ ከልባቸው መራራ የሆነ ሐዘን በማዘን ስለ ክፉ ስራቸው ተጸጸቱ። በተመሳሳይ ሁኔታ ታላቁ መከራ የአይሁድ ሕዝብ በደላቸውን እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል። በሐሰተኛው መሲህ እጅ በመውደቃቸውና ቀደም ብለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛው መሲህ አድርገው ባለመቀበላቸው ከውስጥ የሆነ እውነተኛ ጸጸት ይጸጸታሉ።





ስለዚህም ታላቁ መከራ ለእስራኤል ሕዝብ የተሀድሶ ፍርድ ነው። የእስራኤልን ህዝብ ጥልቅ ወደ ሆነ ንስሀና የልብ ለውጥ ለማምራት የታቀደ አሠራር ነው። በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በአክብሮት ይቀበሉታል (*ኤር.46:28፤ ሉቃ.21:24*)።

## የታላቁ መከራ ምንነት ሳልዳኑት የዓለም ሕዝቦች

ታላቁ መከራ በመጀመሪያ ችግር የሚፈጥረው በእስራኤል ምድርና ሕዝብ ላይ ቢሆንም እንኳ ከዚያም አልፎ በመላው ዓለም ላይ የሚያመጣው ችግር አለው። ልንረሳው የማንችለው ነገር ቢኖር በተለይም በዚህ በመከራው ዘመን በመላው ዓለም አመጸኝነትና ክርስቶስን የመቃወም (የመጥላት) ነገር በፍጥነት እየጨመረ የመሄዱን ነገር ነው። ምክንያቱም መላው የሰው ዘር በሙሉ:-

1. *ከሐደማኖት የተለዩ* ደሆናቱ ይህም ማለት የዓለም ይሆናሉ ማለት ነው።
2. *በርኩሰት የሚቀጥሉ ገድ የለሽ* ደሆናቱ ይህም ማለት ራሳቸውን ለሥጋ ምኞት በማስገዛት በሁሉም አጸያፊ፣ ከእውነትና ከቅድስና የተለዩ ይሆናሉ ማለት ነው።
3. *በሰደጣን ቁጥጥር ስር* ሠሆን ይህም ልበ ደንዳኖች በእግዚአብሔር ቃል የማይደሰቱና በሰይጣን ክፉ ኃይላት እንደሚያዙ ያመለክታል።

ስለዚህም የመጨረሻዎቹ ቀናት በሰይጣናዊ የአሠራር ባሕርይ የተያዙ ናቸው። አንዳንዶች በዓለም ተሀድሶ ይሆናል ብለው እንደሚጠብቁት አይደለም። ሰዎች ከእግዚአብሔር ከመለየታቸው የተነሳ፣ በተለይም በፀረ ክርስቶስ መንግስት አንድ ቀን መላው ዓለም ለሰይጣን የሚሰግዱ ይሆናሉ። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል:-

*«ለዘንዶውም ሰገዱለት፣ ዘንዶው ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና፣ ለአውሬውም ለውሬውን ማን ይመስለዋል፣ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል እያሉ ሰገዱለት» በማለት ይናገራል (ራዕ.13:4)።*

ይህ አስደንጋጭ ሁኔታ አመጸኛ የሆነውን የሰው ዘር ውስጣዊ ሁኔታ ፈጽሞ የተበላሸ መሆኑን የሚያሳይ ነው። አውሬውን ማለትም የፀረ ክርስቶስና ዘንዶውን፣ ራሱን ሰይጣንን ያከብራሉ ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚጠራ ይሆናል። የሰው ዘር ወደ ሰማይ መሄድ የማይፈልግ ከሆነ ወደ ሲኦል የሚሄድ ይሆናል። የፀረ ክርስቶስ ዘመን የዘላለሙ ቅጣት እስኪጀምር በምድር ላይ ተወዳዳሪ የሌለው ሲኦል ይሆናል ማለት ነው።

## የመጨረሻው ቀናት የምጥ ጣር ጅማሬዎች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት በተናገረበት ጊዜ «ስለ ምጥ ጣር ጅማሬዎች» ተናግሯል (*ማቴ.24:8*)፡፡ እንደምናውቀው ሁሉ የምጥ ጣር የሚሆነው ልጅ ከመወለዱ በፊት ነው፡፡ እነዚህ ምጦች በድንገት የሚሆኑና በመጀመሪያም በተለያዩ ጊዜያት የሚመጡት ናቸው፡፡

| የምጥ ጣር ጅማሬዎች<br>በመጨረሻዎቹ ቀናት<br>እንደ ማቴ.24:1-36 | የምጥ ጣር ጅማሬዎች ሙሉ ይዘታ<br>በመጨረሻዎቹ ቀናት<br>እንደ ራዕ.6:1-7፤17 |
|---|---|
| **የማቴ 24 እና ራዕ 6 ንጽጽር** | |
| **1. ሀሰተኛ ነቢያት**<br>ማታለል፣ ሀሰተኛ መሲህ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ (ማቴ. 24:4፣5፣11፣23-26) | **1ኛው ማህተም በነጭ ፈረስ**<br>የተቀመጠው ማታለል፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ ሀሰተኛ ነቢያቶች (ራዕ.6:1-2) |
| **2.ጦርነቶች**<br>የጦርነት ወሬዎች፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ (ማቴ. 24:6-7) | **2ኛው ማህተም በቀይ ፈረስ**<br>የተቀመጠው ሰላም አጦት፣መገዳደል፣ ታላቁ ጦርነት (ራዕ.6:3፣4) |
| **3.ችግር ጊዜ**<br>ረሀብ (ማቴ. 24:7) | **3ኛው ማህተም በጥቁር ፈረስ**<br>የተቀመጠው የችግር ጊዜ፣ረሀብ (ራዕ.6:5፣6) |
| **4.ቸነፈር**<br>ተላላፊ በሽታ፣ የሕዝብ ማለቅ (ማቴ. 24:7) | **4ኛው ማህተም በሐመር ፈረስ**<br>የሕዝብ ማለቅ፣ ሞት፣ ተላላፊ በሽታ (ራዕ..6:7፣8) |
| **5. ስደት**<br>መከራ፣ ስሞት አልፎ መሰጠት (ማቴ. 24:9) | **5ኛው ማህተም የሰማዕታት**<br>ከመስውያው ስር ስደ፣ መከራ፣ ስቃይ፣ ለሞት አልፎ መሰጠት (ራዕ.6:9-11) |
| **6. የምድር መናወጦች**<br>የተፈጥሮ ጥፋት (ማቴ. 24:7) | **6ኛው ማህተም የምድር መናወጦች:-**<br>መናወጥ የፀሐይ መጨለም፣ የጨረቃ እንደ ደም መሆን (ራዕ.6 12-17) |
| **7. እስራኤል**<br>ከታላቁ መከራ መጠበቅ፣ መታደስና መዋጀት (ማቴ. 24:14-36) | **7ኛው ማህተም ከእስራኤል የታተሙ**<br>144.000 በታላቁ መከራ ጊዜ ለመጠበቅ የታተሙ (ራዕ.7:1-17) |
| **ጌታ ኢየሱስ ይመጣል**<br>**ማቴ.24:30** | |





ልጁ እስከሚወለድበት ድረስ ተደጋግመው የሚቀጥሉና በመደጋገም እየባሱ የሚሔዱ ይሆናሉ፡፡ ጌታ የደህንነትን ታሪክ ለመግለጽ በየዕለቱ የሚታዩትን ሁኔታዎች በመጠቀም ተናግሯል፡፡ በዚህ ምድር ላይ ከቀራንዮና ከበዓለ ሀምሳ ጀምሮ በጸጋ ዘመን ውስጥ ኖረናል፡፡ ይህ የጸጋ ዘመን በጌታ መምጣትና በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ያበቃል፡፡ ጌታ ከጸጋው ዘመን ጀምሮ፣የመከራውን ጊዜና እስከ እርሱ መምጣት ያለውን የምጥ ጣር ጊዜ በማለት ጠርቶታል፡፡ ጌታ ይህን የሽግግር ዘመን «የሺው ዘመን መንግሥት» በማለት ገልጾታል፡፡

| የምጥ ጣር ጅማሬዎች መጨመር<br>በመጨረሻዎቹ ቀናት<br>እንደ ራዕ. 8:1-12 ፤ 17 | የምጥ ጣር ፍጻሜያቸው<br>በመጨረሻቹ ቀናት<br>እንደ ራዕይ.13:1-19 ፤ 21 |
|---|---|
| በምድር ሲሶ ላይ የሚሆን ፍርድ | የሰው ዘር ፍርድ ፍጻሜ |
| **1ኛው መለከት**<br>የተፈጥሮ ሲሶ መቀጠል(ራዕ.8:6፣7) | **1ኛው ጽዋ**<br>የሰው ዘር ሁሉ በተለያዩ በሽታዎች መያዝ (ራዕ.16:1-2) |
| **2ኛው መለከት**<br>የባሕር ሲሶው መበላሸት (ራዕ.8:8፣9) | **2ኛው ጽዋ**<br>የውሀ ወደ ደም መለወጥ፣ በውስጣቸው ያሉት በሙሉ መሞት (ራዕ.16:3) |
| **3ኛው መለከት**<br>የወንዞችና የምንጮች መበከል (ራዕ.8:10፣11) | **3ኛው ጽዋ**<br>የወንዞችና የምንጮች መበከል (ራዕ.16:4-7) |
| **4ኛው መለከት**<br>የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ሲሶ መመታት (ራዕ.8:12፣13) | **4ኛው ጽዋ**<br>የፀሐይ በሙሉ መመታት፣ የሕዝብ በጸሐይ ኃይል መቃጠል (ራዕ.16:8፣9) |
| **5ኛው መለከት**<br>የጥልቁ መከፈት፣ በሰይጣን ኃይል ብዙ<br>ስቃዮች መሆን (ራዕ.9:1-12) | **5ኛው ጽዋ**<br>በክርስቶስ ተቃዋሚ ምክንያት በመንግስቱ ላይ ጨለማና ሥቃይ (ራዕ.16:10፣11) |
| **6ኛው መለከት**<br>ከሰዎች ሲሶ በጦርነት መገደል (ራዕ.9:13-21) | **6ኛው ጽዋ**<br>በአርማጌዶን የክርስቶስ ተቃዋሚወታደሮች በጠቅላላ መገደል (ራዕ.16:12-16) |
| **7ኛው መለከት**<br>በታላቁ መከራ ጊዜ የእስራኤል መጠበቅና መዳን (ራዕይ 11:1-12፤17) | **7ኛው ጽዋ**<br>አስቃቂ የምድር መናወጦች (ራዕ.16:17-21)<br>አጠቃላይ ፍርድ በባቢሎን ላይ (ራዕ.17:1-18 እና ምዕ. 24) |
| **ጌታ ተመልሶ ይመጣል!**<br>**ራዕይ.19:11-21** | |

ባጭሩ እንደምናያቸው እነዚህ የምጥ ጣሮች ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት የሚከናወኑ ናቸው:: የፀረ ክርስቶስ በሚመጣው በታላቁ መከራ ጊዜ ወደ ሙላት ይደርሱና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ ሲመጣ ያበቃሉ:: ጌታ *በ(ማቴ.24:8)* ስለተናገረው «ስለ ምጥ ጅማሬ» በበለጠ ለመረዳት ወደ አስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ፍጻሜ ቀስ ብለን መሔድ አለብን:: ይህ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በቅድስት ምድር የመሰባሰብ ጅማሬ ነው:: ራሳቸውን ከዓለምና ከደህንነት ታሪክ ጋር ያያዙ ሰዎች እንደሚሉት እነዚህ «የምጥ ጣሮች» የጀመሩት በ1897 አስቀድሞም ነበር በተደረገው የመጀመሪያው የጽዮናውያን እንቅስቃሴ ጊዜ ነበር::

በዚያን ጊዜ በዓለም ያለ ማንኛውም ሰው ስለዚህ ጉዳይ ትኩረት አልሰጠውም ይመለከተዋል:: ከአስራ ሰባት ዓመታት በኋላ በአንደኛው ዓለም ጦርነት ፍንዳታ በዓለም የሚኖሩ ሰዎች «የምጥ ጣር» ስለሆኑት ጊዜያት በግልጽ ማስታወስ (መገንዘብ) ጀመሩ:: በአራቱ በጥንቱ መንግስታት ድንበሮች ላይ በተለይም በአውሮፓና በእስያ ያሉት መንግስታትና ግዛቶች ወደቁ አዲስ አገሮች መንግስታት፣ ግዛቶችና ዲሞክራሲዎች ተመሠረቱ:: በዚህ ትርምስ ውስጥ ሕዳር 2 ቀን 1917 ዓ.ም. በባልፎሩ ውሳኔ አይሁዳውያን ብሔራዊ ምድር (የእስራኤል ምድር) እንደሚኖራቸው የተስፋ ጭላንጭል ታየ::

ቀጣዩ የምጥ ጣር ማለትም 2ኛው የዓለም ጦርነት ዳግም ከ20 ዓመት በኋላ ተከሰቶ:: ከ1939-1945 ዓ.ም. ዓለምን አናወጣት የፖለቲካዋንም ይዞታ ቀየረው:: የምስራቁ ብሎክ (ሕብረት)፤ የምዕራቡ ኢንዱስትሪ የበለጸጉት ሕዝቦችና የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ምስረታ የዚህ ጦርነት ውጤት ናቸው:: ያለ ጥርጥር የእነዚህ የምጥ ጣር ዋና ምክንያት በግንቦት 1 ቀን 1948 ዓ.ም. የሆነው የእስራኤል መንግስት መመስረት በእነዚህ ጥቂት መረጃዎች መሰረት በዓለም ሕዝቦች ውስጥ የሚሆኑ የምጥ ጣሮች ከእስራኤል ጋር የተያያዙ መሆናቸውን እንገነዘባለን:: በመቀጠል የአሁኗ የእስራኤል መንግስት እንደ ተዓምር ብቅ ብላ ታየች::

ይህ ሁኔታ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የዓለም ሕዝብ ሰላም አላገኘም:: በየክልሉ የምጥ ጣሮች እየፈነዱ ናቸው:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ 140 የሚያህሉ ጦርነቶችና ውዝግቦች ተከስተው ከ30 ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች ሞተዋል:: የእግዚአብሔር ዋና ከተማ የሆነችው ኢየሩሳሌም በ1967 ዓ.ም. የእስራኤል ምድር ሆነች ከስድስቱ ቀን ጦርነት በኋላ የምጥ ጣሮች በአስደናቂ ሁኔታ እየጨመሩ መጡ:: በዮርዳኖስና በቀይ ባሕር መካከል ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የተስፋ ምድር በእስራኤል እጅ ገባ:: ከዚህን ጊዜ ጀምሮ የምጥ ጣሮች አላቆሙም:: ከዚህ





በፊት ያልሆኑ ድንገተኛ ለውጦች ታይተዋል:: ክስተቶቹ ባፋጣኝ አንዱ በአንዱ ላይ እየተነባበሩ በግልጽ እየታዩ ናቸው:: በጊዜው የሚታዩትን ሂደቶች ስንመለከት ይህን በግልጽ ያመለክቱናል:: ለምሳሌ ያህል:- አለም አቀፍ ሽብርተኝነት በ1967 ዓ.ም. ተጀመረ፣ ዓለም አቀፍ የሰይጣን ቤተ ጸሎት መመስረት፣ የወሲባዊ ትምህርት በትምህርት ቤት መሰጠት፣ ሰዶማዊ ድርጊቶች በግልጽ መሆን፣ ነፃ የሆነ የሞራል ሕግ መመስረት፣ በወጣቶች መካከል እፅ የመጠቀሙ ነገር መጨመሩ፣ የሩቅ ምስራቁ ሃይማኖት ወደ ምዕራቡ ዓለም መግባት፣ በክርስትና ሀገሮች አክራሪ የሆነ የእስልምና ሃይማኖት መግባት፣ በአጠቃላይ የሩቅ ምስራቁ ቴራፒ (ዮጋ፣ አውቶጀነስ ስልጠና መካሔድ፣ የደረቅ መርፌ ሕክምና ወ.ዘ.ተ)፣ የድሎት ምግቦች፣ የሲጋራና የመጠጥ ፍጆታና የምድራዊ ደስታ ፍላጎት መጨመር በዓለም እየተስፋፋ ያለው ሰይጣናዊ የሆኑት የሮክና የፖፕ ሙዚቃዎች፣ ምስጢራዊ ሰይጣናዊ አሰራሮች፣ አመጽ፣ ግብረ ገደቢስነትና ከፋት የተሞሉባቸው ጽሑፎች ፊልሞችና ቪድዮዎች በየስቶሩ መብዛትና መገኘት ናቸው:: በአሁኑ ጊዜ አሕዛብ የሰይጣናዊ ሃይማኖቶችን (አምልኮዎችን) አዲስ ተሐድሶን እየተለማመዱ ናቸው:: ሰዎች ፀሐይን ያመልካሉ፣ የተለያዩ የጥንቆላ በዓላትን ያከብራሉ፣ ማንኛቸውንም ዓይነት አስማቶችን ይለማመዳሉ:: በአሁኑ ጊዜ ያለው ሕብረተ-ሰብ ሃይማኖታዊ ልምምዶችን፣ ማሰላሰልንና መመራመርን ስለመናፍስት ማውራትን፣ አስማትንና ድግምትን በመጠቀም ላይ ይገኛል:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ሲል «እንደ ኖህ» ዘመን እንደሚሆን አመልክቷል (*ማቴ.24:37-39*)::

እነዚያ የኖህ ዘመን ክፉ ልምምዶች ዛሬም ከእኛ ጋር እንዳሉ የማይካድ ሀቅ ነው:: የውጭውን ዓለም ሁኔታ ትኩረት ሰጥተን ብንመለከት የመጨረሻው ዘመናት ምጥ ጣሮች እየተፋጠኑ በመሔድ ላይ እንዳሉ ያረጋግጡልናል:: እየጨመረ ያለው ጥፋትና የአከባቢ (የመጠጥ ውሃ የመሬትና የአየር) ብክለት ዓለም አቀፍ የሙቀት መጠን መጨመር (የኦዞን መቀደድ) የውቅያኖሶች መበከል (የነዳጅ ዘይት ዝቃጭ) እየጨመረ ያለው በሽታ (የመበረዝ፣ የላንባ ነቀርሳ፣ የኤድስ ወ.ዘ.ተ) የምጥ ጣሮች ናቸው ብዙ መመዝገብ ይቻላል:: በየቀኑ የሚታተሙትን ጋዜጦቻችንን ስናይ በእነዚህ ልምምዶች የተሞሉ ናቸው::


ሆኖም ይህ ሁሉ «የምጥ ጣር መጀመሪያ» ነው፣ ምክንያቱም ፀረ ክርስቶስ ከመገለጡ በፊት እየጨመሩ የሚታዩ ናቸው:: ቀጥሎ ጨመቅ ተደርገው የተገለጡት ቻርቶች በ ማቴዎስ 24 የተጠቀሱትን የምጥ ጣር ዓይነቶች እንዴት እንደሚጀምሩና ከዚያም በመቀጠል እስከ መጨረሻው የአስፈሪው ፍርድ ቀናት ድረስ መቀጠላቸውን

የሚያሳዩ ናቸው:: ከ ራዕ.6-19 ያሉት ፍርዶች መለኮታዊ ፍርዶች ናቸው:: ማለትም በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚመጡ ፍርዶች ናቸው ማለት ነው:: በመጨረሻው ቀናት በአጋጣሚ የሚከሰቱ ማንኛውም ዓይነት የተፈጥሮ ጥፋቶች አይደሉም:: እነዚህ ፍርዶች ለብዙ ሺህ ዓመታት ወንጌልን ላለመቀበል በመረጡትና ወንጌልን በተቃወሙት ላይ የሚወርዱ መሆናቸውን ልንገነዘብ ያስፈልገናል:: እግዚአብሔርንና ጌታ ኢየሱስን እንዲቃወሙት ያደረጋቸውን ፀረ ክርስቶስን የሚቀበለው ይህ ሕዝብ ነው:

መጽሐፍ ቅዱስ በራዕይ መጽሐፍ የተጻፉትን ሶስቱን ዓይነት ፍርዶች በመለየት አስቀምጧቸዋል::

1. የማህተም ፍርዶች (ራዕይ.6:1-17፣ 8:1)
2. የመለከት ፍርዶች (ራዕይ.8:2-9:21፣ 11:15)
3. የጽዋው ፍርዶች (ራዕይ.16:1-2)

እነዚህ ፍርዶች ሁሉ በፀረ ክርስቶስ የመከራ ዘመን በሰው ዘር ላይ የሚወርዱ ናቸው:: ስለዚህም በማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ ዳግም መምጣት ባለው ጥያቄ ምልክት መካከል የተደረገ ነው:: የዚህ ፍርድ ጊዜ ሊገመት የማይቻል አስፈሪ የሆነ ነው:: ከላይ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በምናነብበት ጊዜ «እነዚህ ቀኖች ባያጥሩ» ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነ ነበር የሚለውን ልንገነዘብ እንችላለን (ማቴ.24:22)::




ስለዚህ ፀረ ክርስቶስ የሚያመጣው መከራ ለእስራኤል ተሐድሶ ፈተናና ፍርድ መሆኑን ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር እስራኤልን ለሚመጣው እውነተኛ መሲህ የሚያዘጋጃት ነው ማለት ነው:: በመጀመሪያ እስራኤል ፀረ ክርስቶስን ይቀበሉትና በኋላ ግን የሚጠይቀውን አምላካዊ አክብሮት ባለመስጠት ይቃወሙታል:: ሆኖም ትልቁ መከራ ለሚጠፉት (ጌታን ላልተቀበሉት)





የጥፋት ፍርድ ይሆንባቸዋል:: ምክንያቱም ዘንዶውንና አውሬውን በግል ስለሚያመልኩት (ራዕ.13:4) በዚህም ሰይጣን የሚጠይቀውን አምልኮት በቀጥታ ስለሚሰጡት ነው::

## ፀረ ክርስቶስና ሐሰተኛው ነቢይ

የፀረ ክርስቶስ ማንነትና መንግስቱን በተመለከተ ቀደም ያሉት መግለጫዎች ግልጽ አድርገውታል:: ታላላቅና እታላይ የሆኑት ኃይላት በዓለም ማንኛውንም ሰው ለፀረ ክርስቶስ እንዲሰግድ ያደርጉታል (ራዕ.13:4):: መጽሐፍ ቅዱስ ክፉና የሰይጣን መናፍስት የዓለም ነገሥታትን ለማታለል እንደሚዞሩ ይናገራል (ራዕ.16:13-14):: ከእነዚህ የጨለማ ኃይላት እርዳታ ውጪ መላው ዓለም በሌላ ኃይል ለፀረ ክርስቶስ ሊሰግድለት አይችልም::

የራዕይ መጽሐፍ የፀረ ክርስቶስ በፀረ-ክርስቲያናዊ የዓለም መንግስታት ላይ የመጨረሻው መሪ በመሆን አስፈሪ ስልጣኑን ለብቻው እንደማያሳይ ይነግረናል:: ተከታዩ የሆነው ረዳው በጎኑ ይቆማል:: ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ

*«ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፤ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር» በማለት ይናገራል (ራዕ.13:11)::*

እዚህ ሁለተኛውን አውሬ እንመለከታለን:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አውሬ «ሀሰተኛው ነቢይ» በማለት ይገልጸዋል:: (ራዕ.19:20) ይህ አውሬ የመለኮት ተቃዋሚ የሆነው የሰይጣናዊ ሦስትዮሽ ሦስተኛው ሰው ነው:: ራሱንም እንደሚከተለው ይገልጻል:: የሠይጣን ሦስትነትም እንደሚከተለው ይገለፃል::

1. ዘንዶው:- ራሱ ሰይጣን (ራዕ.12)
2. ከባሕር የሚወጣው አውሬ-የፀረ ክርስቶስ (ራዕ.13:1-8)
3. ከምድር የሚወጣው አውሬ - ሀሰተኛው ነቢይ (ራዕ.13:11) ናቸው::

ከመለኮት ሁለተኛውና ሦስተኛው ማንነት (ኢየሱስ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ) ከላይ ከሰማይ ወደ ምድር ወርደዋል:: በተቃራኒው ደግሞ የሰይጣን ሦስትዮሽ ሁለተኛውና ሦስተኛው አካል (ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛው ነቢይ) ከታች ከጥልቅ ይመጣል:: (ራዕ 11:7፣ 17:8) ፀረ ክርስቶስ ከባሕር ሲወጣ (ከሕዝብ መካከል) (ራዕ.13:1) በተቃራኒው ደግሞ ሐሰተኛው ነቢይ ከምድር (ከእስራኤል) ይወጣል:: በእስራኤል ከሚኖሩት ሰዎች አንዱ ሊሆን ይችላል::

የሚቀጥለው ንጽጽር ሀሰተኛው ነብይ የመንፈስ ቅዱስ ተቃራኒ እንደሆነ ያሳየናል:: በቅጂ (የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በማስመሰል) ሰዎችን ለክርስቶስ ተቃዋሚ እንዲሰግዱ ያደርጋል::

| መንፈስ ቅዱስ<br>ዮሐ. 16:13-15 | [illegible] |
| --- | --- |
| 1. መንፈስ ቅዱስ እንደሚነድ እሳት ከሰማይ መጣ (ሐሥ.2:1-4):: | 1. ሀሰተኛው ነቢይ ከሰማይ እሳት እንዲወርድ ያደርጋል (ራዕ 13:13):: |
| 2. መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን ያከብራል (ዮሐ.16:14-15):: | 2. ሀሰተኛው ነቢይ ፀረ ክርስቶስን ያከብራል<br>(ራዕ. 13:15):: |
| 3. መንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱትን አብንና ወልድን እንዲያመልኩ ይመራል (ዮሐ. 4:23-24):: | 3. ሀሰተኛው ነቢይ ሰዎች ፀረ ክርስቶስንና ሰይጣንን እንዲያመልኩ ያበረታታል (ራዕ. 13:13-17):: |
| 4. መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያቱ በኩል ድንቅና ተዐምራትን ያደርጋል (ዕብ.2:4):: | 4. ሀሰተኛው ነቢይ ምልክቶችንና ታምራቶችን ያደርጋል፡ (ራዕ.13:13):: |
| 5. መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ያትማል (2ቆር. 1:22፤ ኤፌ.1:13፤ 4:30) | 5. ሀሰተኛው ነቢይ የማያምኑትን የራሱን ምልክት ያትምባቸዋል (ራዕ. 13:16) |
| 6. መንፈስ ቅዱስ በመስቀል ላይ የተፈጸመውን የደህንነትን ሥራና የክርስቶስ ትንሣኤ ከፍ ከፍ ያደርጋል(1ቆር.1:23፤2:2፤ዮሐ.14:6፤ ሐሥ.1:8፤ 1ጴጥ.1:11፤ 1ተሰ.1:4-6):: | 6. ሀሰተኛው ነቢይ የፀረ ክርስቶስን መቁሰልና መነሳት /መፈወስ / ከፍ ከፍ ያደርጋል /የክርስቶስ ትንሣኤ ቅጅ በማድረግ ሰይጣናዊ ትንሣኤ/ (ራዕ.13:12):: |
| 7. መንፈስ ቅዱስ አማኞች ክርስቶስን እንዲመስሉ ይለውጣል::<br>(2ቆር.3:17፤18 ሮሜ.8:26-30) | 7. ሀሰተኛው ነቢይ የፀረ ክርስቶስን ምስል እንዲያመልኩ ይጋብዛል::<br>*(ራዕ.13:14-15):*: |

ሁለቱም ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛው ነቢይ በመዋጀት ካርታ ላይ በስም ተጠቅሰዋል:: እነዚህ ሰይጣናዊ ሰዎች ሰዎችን ወደ ጥልቁ ለመሳብ አንድ ላይ ይገለጣሉ::

*የሐሰተኛው ነቢይ ሚና በፀረ ክርስቶስ መንግስት ምንድን ነው?*

እንደ *(ራዕ.13:11-18)* መሠረት ሀሰተኛው ነቢይ የፀረ ክርስቶስ አስተዋዋቂ ነው:: ፀረ ክርስቶስ ስልጣን በፊቱ በማድረግና ስለ እርሱ በመቆም ሰዎች ይህን





የመጨረሻውን የዓለም መሪ እንዲያከብሩትና መለኮታዊ አክብሮት እንዲሰጡት ያደርጋል *(ራዕ.13:14)*: ማንኛውም ሰው ሀሰተኛውን ነቢይ ለመቃወም ምርጫ አለው:: አስፈሪና አስገዳጅ ኃይል ከእርሱ ጀኔራል ጋር ይሆናል:: አሳች ኃይሎች ማለት ነው:: ፀረ ክርስቶስ ወይም ምስሉን (የአውሬውን ምስል) ላለማምለክ አሻፈረኝ የሚሉት ይሰደዳሉ፣ ይገደላሉ:: *(ራዕ.13:15)*

## ሐሰተኛው ነቢይ

- እንደ ዘንዶው ይናገራል *(ራዕ.13:11)*
- ፀረ ክርስቶስ ስልጣን ይጠቀማል *(ራዕ.13:12)*
- ታላላቅ ምልክቶችን ያደርጋል *(ራዕ.13:13)*
- ከሰማይ እሳት እንዲወርድ ያደርጋል *(ራዕ.13:13)*
- ሰዎች ፀረ ክርስቶስን ለማክበር «ምስል» እንዲያበጁ ያስገድዳል *(ራዕ.13:14)*::
- ለአውሬው ምስል እስትንፋስ ይሰጠዋል *(ራዕ.13:14፣15)*
- ማንኛውም ሰው «ምልክትን» እንዲቀበል ያስገድዳል *(ራዕ.13:16፣17)*

ከእነዚህ ጥቂት ነጥቦችን እንመልከት::

## «እንደ ዘንዶው ይናገራል»

ሀሰተኛው ነቢይ ከፀረ ክርስቶስ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ባሕርይ አለው:: ከፍተኛ የመናገር ችሎታ አለው:: በተለይም ፀረ ክርስቶስን ከፍ ከፍ በሚያደርግበት ጊዜ የንግግር ችሎታው የተገለጠ ይሆናል:: በተጨማሪ እንደ ፀረ ክርስቶስ «በአማልክት አምላክ ላይ በትዕቢት» ይናገራል *(ዳን.11:36)*: «እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንም፣ ማደሪያውንም፣ በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ» አፉን ይከፍታል:: *(ራዕ.16:6)* መለኮታዊ፣ ሰማያዊ፣ የክቡሩና ዘላለማዊ የሆኑትን ማንነቶችና ነገሮች እንደ እድፍ አድርጎ በማሰብ ፍጹም ዋጋ የሌላቸው ከንቱዎች አድርጐ ይቆጥራል *(ሮሜ.1:28)*: የሰይጣን ዜና አሰራሮች የዚህችን ዓለም ውበት ለዓለም ሕዝቦች ብሩህ አድርገው በመሳል እንዴት እደሚያታልሉ ያውቃሉ *(ማቴ.4:8)*: መላው የሰው ዘር ከእውነት በመለየት፣ ከተስፋዎች ሁሉ ርቀው በመወሰድ (በአጠቃላይ በምድራዊ ቁሳቁሶችና በሚያልፉት ነገሮች በመወሰድ) መላ ሕይወታቸውን ከታላቁ መሪ ፀረ ክርስቶስ ጋር የተጣበቀ ያደርጉታል:: ከእግዚአብሔር በመራቅ ወደ ክፋው ክህደት ይገባሉ:: የዚህ ሰይጣናዊ ነቢይ ንግግር ቁጥር የሌላቸውንና በአጠቃላይ በሰይጣን የተያዙትን ሕዝቦች ለሰይጣን እንዲሰግዱ ያደርጋቸዋል *(ራዕ.13:4)*::

## «ታላላቅ ምልክቶችን ያደርጋል»

ዛሬ እየጨመሩ ስላሉት «ምልክቶችና ተዓምራቶች» ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ እውነት ነው። በየአቅጣጫው በዜና ማሰራጫዎች ይታያሉ። ጋዜጦችና ቴሌቪዥኖች አስደናቂ የሆኑ ሁኔታዎችን፣ ስሜታዊና ተዓምራዊ የሆኑ ነገሮችን ያቀርባሉ። እነዚህ ነገሮች በሕዝብ መካከል የተገለጡ ሆነዋል ምክንያቱም የሚስቡ ስለሆኑ ምልክቶችና ታምራቶች በፀረ ክርስቶስ መንግስት ከፍተኛ ስፍራ አላቸው። ሰይጣን ጉጉት ያላቸውን ሰዎች እንዴት እንደሚስብ ያውቃል። ስለዚህም ሀሰተኛው ነቢይ ብዙ ታላላቅ *ሥራዎችን* ይሠራል። «እሳትንም እንኳን ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪወርድ ድረስ» ያደርጋል (*ራዕ.13:13*)። በታምራቱ የተደነቁት የሰው ዘሮች ከመሳሳታቸው የተነሳ በእነዚህ ታምራት አድራጊዎች የተገለጠው ኃይል ከእግዚአብሔር የመጣ ነው በማለት ያምናሉ።

የፀረ ክርስቶስ ተዓምራታዊ መዳን (በድጋሚ መነሳት) በብዙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ውጤት ያስከትላል ያመጣል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ

*«ከራሶቹም ለሞት እንደታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፣ ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰ። ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ» በማለት ይናገራል (ራዕ.13:3።)*

ከፀረ ክርስቶስ መገለጥ ጋር የተያያዘው የመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነው። ስሞት የሚሆን ወደሞት የሚያደርስ መቁሰል በእርሱ ላይ ከደረሰ፣ በእርግጥ ይገደላል ማለት ነው። ለሞት የሆነ አደጋ የሚደርስበት ሰው ይሞታል። ስለሆነም ፀረ ክርስቶስ ወደፊት ይሞታል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ለሞቱ የሆነው ቁስሉ በድንገት እንደሚፈወስ ይነግረናል። ይህም ማለት ፀረ ክርስቶስ ተሐድሶ ደርጋል ወይም በተለየ ሁኔታ ይገለጻል ማለት ነው። ፀረ ክርስቶስ ለመላው ዓለም እርሱ እውነተኛው መሲህና መሪ መሆኑን ለመግለጽ በሰይጣናዊ መንገድ የክርስቶስ ኢየሱስን ትንሳኤ በማስመሰል ይጠቀማል። ለጊዜው ይህ «ምልክት» አይሁድን እንኳን የሚስባቸው ይሆናል። ለረጅም ዘመናት የተጠበቀው መሲህ እርሱ ነው በማለት ፀረ ክርስቶስን ይቀበሉታል። በኢየሩሳሌም በነበርንበት ጊዜ ጥቂት አይሁዶች «ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት አልዓዛር በቢታንያ ከሞት እንደተነሣ (ዮሐ. 11:1-45) ኢየሱስ ክርስቶስም ከሙት የተነሳና በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች የተዘዋወረ ቢሆን ኖሮ መላ እስራኤል በእርሱ ያምኑ ነበር» ብለውናል። ፀረ ክርስቶስ የሚያደርገው ልክ እንደዚህ ነው።





ፀረ ክርስቶስ ሙት ከቀረበ ህልውና ይነሳል፤ ራሱንም እውነተኛ መሲህ በማድረግ ይገልፃል። ኢየሱስ ክርስቶስን ግን ይቃወማል (ይኮንናል)። በዚህ ድርጊቱ እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ መላው ዓለምም ጭምር ይወሰዳል። በክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ መንግሥት ምልክቶችና ታምራቶች ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ይሆናሉ። በሀሰተኛው ነቢይ እጅ አደገኛ የማታለያ መሣሪያዎች ይሆናሉ።

## ፀረ ክርስቶስ ለክብሩ «ሰዎች ምልክትን እንዲቀበሉ ያስገድዳል»

በኃጢአት የወደቀው ሰው ሁልጊዜ የሚያመልከውን ምስል ይፈጥራል (ይሠራል)። ብሉይ ኪዳን ብዙ ሰዎች እራሳቸው ለሰሯቸው ምስሎች እንደ ሰገዱ ይናገራል። በፀረ ክርስቶስ መንግሥትም በከፍተኛ ደረጃ የዚህ ዓይነቱን የጣዖት አምልኮት የሚለማመዱ ይሆናሉ። ከምልክቶቹና ከታምራቶቹ ጎን ሌላ ሰይጣናዊ የሆነ ሁለተኛ ኃይል የሚሔድ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን «የአውሬው ምስል» በማለት ይገልጸዋል።

## የአውሬው ምስል

*«በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሳ በምድር የሚኖሩትን ያስታል፣ የሰይፍም ቁስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደረጉ በምድር የኖሩትን ይናገራል» (ራዕ.13:14)።*

ቀደም ብለን እንዳየነው ሐሰተኛው ነቢይ ከሚያደርጋቸው ምልክቶችና ታምራቶች የተነሳ በተሰጠውና በሕዝብ ዘንድ በተመሰከረለት ሥልጣኑ ለፀረ ክርስቶስ ዓለም አቀፍ ስግደት (አምልኮ እንዲደረግ) ይጠይቃል። ይህን እያደረጉ ሰዎች ሁሉ ለፀረ ክርስቶስ ምስልን እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋል። ሰዎች ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተለያዩ መንገዶች ሲተረጉሙ ይችላሉ። ስለምስሉቹ ቀጥሎ ያሉትን ሁለት ታሪካዊ ገፅታዎች እንመለከታለን። አንደኛ፡ በንጉሡ ናቡከደነጾር ሕልም የባቢሎን የመጀመሪያው የዓለም መንግስት በትልቅ ምስል መጀመሩ አስደናቂ የሆነ ነገር ነው። ይህን ቀደም ባለው ምዕራፍ ተመልክተናል። *«አንተ ንጉሥ ሆይ! ታላቅ ምስል አየህ፣ ይህም ምስል ታላቅና ብልጭልጭታው የበዛ ነበር በፊትህም ቆሞ ነበረ። መልኩም ግሩም ነበር» (ዳን.2:31)።*

አሁን በመጨረሻዎቹ ቀናት በፀረ ክርስቶስ መንግስት ሰዎች ቁስሉ ስተፈወሰው ለአውሬው ክብር ምስልን እንደሚሠሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (*ራዕ.13:14*)፡ እንደምናውቀው ሁሉ ሀሰተኛው ነቢይ ሰዎች ለፀረ ክርስቶስ ምስል እንዲያደርጉ ያስገድዳል። ለዚህ ጣዖት ለሆነ ምስል የማይሰግዱት ደግሞ ይገደላሉ። ይህ ልክ ከ2600 ዓመታት በፊት ናቡከደነጸር ያደረገውን ይመስላል። እርሱ የፀረ ክርስቶስ አመልካች እንደ መሆኑ መጠን ከሥሩ የሚገዙትን «እርሱ (ናቡከደነጸር) ላቆመው ምስል» እንዲሰግዱ ጠይቋል (*ዳን.3:5*)፡

በማቴዎስ ወንጌል ጌታ ኢየሱስ ከታላቁ መከራ ጋር በተያያዘ «የጥፋት ርኩሰት» በተቀደሰው ስፍራ ስለመቆሙ ተናግሯል (*ማቴ.24:15*)፡ ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን ነቢዩ ዳንኤል በቤተ መቅደስ ስለሚቆመው «የጥፋት ርኩሰት» ተናግሯል (*ዳን.9:27*)፡ ይህም ማለት «በተቀደሰው ስፍራ (በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ) የፀረ ክርስቶስን ምስል እንደሚከተል ያሳያል። አስደንጋጭ የሆነም ጣዖታዊ ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል። ከዚህ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ጋር በተያያዘ አስከፊ የሆነ ክፉ ነገር ይደረጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ፡-

*«የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳን ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው»ይላል ራዕይ.13:15።*

ታላላቅ ሰይጣናዊ ኃይላት ይህን በድን የሆነውን ምስል *ሕይወት* እንዲኖረው ያደርጉታል። ምስሉ መናገር ይጀምርና ስምስሉ ላሰመስገድ አሻፈረኝ የሚሉትን ሰዎች እንዲገደሉ ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ ሰይጣን አጥፊ የሆነውን ሥራውን ወደ ፍፃሜ ያደርሳል (ያመጣል)» ሰዎችን ወደ አጠቃላይ ጥፋቱ እንዲገቡ ያስገድዳል። የዚህ «የአውሬው ምስል» ፍቺ በትክክለኛ ቃል «የጥፋቱ ርኩሰት» ይባላል።

ሁለተኛ፡ በዚህ ክፍል ሌላ ሊታይ የሚገባውን ትልቅ ነገር እናገኛለን። በምንኖርባቸው በመጨረሻዎቹ ቀናት ብዙ ምስሎች ከቀን ወደ ቀን እያጥለቀለቁን ናቸው። እነዚህ ምስሎች ወደ ፊት በተራመደው ቴክኖሎጂ አትመት፣ ፊልሞች፣ ቴሌቪዥንና ቪድዮ ኢንዲስትሪዎች የሚፈጠሩ ናቸው። እነዚህ ምስሎች በአሁኑ ጊዜ በኃጢአት የተሞሉትን የሰዎችን ፍላጎቶች የሚያረኩ ናቸው። በእነዚህ መጠን ብዙ ምስሎች በመረዳት (በመደገፍ) የሰው ዘር በዚህ ምድርና በማይታየው ዓለም





ባለው ሕይወት ላይ ትኩረት ማድረግ ይችላል። ውጤቱም የሰው ዘር በልቡ ለተከላቸው ምስሎች የሚገዛና በቁጥጥራቸው ሥር የሚሆኑ ነው። በበለጠ የሰው ዘር በማየት ስለሚመራ የማመኑ ነገር ያነሰ ይሆንበታል። ማየት ሰውን በሚታየው፣ በአመጻና በሚያልፍ ነገር ላይ እንዲቆራኝ ያደርገዋል። እምነት (ማየት ሳይሆን) ሰውን ወደ ዘላለሙና ወደማይጠፋው ህይወት ይመራዋል (*2ቆሮ.5:7፣ ዮሐ.20:29)*። ፀረ ክርስቶስ መላውን የሰው ዘርን ለማሳት እንዲቻለው የዜና ማሰራጫዎችን ዘመናዊ ምስሎችን መጠቀሚያ ለማድረግ የመያዝ ችሎታ አለው። በተለይም ቴሌቪዥን በዘመናዊ ሳተላይት ቴክኖሎጂ በመደገፍ የክርስቶስን ተቃዋሚ በመላ ዓለም በማንኛውም ቤትና መኖሪያ ሥፍራ በአንድ ጊዜ እንዲገኝ ያደርገዋል። በዚህ ገለጻ ቴሌቪዥን ሰዎች ሁሉ በቁጥጥሩ ስር የሚገቡለት «የሚናገር ምስል» ይሆናል ማለት ነው። በቀላል መንገድ ፀረ ክርስቶስ «መንፈሱን» በሰዎች ልብና ቤት ለማስገባት ያስችለዋል ማለት ነው። ለይጣናዊ በሆነ ኃይል ፀረ ክርስቶስ የሰውን ዘር ከእርሱ ሊርቁ ወይም ሊቃወሙት በማይችሉበት ሁኔታ በታላቅና በአስደናቂ ኃይል ይይዛቸዋል። እነርሱም እርሱ የጠየቀውን አምልኮና ስግደት ይሰጡታል።

## «ሰዎች ሁሉ ምልክት እንዲቀበሉ ያስገድዳል»

ባለንበት ዘመን አማኞችም ሆኑ ከሃዲያን (የማያምኑ) በይበልጥ እየተደነቁ ናቸው። በፍጥነት እያደገ ባለው ቴክኖሎጂ በተለይም በኮምፒዩተርና በኤሌክትሮኒክ በሚለሩት ኢንድስትሪዎች፣ የሰው ልጅ በመጽሐፍ ቅዱስ ፀረ ክርስቶስ ብሎ ወደሚጠራው እየተፋጠኑ በመድረስ ላይ ነው። (*ራዕ.11-19*) የሰው ዘር በሙሉ በዚህ ተቃዋሚ በቁጥጥር ስር እንደሚሆን ይገልጻል። በምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች በሀሰተኛው ነቢይ (ሀሰተኛው የሰይጣን ስብዕና) አማካኝነት ፀረ ክርስቶስን ያከብሩታል፣ ሰይጣንን ያመልካሉ፣ ለአውሬው ምስል እዲሰግዱ ይገደዳሉ (*ራዕ.13:1-18*)፡

የፀረ ክርስቶስ መንግስት (በአንድ መሪ ስር የሆነ አገዛዝ)፣ ሰዎች በቁጥጥሩ ስር የሚውሉበት አገዛዝ ብቻ ሳይሆን ባሪያም የሚደረጉበት ነው። ሀሰተኛው ነቢይ ሰዎችን ለፀረ ክርስቶስ ተገዢዎች ለማድረግ ለማታለል የሚያስችለውን የመጨረሻውን ስልት በመጠቀም ለማንኛውም ሕዝብ ግልጽ የሆነውን *መሣሪያ* ይጠቀማል። *መጽሐፍ* ቅዱስ ይህን ሰይጣናዊ *መሣሪያ* «የአውሬው ምልክት» በማለት ይገልጸዋል።

## የአውሬው ምልክት

*«ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግንባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፣ የአውሬው ስም ወይም የስሙ ቁጥር ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው፣ ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና፣ ቁጥሩም በድበት መቶ በድሳ ስድስት ነው» (ራዕ.13:16-18)።*

በአሁኑ ቀናት ያለ ቁጥር የሚሰራ ነገር እንደሌለ ግልጽ ነው። ሰዎች በማንኛውም ቦታ በባንክ ቢሆን፣ በኢንሹራንስ ኩባንያ፣ በመንግስታዊ ቢሮዎች በመጋዚኖች፣ በሱቆች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በዩኒቨርስቲዎች ወይም በማንኛውም ሕዝባዊ ድርጅቶች ቁጥር ተሰጥቷቸው ወይም የኮምፒዩተር ኮድ የተሰጣቸው (የተመዘገቡ) ናቸው። የዚህ ምዝገባ አሰራር ለብዙዎች ሊገለጽ የማይቻል ምስጢራዊ ስሜትን ያሳድርባቸዋል። በአሁኑ ጊዜ የዚህ ምዝገባ ስፋት ከግለሰብ ቁጥጥር ባሻገር አልፎ ሄዷል። በአሁኑ ቀናት ስለ እርሱ ማንነትና ሁኔታ በኮምፒዩተር ተመዝግቦ የት እንደሚገኝ እውነተኛ ሊሆን የሚችል የለም። ሰዎችን በታላላቅ መንግስትና ኩባንያ መመዝገብ (በተጨማሪ ሁኔታን በሚመዘግቡ የዕርዳታ ማዕከላት) በዓለም አቀፍ አንዱን ከሌላው ጋር ለማያያዝ የሚቻልበት ዘዴ አሁን ግልጥ እየሆነ ነው። በክልላዊ ድንበሮች ሳይወሰኑ በማንኛውም ሁኔታ ስር ኢንፎርሜሽንን (ሀሳብን) ለመለዋወጥ የሚቻል ሆኗል። ያልተገለጡ (በሀሳብ ያሉ) ፖለቲካዊና ሕዝባዊ ሥርዓቶች ተሰውረው አይቀሩም። በዚህ ምትክ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተገለጡ (እውን የሆኑ) ይሆናሉ። በአጭሩ እንደምንመለከተው የቴክኖሎጂ እድገት ለፀረ ክርስቶስ ዓለምን በሙሉ ባርያና በቁጥጥሩ ስር ሊያደርግ የሚችልበትን መሣርያ እየሰጠው ነው። እንደ (*ራዕ.13:16*) በፀረ ክርስቶስ አገዛዝ ዘመን ሀሰተኛው ነቢይ ማንኛውንም ሰው በእጁ ወይም በግንባሩ ምልክት እንዲቀበል ያስገድዳል። ያለዚህ ምልክት ማንኛውም ግለሰብ ሊገዛም ሆነ ሊሸጥ አይችልም (*ራዕ.13:17*)። ይህም ማለት ከማንኛውም ለሕይወት ከሚያስፈልገው ነገር የተወገደ ይሆናል ማለት ነው። የገንዘብ፣ የምግብ፣ የልብስ፣ የህክምናና ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን መብቶች ከማጣት የተነሳ ለመቃወምም ሆነ ጭቆናዊ ከሆነው አገዛዙ ማምለጥ አይቻልም። ስለሆነም በመጨረሻ አብዛኛውን ሕዝብ በመስማማትና በመከተል ሕዝቡ የአውሬውን ምልክት ይቀበላል። በቴክኒካዊ





አሰራር የማይታይ ኮምፒውተራዊ «ምልክት» መቀበል በሰው ቆዳ ላይ ቴክኒካዊና ልምምዳዊ ጉዳይ ያለው ብቻ ሳይሆን ከዚህ በበለጠ ሁኔታ

*የአውሬው ምልክት ፍቺ ምንድን ነው?*

ብለን እንድንጠይቅ ያስገድደናል «የአውሬው ምልክት» የፀረ ክርስቶስ ምልክት ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ «ምልክቱ» «የአውሬውን ስም ወይም የስሙን ቁጥር» የያዘ ነው(*ራዕ.13:17*)።ለዚህ መሪ ራሳቸውን በሰጡ ሰዎች የሚደረግ ነው።

የዚህ ምልክት ፍቺ በእጅና በግንባር ላይ ከሚታየው ምልክት ባሻገር የላቀ ነገር አለው። ከዚህ ከሚታየው *ሥራ* በስተኋላ አስፈሪና የማይታይ እውነታ ይከናወንበታል። ይህንን ምልክት መቀበል ማለት ራስን ለዲያብሎስ በመስጠት በሰይጣናዊ ማህተም መታተም ማለት ነው። ይህ አሠራር ዳግም ለተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ ቅዱስ የመታተሙ ተቃራኒ የሆነ አሠራር ነው (*ኤፌ.1:13፣ 2ቆሮ.1:22*)። ለው ይህን ምልክት በመቀበል ዘላለማዊ የሆነ ጥፋቱን ያትማል።

*«ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፣ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግንባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ካዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል። በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያል። የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል። ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ፣ የስሙንም ምልክት የሚቀበሉ ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም» ተብሎ ተጽፏል። (በራዕይ.14:9-11)*

የአውሬውን ምልክት የሚቀበሉ ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ለፀረ ክርስቶስና ለሰይጣን ግልጽ የሆነ የመጨረሻ ውሳኔያቸውን መስጠታቸውንና በግልጽ እርሱን በማምለክ ማክበራቸውን ያሳያሉ። ለዘላለምም ከእውነተኛው አምላክና አዳኝ የተለዩና የጠፉ ይሆናሉ።

*የ666 ፍቺ ምንድን ነው?*

666ትን በተመለከተ ብዙ ዓይነት አመለካከቶችና ግምቶች አሉ። ሆኖም ግን ስለ 666 የተሰጡትን ግምታዊ ሀሳቦች ወደ ጐን በመተው በግልፅ በተጻፈው ላይ እናተኩራለን። (ራዕ. 13:17) ይህ ቁጥር ስለ ስሙ ቁጥር የሚናገር መሆኑን እርግጠኛ ነን። የፀረ ክርስቶስ ስም በዚህ ቁጥር ውስጥ የተሰወረና (ምስጢር) የሆነ

ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዕብራውያን፣ በግሪክና በላቲን ስሞች በቁጥር የሚገለጡ ናቸው፣ ምክንያቱም የእነዚህ ቋንቋዎች ፊደላት ቁጥር አላቸው፡፡ ለምሳሌ በግሪክና በዕብራውያን ቋንቋ አልፋ /አሌፍ=1፣ ቤታ/ ቤት=2፣ ጋማ /ጋሜል=3፣ ኤዴልታ/ ዳሌጥ=4 ወ.ዘ.ተ. በማለት ፊደላት በቁጥር ይለየማሉ፡፡ ስለዚህም የግሪክና የዕብራውያን ፊደላት በሙሉ የቁጥር ስያሜ አላቸው በላቲን ጥቂት ፊደላት ብቻ ናቸው የቁጥር ስያሜ ያላቸው፡፡ I=አንድ II=ሁለት፣ III=ሦስት፣ IV=አራት፣ V=አምስት፣ X=አስር፣ XX=ሀያ፣ L=ሀምሳ፣ C=መቶ፣ D=አምስት መቶ፣ M=አንድ ሺህ ፡፡ ሌሎቹ ቁጥሮች ከእነዚህ ቁጥሮች የሚወስዱ ናቸው፡፡ የሚቀጥለው ምሳሌ ይህን ያሳየናል፡፡ ከተሐድሶ በፊት እንደ ነበሩት እንደ ፒተር ዋልዱስ፣ ጆን ዊክሊፍ፣ ጃን ሁስ፣ ተሐድሶ ካደረጉ ከማርቲን ሉተር፣ ከሁልድርቺ ዝዊንግሊ፣ ከጆን ካሊቪን ጋር የሮሙ ጳጳስ ፀረ ክርስቶስ ነው በማለት ገምተው ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች በሶስት ደረጃ ከተሠራው ከጳጳሱ ዘውድ (ቲአራ) ላይ የተጻፈውን **VICARIUS FILII DEI** (የእግዚአብሔር ልጅ ምትክ) የሚለውን ማዕረግ በመውሰድ 666 ቁጥርን ይተረጉሙታል፡፡ **VICARIUS FILII DEI** (ቪካሪዩስ ፊሊ ዲያ) ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ተወካይ ማለት ነው፡፡ የላቲኑን ፊደል በመውሰድና ለፊደላቱ የተሰጡትን ቁጥሮች በአንድ ላይ ሲደመሩ ውጤቱ 666 ይሆናል፡፡

**V I C AR I V S F I L I I D E I**

↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓ ↓

**5 + 1 +100 + 1+5 + 1 +50+ 1+ 1 + 500+ 1=666**

ይህን ምሳሌ ቁጥሩ እንዴት ከፊደላት ቁጥር ድማሬ እንደሚመጣ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም አንድን ቁጥር ወደ ስም ለመተርጎም የሚቻለው በመጀመሪያ ስሙ የሚታወቅ ሲሆን ነው፡፡ በፀረ ክርስቶስ ነገር ላይ ግን ስሙን በቅድሚያ ያወቀ ስለሌለ 666 የሚለውን ቁጥር በስሙ ትርጉም ለመፍታት አይቻልም፡፡ ፀረ ክርስቶስ አንድ ቀን በሚጣልበት ጊዜ ግን አንጎል ያላቸው (አእምሮ ያላቸው) ይህን ቁጥር ለመተርጎም ይተጋሉ(*ራዕ.13:18*)፡፡

በዚያን ቀን በፀረ ክርስቶስ መንግስት ቁጥሩ ታላቅ ሰይጣናዊ መግለጫ (መለያ) የሆነ ታላቅ ፍቺ እንዳለው ይታወቃል፡፡ ሰይጣን ዓለምንና፣ ሰዎችን በሙሉ ለመቆጣጠር የእያንዳንዱን ሰው ልብ ለመያዝ ይፈልጋል፡፡ ይህም ግልጽ የሆነና





የታወቀ ነገር ነው፡፡ በሙሉ መገዛት ባለበት ቦታ «ሰዎች በሰይጣን ተይዘዋል» ለማለት እንችላለን፡፡ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት የሆነ አስደንጋጭ (አስፈሪ) እውነታ ነው፡፡ ሰይጣን በሂደት የሰዎችን ስብዕና በማጥፋት የሰውን ዘር በእርሱ ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ ያስገድዳል፡፡ በዚህ ምክንያት እያንዳንዱ ግለሰብ ወደ ምንምነት ይዘቅጣል፡፡ በመጨረሻም ግለሰብነት የሌለው በህዝብ መንከል አንድ ቁጥር ሆኖ ይገኛል፡፡ ግለሰቡ እንደ ተሳቢ ፍጥረት (እንስሳ) ለፀረ ክርስቶስ ባርያና ተገዢ ይሆናል፡፡ በዚያም ሰይጣን የመጨረሻ ግቡን ያከናውናል፡፡ማንኛውም የዚህ አባል የሆነ ያለ ጥርጥር ሰይጣንን ያመልካል፡፡ጥልቅ የሆነው የ666 ቁጥር ፍቺ ይህ ነው፡፡

## ፀረ ክርስቶስ ላይ የሚካሔደው ፍርድ

ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን በፀረ ክርስቶስና በመንግስቱ ላይ ስለሚወሰደው ፍርድ ቀደም ብለው ተናግረዋል፡፡ በትንቢተ ዳንኤል በተወሰነው ጊዜ ፍጻሜ እንደሚሆን ይናገራል (*ዳን.9:24*)፡ ስለዚህ ትኩረት ሰጥተን ስንመረምር ይህ ፍርድ በሁለት ክፍል የተከፈለ ይሆናል፡፡

1. የፀረ ክርስቶስ መንግስት ፍርድና
2. የፀረ ክርስቶስ የሃሰተኛው ነቢይ ፍርድ

## 1. የፀረ ክርስቶስ መንግስት ፍርድ

ለማስታወስ ያህል የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነጾር የሰው ገጽታ ያለውና ለማየት አስፈሪ የሆነ ምስል ማየቱን ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ የዚህ ምስል ራስ ወርቅ፣ ደረትና ክንዶቹ ብር፣ ወገቡና ጭኖቹ ነሐስ፣ እግሮቹ ብረትና የእግሮቹም ጣቶች ብረትና ሸክላ ነበሩ (*ዳን.2:31-33*)፡ መጽሐፍ ቅዱስ

*«እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሉ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ፡፡ የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፣ ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት ተፈጨ ፡፡ በመከርም ጊዜ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ፣ ነፋስም ወሰደው፣ ቦታውም አልታወቀም፣ ምስሉንም የመታ ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ፣ምድርንም ፈጽሞ ሞላ»ይላል (ዳን.2:34-35)፡፡*

ቀደም ባለው ምዕራፍ የናቡከደነጾር ሕልም ምስል በዚህ ምድር ላይ አምላክ የለሽ (አመጸኛ) የሆነውን የሰውን አገዛዝ እንደሚያመለክት ግልጽ

ተደርጓል:: በእነዚህ ቀናት አራት በወርቅ፣ በብር፣ በነሐስና በብረት የተመሰሉ ታላላቅ የዓለም መንግስታት እንደሚነሱ ተነግሯል:: በእነዚህ መንግስታት እግዚአብሔር ሳይሆን ማዕከሉን የያዘ ሰው ነበር:: እነዚህ አራቱ መንግስታት በጊዜያቸው መጥተው ሄደዋል (አልፈዋል):: በመጨረሻዎቹ ቀናት እንደገና በፀረ ክርስቶስ መንግስት ይገሰጣሉ (*2ተሰ.2:3*):: በምድር ላይ የሰው የአመጸኝነት ጽዋ የተሞላ ይሆናል:: ይህ መንግስትና ከእርሱ በፊት የነበሩት መንግስታት ጭምር በጌታ እየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት የሚፈረድባቸውና የሚጠፉ ይሆናሉ (ዳን. 2:24 ፣35)::



**የፀረ ክርስቶስ ፍርድ በዳንኤል አገላለፅ**

«ከዚህም በኋላ ዳንኤል ንጉሡ የባቢሎንን ጠቢባን ያጠፋ ዘንድ ወዳዘዘው ወደ አርዮክ ገባ በገባም ጊዜ:- የባቢሎንን ጠቢባን አታጥፋ፤ ወደ ንጉሡ አስገባኝ እኔም ፍቺውን አሳያለሁ አለው (ዳን 2:24)»::

«ድንጋዩም እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሉ ብረቱንና ናሱን ሸክላውንና ብሩን ወርቁንም ሲፈጨው እንደየህ እንዲሁ ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ታላቁ አምላክ ለንጉሱ አስታውቆታል፤ ሕልሙም እውነተኛ ፈቺውም የታመነ ነው» (ዳን.2:35)

ትንቢት የተነገረለት «ድንጋይ» በሰው የተመሰለውን ምስል እግሮች መታና ምስሉን ያጠፋዋል (ይደመስስዋል):: ይህም ማለት በምድር ላይ የመጨረሻው መንግስት በሆነው በፀረ ክርስቶስ መንግስት በመጀመር አስቀድመው የነበሩትን ሌሎችን መንግስታት ጭምር መታሰቢያ እስከማይገኝላቸው ድረስ ክርስቶስ ፈጽሞ ይደመስሳቸዋል ማለት ነው:: (ዳን. 2:35) በእነርሱ ቦታ «የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስና ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር መንግስት ይመሠርታል» (*ዳን.2:44*):: ይህ የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግስቱንና ግዛቱን ለመመስረት «በኃይልና በክብር» ሆኖ ሲመጣ ነው (*ማቴ.24:30*):: «የማንም እጅ» ሳይነካው (የሰው እጅ





ሳይረዳው የሚመጣው ድንጋይ) (ዳን2:39) ከእግዚአብሔር ልጅ ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመሰክረው ሁሉን ቻይ አምላክ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሆነችውን አዲሷን ፍጥረት የመሠረተበት የማዕዘን ድንጋይ ነው:: (*መዝ.(118):22፤ ኢሳ.28:16፤ ማቴ.21:42-44፤ ኤፌ.2:20፤ ሮሜ.9:33፣ 1ጴጥ.2:6*)::

በዚህ ዓለት (ድንጋይ) በክርስቶስ ኢየሱስ የማያምን ሁሉ በማዕዘኑ ድንጋይ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጨ ይሆናል:: ያለ እግዚአብሔርና ያለ ክርስቶስ ኢየሱስ ይገዙ የነበሩት መንግስታት በሙሉ በተመሳሳይ ሁኔታ ይጠፋሉ:: አራቱ የዓለም መንግስታት ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም ከብዙ ጊዜ በፊት ወድቀዋል (ጠፍተዋል):: ነገር ግን የእነዚህ መንግስታት መንፈስና ሰይጣናዊ ኃይል በዓመጸኛው ሕዝብ ውስጥ ገብተው በመስራት የቀጠሉ ናቸው:: በአሁኑ ቀናት የግሪክና የሮማውያን ባሕሎችና ቋንቋዎች ዘመናዊውን የአውሮፓን አህጉር ምን ያህል እንደሳቡት መገመት ይቻላል:: በአንጻሩ የዘመኑ የአውሮፓ ሕዝብ ወንጌልንና የክርስቶስን ማዳን እንደሚቃወሙ ገምቱ:: ይህም የሆነበት ምክንያት በአስመሳዩና በፀረ ክርስቶስ መንፈስ ተማርከው በመወሰዳቸው ነው:: ይኸውም መንፈስ የአሁኗን የእስራኤልን መንግስት ከሚቃወሙት በስተ ጀርባ ሆኖ የሚያስተላልፈው ዜና መሠረት የሌለውና ሀሰት ነው:: ወቅታዊው የሕብረተሰብ ሁኔታና ሀሳቦች እስራኤልን በመቃወም እየጨመሩ ናቸው:: በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔር የፍርድ ድንጋይ አመጸኛ የሆኑትን የሰው ዘር መንግስታት በሙሉ ይደመስሳቸውል:: በፍጻሜም ዘላለማዊ መዋጀትን በቀራንዮ መስቀል ላይ የፈጸመው አዳኙ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ደህንነት በተቃወሙትና በምትኩ ፀረ ክርስቶስና መንግስቱን በመረጡት ሁሉ ላይ ፈራጅ ሆኖ ይገለጣል::

## 2. የፀረ ክርስቶስና የሀሰተኛው ነቢይ ፍርድ

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛውም ነቢይ የሚፈረድባቸው ይሆናል:: ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ
*«አውሬውም ተያዘ በእርሱም ፊት ተአምራትን እያደረገ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትን ለምስሉም የሰገዱትንም ያሳተ ሐሰተኛው ነቢይ ከእርሱ ጋር ተያዘ ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ» ይላል (ራዕ.19:20)::*

ከእግዚአብሔር ልጅ ከጌታ ኢየሱስ በቀር «ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን ወይን መጥመቂያ» የሚረግጥ የለም (*ራዕ.19:15*): አመጸኝነት በፀረ

ክርስቶስ ጽዋውን ከሞላ በኋላ ቅዱስና ትክክለኛ የሆነውን ፍርድ ይቀበላል:: ፀረ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ ኃጢአት ነው:: ይህም ማለት በእርሱ የኃጢአትና የአመጸኝነት ጽዋ የሞላበት ነው ማለት ነው:: ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያለውን የሰይጣንን አገዛዝ «በአፉ መንፈስ» በማጥፋት ወደ ፍፃሜ የሚያመጣው *(2ተሰ.2:8)*::

ሀሰተኛው ነቢይ ፀረ ክርስቶስ የተቀበለውን ስቃይ በተመሳሳይ ሁኔታ ይቀበላል:: እንደ ሃይማኖት መሪ የዓለም መሪ የሆነውን ፀረ ክርስቶስን በዓለም ሰዎች ፊት ከፍ በማድረግ አክብሮታል:: የዓለምን ሰዎች ለዚህ ዓለማዊ መሪና ለስዕሉ እንዲሰግዱ ከማሳቱም በላይ የሰይጣን ማህተም የሆነውን ምልክቱን በእጃቸውና በግንባራቸው እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል:: ስለሆነም በፍጻሜው ፀረ ክርስቶስ የሚቀበለውን ፍርድ ይቀበላል:: «ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል የእሳት ባሕር» ይጣላሉ:: *(ራዕ.19:20)* ሁለቱም በሰይጣን ሥልጣን ሰርተዋል:: *(ራዕ.13:2-4)* ሁለቱም አንድ ላይ ይፈረድባቸዋል:: ከሺህ ዓመት በኋላ ሰይጣን ወደዚያ ወደ እሳቱ ባሕር ይከተላቸዋል:: ሰይጣን የተፈረደበት ስለሆነ ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ይጣላል:: *(ራዕ.20:10)*

ፀረ ክርስቶስና መንግስቱን በተመለከተ በእነዚህ አስተያየቶች ማጠቃለያ ላይ የሚከተለው ቻርት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና በፀረ ክርስቶስ መካከል ያለው ንጽጽር የሚያሳይ ይሆናል:: ይህ ንጽጽር በእርግጥ የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ ፣ የክርስቶስን ቦታ ለመያዝና ለመወከል የሚጥር አስመሳይ ክርስቶስ እንደሆነ ያሳያል::

| [illegible] | ፀረ ክርስቶስ |
|---|---|
| (ማር.1:1) | (1ዮሐ.2:22) |
| 1. ኢየሱስ ክርስቶስ ስልጣን ሁሉ ከሰማይ አባቱ ተሰጥቶታል:: (ዮሐ.3:35) | 1 ሥልጣንና ኃይል ሁሉ ከሰይጣን አለው:: (ራዕ.13:2) |
| 2. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ፣ከክብር፣ ከላይ መጥቷል:: (ዮሐ.3:31) | 2. ፀረ ክርስቶስ ከታች ከጥልቁ ከሰይጣን ይመጣል:: (ራዕ.17:8) |
| 3. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ በመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል:: (ሉቃ.1:35) | 3. ፀረ ክርስቶስ በሰይጣናዊ ኃይል ይመጣል:: |
| 4. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ ስምባክና ነው:: (1ጢሞ.3:16) | 4. ስሥጋ የተገለጠ ሰይጣናዊ ነው:: |
| 5. ኢየሱስ ክርስቶስ ስባቱን ብቻ ያከብራል:: (ዮሐ.17:4) | 5. ፀረ ክርስቶስ ሰይጣንን ያከብራል ለሰይጣንም ይናራል:: (ራዕ.13:1-10) |
| 6. ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የአባቱን ፈቃድ ይፈጽማል:: (ዮሐ.17:4) | 6. ፀረ ክርስቶስ አጥሬ የሆነውን የሰይጣንን ሥራ ይፈጽማል:: (ራዕ.13:1-10) |
| 7. ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባቱ ክብር መስጠት ብዙ | 7. ፀረ ክርስቶስ ለሰይጣን ክብርን |






| | |
|---|---|
| ተዓምራትን በምድር ላይ ሰደርጓል:: (ዮሐ.9:4) | በመስጠት ብዙ ሐሰተኛ ምልክቶችን ያደርጋል (2ተሰ.2:10):: |
| 8. ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ወደ ሰማያዊ አባቱ ዕውነት ይመራል (ዮሐ.14:6):: | 8. ፀረ ክርስቶስ ሰዎችን ወደ አመጽ ይመራል:: (2ተሰ.2:10) |
| 9. ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሰዎችን ይዋጃል ያድናል (ማር.10:45) | 9. ፀረ ክርስቶስ ሰዎችን ወደ ጥፋት ይስባል:: (2ተሰ.2:10) |
| 10. ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን አዋረደ፣ የባርያን መልክ ያዘ:: (ፊል.2:5-8) | 10. ፀረ ክርስቶስ ራሱን እግዚአብሔርን ከሚያመልኩት በላይ ከፍ ከፍ ያደርጋል (2ተሰ.2:4) |
| 11. ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ሊባርክ ይመጣል (ሉቃ.19:10):: | 11. ፀረ ክርስቶስ መነሳት የሚያምኑትንም ስማያምኑትም ፍርድ ነው:: (2ተሰ.2:4) |
| 12. ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ሰማያዊ አባቱን እንዲያመልኩ ያስተምራል:: *(ዮሐ.4:24)* | 12. ፀረ ክርስቶስ ሰዎችን ለሰይጣን እንዲሰግዱ ያስገድዳል:: *(ራዕ.13:4)* |
| 13.ኢየሱስ ክርስቶስ ትሁት የሆነና አባቱን የሚያከብር ነው::*(ኢሳ.42:2፣ ዮሐ.8:49)* | 13 ፀረ ክርስቶስ ታላቅ ነገር የሚናገርና ትዕቢተኛ እግዚአብሔርን የሚሳደብ ነው::*(ራዕይ.13:5-6)* |
| 14. ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱ ምሳሌ ነው:: *(ዕብ.1:3፣ ቆላ.1:15፣ ዮሐ.14:9)* | 14. ፀረ ክርስቶስ የሰይጣን ምሳሌ ነው:: *(ራዕ.12:3፤ 13:1-2)* |
| 15. ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ኃጢአት የሌለበት ፍጹም ሰው ነው:: *(ሮሜ.9:5፣ 2ቆሮ.5:21)* | 15. ፀረ ክርስቶስ ፍጹም ሰይጣንና የአመጽ ሰው ነው:: *(2ተሰ.2:3)* |
| 16. ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያዊ አባቱ ስም መጣ:: *(ዮሐ. 5:43)* | 16. ፀረ ክርስቶስ በራሱ ስም ይመጣል:: *(ዮሐ.5:43)* |
| 17. ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማያዊ አባቱ ባሕርይ አለው:: *ዕብ.1:3* | 17. ፀረ ክርስቶስ ሰይጣናዊ ባሕርይ አለው:: *2ተሰ.2:3* |
| 18. ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠ እግዚአብሔር ፍቅር ነው:: *(1ዮሐ.4:9)* | 18. ፀረ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የሚቃወም፣ የአመፅ ልጅ የእግዚአብሔር ጠላትና የአመፅ ሰው ነው*(2ተሰ.2:3-8)*:: |
| 19. ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ህግ ፈጻሚ::*(ማቴ.5:17፣ሮሜ.10:4)* | 19. ፀረ ክርስቶስ በባሕርዩ አመጸኛ ነው *(2ተሰ.2:3-9፤ዳን.7:25)* |
| 20.ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የመምሰል ሚስጥር ነው:: *(1ጢሞ.3:16፤ ማቴ.11:27)* | 20. ፀረ ክርስቶስ የዓመፅ ሚስጢር ነው:: *(2ተሰ. 2:7)* |
| 21. ኢየሱስ ክርስቶስ ራስን ዝቅ የማድረግን መንገድ ተከትሏል *(ፊል.2:5-8)* | 21. ፀረ ክርስቶስ ራስን ከፍ የማድረግ መንገድ ይከተላል:: *(ራዕ.17:8)* |
| 22. ኢየሱስ ክርስቶስ በትህትናው በአባቱ ከፍ ከፍ ተደርጓል:: *(ፊል.2:9-11)* | 22. ፀረ ክርስቶስ ጥልቅ ወደ ሆነው ጥፋት ይጣላል::*(ራዕ.17:8፣19:20-21)* |
| 23. ኢየሱስ በክብር የተነሳና ለአንዴና ለመጨረሻ ሞትን ድል ያደረገ ነው *(1ቆሮ.15:20፤ ዕብ.2.14)*:: | 23. ፀረ ክርስቶስ ትንሳኤን ቅጂ ያደርጋል (የሞት ቁስል መፈወስ) *(ራዕ. 13:3-14)*:: |
| 24. ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ክብሯል (ይከብራል) *(ዮሐ.16:14)* | 24. ፀረ ክርስቶስ በሀሰተኛው ነቢይ ይከብራል:: *(ራዕ.13.11-18)* |
| 25. ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ በሰማይና በምድ ይገዛል፣ ያስተዳድራል:: *(ራዕ.11:15፣22:1-5)* | 25.ፀረክርስቶስ የሚፈረድበት፣የሚጠፋና ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የሚኮነን ነው::*(ራዕ.19:20፣20:10)* |

# የጎግና ማጎግ

ወደ ጌታ ኢየሱስ ምጽአት እየቀረብን ስንሄድ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚሆነው ነገር፣ በብሉይ ኪዳን የተነገረ፣ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ከቶ ያልተፈጸመ ሌላ ታሪካዊ ሁኔታ እንመለከታለን:: የነቢዩ *ሕዝ. 38 እና 39* በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚካሄድ ታላቅ ውጊያ ይናገራሉ *(ሕዝ.38:1-16)*:: እጅግ ታላቅ የሆነ ሠራዊት ከእስራኤል በስተ ሰሜን ያሉት በመሰባሰብ የእስራኤልን ሕዝብ ይከብባሉ *(ሕዝ.38:15ብ16)*:: ይህ ቅድስቲቱን ምድር የሚከብበውን ሠራዊት የሚመራው ኃይል «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግ» በመባል ተገልጿል:: *(ሕዝ.38:2)*

ይህን ስመጀመር «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግና የፀረ ክርስቶስ መንግስት» ሁለቱ የተለያዩ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ ትንቢቶች መሆናቸውንና አንዱ ከሌላው የተለዩ መሆኑን ግልጽ ልናደርግ ይገባናል:: በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚነሱ ሁለት የተለያዩ ኃይላት ናቸው:: በማዳን ታሪክ ቻርት ላይ የማጎግ ጎግ ፀረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳና አስቃቂ አገዛዙን የሚጀምር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

1\. ነቢዩ ሕዝቅኤል የማጎግን ጎግ በአምስት የተለያዩ ስሞች ይጠራቸዋል:: ነርሱም ሮሽ፣ ሞሳህ፣ ቶቤል፣ ጎግና ማጎግ ናቸው:: *(ሕዝ.38:1-3)* እነዚህ ስሞች ከእስራኤል በስተሰሜን በኩል ያሉትን የአሕዛብን ግዛቶች ያመለክታሉ:: *(ሕዝ.38:15)*








እንደ ፍላቪዩስ ጆስፉስ የአይሁድ የታሪክ ሰው ገለጻ የማጎግ ትውልዶች ከእስራኤል በስተሰሜን በጥቁር ባሕር አካባቢ የሚኖሩት ናቸው:: (በዘፍ.10:2) የኖህ ልጅ የያፌት ልጆች ማጎግ፣ ቶቤል፣ ሞሳህን ጎሜር ተብለው እንደተጠሩ ተጽፎ ይገኛል:: የስላቪክ ሕዝቦች የማጎግ ቶቤልና የምስህ ትውልዶች ናቸው:: የጀርመን ሕዝብ ግን የጎሜር ትውልድ ናቸው:: ዛሬ እነዚህ ሕዝቦች ሁሉ ከኤሌብና ከዳንዩብ ወንዞች በስተሰሜንና ምስራቅ ባሉት ሀገሮች ውስጥ ይኖራሉ:: ያም ማለት በአውሮፓ በስተ ምስራቅና ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ድንበር ውጪ ናቸው:: ነገር ግን በመጨረሻው ጊዜ የሚነሱትን ሁለት የተለያዩ ታላላቅ ኃይላትን የሚመሠርቱ ናቸው::

2\. የሮሽ፣ የምሳህ፣ የቶቤል፣ የጎግና የማጎግ ስሞች ፍቺ ፀረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳ ሌላ ኃይል እንደሚነሳ የሚገልጹ እውነታ ናቸው:: እንደ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 እና 39 መሠረት ይህ ኃይል በእስራኤል ምድር ውስጥ የሚደመሰስ ነው::

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የሩሲያ ደቡባዊ መንግሥት ከዋናው ከተማ ከኪብ ጋር ሮሽ ተብሎ ይጠራ ነበር:: ትርጉሙም «ዋና አለቃ፣ መጀመሪያ፣ አንደኛ ማለት ነው» (በአዲሱ ዓለም አቀፍ ትርጉም ሐህሞ ግርጌ ሮሽ ዋና አለቃ በመባል ተተርጉሞ ይገኛል:: (ሕዝ. 38:2-3) ሮሽ የሚለው ስም በኋላ ሩሲን እንደተባለና




# የጎግና ማጎግ

ወደ ጌታ ኢየሱስ ምጽአት እየቀረብን ስንሄድ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚሆነው ነገር፣ በብሉይ ኪዳን የተነገረ፣ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ከቶ ያልተፈጸመ ሌላ ታሪካዊ ሁኔታ እንመለከታለን። የነቢዩ ሕዝ. 38 እና 39 በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚካሄድ ታላቅ ውጊያ ይናገራሉ (ሕዝ.38፡1-16)፡፡ እጅግ ታላቅ የሆነ ሠራዊት ከእስራኤል በስተ ሰሜን ያሉት በመሰባሰብ የእስራኤልን ሕዝብ ይከብባሉ (ሕዝ.38፡15-16)፡፡ ይህ ቅድስቲቱን ምድር የሚከብበውን ሠራዊት የሚመራው ኃይል «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግ» በመባል ተገልጿል። (ሕዝ.38፡2)

ይህን ስመጀመር «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግና የፀረ ክርስቶስ መንግስት» ሁለቱ የተለያዩ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ ትንቢቶች መሆናቸውንና አንዱ ከሌላው የተለዩ መሆኑን ግልጽ ልናደርግ ይገባናል። በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚነሱ ሁለት የተለያዩ ኃይላት ናቸው። በማዳን ታሪክ ቻርት ላይ የማጎግ ጎግ ፀረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳና አስቃቂ አገዛዙን የሚጀምር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

1. ነቢዩ ሕዝቅኤል የማጎግን ጎግ በአምስት የተለያዩ ስሞች ይጠራቸዋል። እነርሱም ሮሽ፣ ሞሳህ፣ ቶቤል፣ ጎግና ማጎግ ናቸው። (ሕዝ.38፡1-3) እነዚህ ስሞች ከእስራኤል በስተሰሜን በኩል ያሉትን የአሕዛብን ግዛቶች ያመለክታሉ። (ሕዝ.38፡15)








እንደ ፍላቪዩስ ጆሴፉስ የአይሁድ የታሪክ ሰው ገለጻ የማጎግ ትውልዶች ከእስራኤል በስተሰሜን በጥቁር ባሕር አካባቢ የሚኖሩት ናቸው። (በዘፍ.10፡2) የኖህ ልጅ የያፌት ልጆች ማጎግ፣ ቶቤል፣ ሞሳህን ጎሜር ተብለው እንደተጠሩ ተጽፎ ይገኛል። የስላቪክ ሕዝቦች የማጎግ ቶቤልና የምሳህ ትውልዶች ናቸው። የጀርመን ሕዝብ ግን የጎሜር ትውልድ ናቸው። ዛሬ እነዚህ ሕዝቦች ሁሉ ከኤሴብና ከዳንዩብ ወንዞች በስተሰሜንና ምስራቅ ባሉት ሀገሮች ውስጥ ይኖራሉ። ያም ማለት በአውሮፓ በስተ ምስራቅና ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ድንበር ውጪ ናቸው። ነገር ግን በመጨረሻው ጊዜ የሚነሱትን ሁለት የተለያዩ ታላላቅ ኃይላትን የሚመሠርቱ ናቸው።

2. የሮሽ፣ የምሳህ፣ የቶቤል፣ የጎግና የማጎግ ስሞች ፍቺ ፀረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳ ሌላ ኃይል እንደሚነሳ የሚገልጹ እውነታ ናቸው። እንደ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 እና 39 መሠረት ይህ ኃይል በእስራኤል ምድር ውስጥ የሚደመሰስ ነው።

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የሩሲያ ደቡባዊ መንግሥት ከዋናው ከተማ ከኪቭ ጋር ሮሽ ተብሎ ይጠራ ነበር። ትርጉሙም «ዋና አለቃ፣ መጀመሪያ፣ አንደኛ ማለት ነው» (በአዲሱ ዓለም አቀፍ ትርጉም ሐህሞ ግርጌ ሮሽ ዋና አለቃ በመባል ተተርጉሞ ይገኛል። (ሕዝ. 38፡2-3) ሮሽ የሚለው ስም በኋላ ሩሲን እንደተባለና



ከዚያም ሩሲያ ተብሎ እንደተሰወጠ ይገመታል። የምሳህ ትርጓሜ ደግሞ ሀብት መውረስ (መበዝበዝ፣ መሻት) ማለት ሲሆን መስኮብ የሚለው ስም ከዚህ የተወረሰ እንደሆነ ይታመናል። ቶቤል ማለት «የጦር መሳሪያ ሠሪ» ማለት ነው። ከእርሱ ቶብልሲክ እንደ ወጣ ይገመታል። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ከፍተኛ የጦር ክምችት ያለው በምስራቅ አውሮፓ ነው። ከጎግ (ከፍተኛ፣ ዋና) ካህን፣ ካውክና ካውካሱስ የሚሉት ስሞች ወጥቷል። እንደ አይሁዳዊው የታሪክ ሰው ፍላቪዩስ ጆሰፉስ አባባል የያፌት ዝርያዎች ከካውካሱስ በስተደቡብ እንደ ሰፈሩ ይታወቃል። ማጎግ የሚለው ስም ትርጉም «መስፋት» ወይም «የቤተ ሰብ ፈጥኖ መብዛት» ማለት ነው። ከዚህም የተነሳ የምስራቅ አውሮፓ ሕዝቦች መብዛትን ልናይ እንችላለን። እምስቱ ሮሽ፣ ሞሳህ፣ ቶቤል፣ ጎግና ማጎግ የተባበረውን ሩሲያን እንደሚመሰርቱ እንናገራለን። በዚህም ጎግ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወት ይሆናል። ሩሲያ ከእስራኤል በስተሰሜን ትገኛለች። ኢየሩሳሌምና ሞስኮ በአንድ ሎንግትዩድ (የምድር የሀሳብ መስመር) ላይ ይገኛሉ።

3. የማጎግ ጎግ ከፍተኛ የእስራኤል ጠላቶች ከሆኑት ከአረቦች መንግስታት ጋር ሕብረት ይመሠርታል። እንደ (*ሕዝ.38:5-6*) ወደፊት በቅድስቲቱ ምድር ላይ በሚደረገው ወረራ ብዙ የአረብ መንግስታት እንደሚተባበሩ ለማየት ይቻላል። ፋርሶች ሙሮች፣ ሊቢያውያን፣ ጎሜርና ቶጋርማ ይሰለፋሉ። ሙሮች ኢትዮጵያን ጎሜር ጀርመንና ቶጋርማ ቱርክን ይወክላሉ። ሳባ (አረቢያ) ዲዳንና ተርሴስ ተካፋይ እንደሚሆኑ (በሕዝ.38:13) ተጠቅሰዋል። ወደ እነዚህ ነገሥታት ስንመለከት በሕዝ.38 መሠረት በሰሜንና በደቡብ ማጎግ ጎግና የአረቦች መንግስታት ቅንጅትን ልንመለከት እንችላለን። በየዕለቱ የሚወጡት ጋዜጦች ለዓመታት የሆነው የዚህን ዕድገት ሪፖርት ያስተጋባሉ።

4. የማጎግ ጎግና የክርስቶስ ተቃዋሚ መንግሥት የተለያዩ ኃይላት መሆናቸውን ለማወቅ የሚያስችለው እውነት በሁለቱም ላይ የሚካሔደው የእግዚአብሔር ፍርዶች የተለያዩ መሆናቸው ነው።

*(በሕዝ.38:18-23)* እንደተጻፈው የማጎግ ጎግ ወዲያውኑ በእስራኤል ላይ ወረራ እንዳካሄደ በእግዚአብሔር ተፈርዶበት በእስራኤል ምድር ውስጥ ይደመሰሳል። በእስራኤል ጠላት በሆነው ሠራዊት ላይ ተፈጥሮአዊ የሆኑ መቅሰፍቶች ማለት የምድር፣ የባሕር፣ የአየር መናወጥ፣ የበረዶ፣ ዝናም፣ እሳትና እጥፊ የሆነ ዝናብ ይወርድበታል።





እነዚህ አስቃቂ መቅሰፍቶች በራሱ በሠራዊቱ መካከል ችግር ይፈጥራል። በድንገት በሠራዊቱ መካከል ተወዳዳሪ የሌለው መበጣበጥን ይፈጥራል። ይህም እርስ በእርሳቸው ይገዳደላሉ (*ሕዝ.38:21*)። ሠራዊቱ ከፍተኛ የደም መፋሰስን በመካከላቸው ያደርጋሉ (*ሕዝ.38:22*)። ሠራዊቶችን የሚገድልና የእጅግ ከፍተኛ ወታደሮችን ጥፋት የሚያመጣ ታስቅ መቅሰፍት በድንገት ይገለጣል። በማጎግ ጎግ ላይ የሚወርደው ፍርድ ተፈጥሮአዊ መቅሰፍቶች ብቻ እንደሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን በክርስቶስ ተቃዋሚ ላይ የሚወርደው ፍርድ «... ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው» በሚል ቃል ተገልጿል *(2ተሰ.2:8)*። ይህ ጌታ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ሲገለጥ የሚሆን የተለየ ፍርድ ነው (*ማቴ.24:30*)። ይህ የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ ከመገለጡ በፊት የማጎግ ጎግን ከሚያጠፋው የተለየ ነው።

5. ፍርድ የሚካሔድባቸው ስፍራዎች እንኳን አንዱ ከሌላው የተለየ ነው። የማጎግ ጎግ መቃብር ሐሞንጎግ ተብሎ ይጠራል (የሐሞንጎግ ሸለቆ ማለት ነው)። ይህም የሚገኘው ከሙት ባሕር በስተምስራቅ በኩል ነው (ሕዝ.39:11-16)። በሌላ በኩል ፀረ ክርስቶስ የሚደመሰሰው ከእስራኤል በስተሰሜን በኩል ከ250 ኪሎ ሜትር ርቀት በላይ በሚገኘው በአርማጌዶን ላይ ነው (*ራዕ.16:12-16፣ 19:11-21*)።

6. ከዚህ በላይ ደግሞ የማጎግ ጎግ ወደ እስራኤል የሚዘምተው ለመማረክና ለመበዝበዝ *(ሕዝ.38:12)* ሲሆን ፀረ ክርስቶስ ግን ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግና የሰው ዘር ሁሉ እንዲሰግዱለት በመመኘት ነው። (*ራዕ.13:3-8)*

7. በመጨረሻም የሚመጣው ወረራና በእርሱ ላይ የሚወርደው ፍርድ እኛ ባለንበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል እስራኤል «ያለ ቅጥርና ያለ መወርወሪያ ያለ መዝጊያ» የሆነች ሀገር ትሆናለች (ሕዝ.38:11)፣ (*ዘካ.2:8*)። ዛሬ እስራኤል በእንደዚህ ባለ ሁኔታ እንዳለች እናገኛለን። ከ1918 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አንድም የእስራኤል ከተሞች ቅጥር የላቸውም። ሕዝቡም የሚኖረው ባልተመሸጉ ከተማዎችና ሸለቆዎች ነው (ኪቡቲዝምና ምሻቪም) ።

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው በመጨረሻዎቹ ቀናት የክርስቶስ ተቃዋሚ ከመምጣቱ በፊት የማጎግ ጎግ ባጠቃላይ አመጸኛ፣ ኃይለኛና በፖለቲካም ነፃ የሆነ ኃይል ይሆናል። በእስራኤል ተራሮች ላይ በእግዚአብሔር ይፈረድበታል (*ሕዝ.39:4*:) ከዚያ በኋላ ፀረ ክርስቶስ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት እስኪፈረድበት ድረስ ከፍ ወዳለው ሕብረቱ ይደርሳል።

የሥነ መለኮት ሰው ኮንራድ ቡስሚር (1874-1944) በ1931 ዓ.ም የትንቢት ቃል ስለ ሩሲያ ምን ይላል? (what does The Prophetic word say about Russia?) የሚል መጽሐፍ ጻፈ:: በመጽሐፉ ውስጥ ሰሮሽ፣ ለምሳህና ለቶቤል ዋነኛ አለቃ የሚሆናቸው ጎግ ሌላ ሳይሆን ሩሲያ እንደሆነ ተጠቅሷል:: የሰጠውን ግምት ተቀባይነት ባላቸው ሀሳቦች በመደገፍ ጽፏል:: እነርሱንም በዚህ ፍሬ ነገር ላይ ለማከል እንፈልጋለን:: እመጻኝነት ወደ ፍርድ ይመራል በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለውን ጽፏል::

በሕዝቅኤል ራዕይ ውስጥ ሰሮሽ፣ ለሞሳህና ለቶቤል ዋና አለቃ ስለሚሆናቸው ጎግ ምን መደምደሚያን እናገኛለን? ወደሚለው ጥያቄ እንመለስ:: ይህን ጥያቄ በአእምሮአችን ይዘን የሕዝቅኤልን ትንቢት ባጠቃላይ ብንመለከት፣ ትንቢቱ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስላለው ስለ ጎግ ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን:: በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔር ተቃራኒ የሆነ ኃይለኛ መሪ ይገለጣል:: ጎግ ለእግዚአብሔር ፍርድ የተዘጋጀ (የበሰለ) ኃይል እንደሆነ የታወቀ ነው:: በሬ በእራዱ ወደ ሚታረድበት እንደሚነዳ ሁሉ እግዚአብሔርም (ይሆዋ) በጎግ አፍንጫ ውስጥ ስናግ በማስገባት(*ሕዝ.38:4*) ወደ ፍርድ ይስበዋል:: (*ሕዝ.39:2*) ነገር ግን ስለ ጎግ ቀደም ያለ ታሪክ ባናገኝም ጎግ ለምንና ስለ ምን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ ስር እንደሚመጣ ለማወቅ እንፈልጋለን ነቢዩ አልጠቀሰውም:: ሕዝብን ስድ የለቀቀ ሰው ያለ ምክንያት በአንድ ምሽት በፍርድ ስር አይሆንም:: ቀደም ሲል በእመጻኝነት የኖሩበት ረጅም ታሪካዊ ሂደት ሊኖር ይችላል:: እንደዚህ ያለ ዕድገት በሩሲያ ታሪክ ውስጥ እናገኛለን:: ስለዚህ ውጤቱ ሩሲያ የዚህን ዓይነት ታሪክ ልታሳይ ይሆን? ብለን ራሣችንንም ብንጠይቅ የኛ ሃሳብ (መልስ) አዎን ይሆናል::

ቀደም ብለን ከማንኛዎቹም ከአውሮፓ ሕዝቦች የሩሲያ ታሪክ በጥላቻና በፍርሀት የተሞላ እንደሆነ ጠቅሰናል:: ይህ ባይሆን እንኳን ሩሲያ ሁልጊዜ ክርስቲያኖችን የምታሳድድ የእግዚአብሔር ጠላት ነበረች:: ቦልሺቪኮች የአሁኑን የሩሲያን ባሕርይ ለመመስረት መጀመሪያዎቹ አይደሉም:: በቄሳሮች ዘመን የግሪክ ኦርቶዶክሶች ነበሩ:: በብሔራዊ መዝሙር ቄሳር «የኦርቶዶክስ ቄሳር» እንደሆነ ተደርጎ ተከብሯል:: ስለሆነም ክርስትና በሩሲያ በግልጽ የታወቀ ነበር:: በመላ ሩሲያ ታላላቅ ገዳማት፣ ግዙፍ የሆኑ ካቴድራሎች ከፍተኛ የአምልኮት ስርአቶችና የክርስትና በዓላት፣ ልምዶች ወጎችና የቅዱሳን ምስሎች ይገኛሉ:: ከ40 ዓመታት በፊት በቅዱስ ሲኖዶስ ላይ የበላይ ጠባቂ የሆነው ፓቢዶኖሲው ስለ ምዕራብ ሀገሮች





እመጻኝነት ተናግሯል:: ነገር ግን ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች እምነታቸውን በነፃነት ይለማመዱ ነበርን? የባብቲስት እድላቸው እንዴት ነበር? የፒተርስበርግ ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት ወደ ጌታ ኢየሱስ ሲመለሱ እድላቸው እንዴት ነበር? የኮሎኔልን ፓስቻኮውና የተከበረውን ኮርፍና የሌሎቹን ታሪክ እንረሳው ይሆን? ዳግማዊት ካቴሪን ሜኖናይቶችን ወደ ሩሲያ ተቀብላ ማስገባቷ እውነት ነው:: ነገር ግን ይህን ያደረገችው ስለ እምነት ነው ወይስ ጠንካራ ገበሬዎችን ስለ ፈለገች ነው? በዓለም ጦርነት ጊዜ የተገባላቸው ነጻነት ሜኖናይቶች ተፈቅዶላቸዋልን? ቀዳማዊ እስክንድር መጽሐፍ ቅዱስ በሩሲያ እንዲሰራጭ ፈቅዷል:: ቢሆንም በመጀመሪያ የሩሲያ ኦርቶዶክስ መፍቀድ ነበረባት:: ይህ የሚያስገርም ነገር አይደለምን? ስለ ሚስጢራዊው ቄሳር እስክንድር በመንፈሱ ባይታደስ በማዳም ዲ ክሩድነር የተሳበው የሕይወቱና የሞቱ ሚስጢር እስከ አሁን ድረስ ያልታወቀ ነው:: ለቅዱስ አልያንስ መሠረት ከሌለው ሀሳባቸውና ሕልማቸው የተሳበ ነበር:: በሩሲያ እውነተኛ ክርስትና ተቀባይነት እንዳልነበረው ሁሉ ተቀባይነት አልነበረውም:: ከእርሱ ቀጥሎ የነበሩት ወራሾቹ በመንግስቶቻቸው ዘመን ክርስቲያኖችን አሳድደዋል፣ አስረዋል ወደ ሳይቤርያም ወስደዋል:: ምንም እንኳን ዛሬ በቦልሺቪያውያን በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ቢፈጠርም አዲስ ነገር አይደለም:: አንዳንድ ሰዎች አሁን በሩሲያ ያለው እግዚአብሔርን የመጥላት ምክንያት በጀርመን የነበረው የሊበራሊዝም ውጤት ነው ብለው ጀርመንን ምክንያት ቢያደርጉም ታላቅ የድፍረት ሀሳብ ነው:: በእርግጥ ጀርመንም የክርስትና ተቃዋሚ ለመሆኗ ድርሻ ነበራት ዛሬም አለ:: ይህ በሊበራሊዝምና በሶሺያሊዝም ብቻ ሳይሆን በኦርቶዶክስና በመንግስቱም አብያተ ክርስቲያናት ያለ ነው:: በሩሲያ በክርስቲያኖች ላይ ያለው ጥላቻ በጀርመን የመነጨ አይደለም :: መሠረቱ በራሷ በሩሲያ የሆነና የተወለደ ነው:: የቄሳር ወታደሮችንና ፖሊሶችን በሚደግፉ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያናት ኃይላቸውን ይጠቀሙ (ይለማመዱ) ነበር:: ዘሬ ኃይሏ በሶቪየቶች ላይ ነው:: ከመጀመሪያው ጋር ሲመዛዘን ዛሬ የበለጠ ሰይጣናዊ ሆናለች:: የኦርቶዶክስ ካባዋን ጥላለች:: ነገር ግን የጎግ መንፈስና ባሕርይ ከጥንት ጀምሮ በሩሲያ እንደነበር ዛሬም አለ:: ዛሬ ያለ ክርስትና ማስክ ትታያለች:: *በሕዝ.38* እና *39* እንደተጻፈው ወደ መጨረሻ ጥፋቷ እየቀረበች ነው:: ይህን ብንልም እውነተኛ አምልኮና መልካም ሥራ ከሩሲያና ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ የጠፉ ነበር ብለን እንክድም:: ከሰዎቻቸው መካከል ጥቂቶቹ መልካም አምላካዊ ባሕርይ ያላቸው አሉ:: በዚህም አንድ ቀን በታላቁ በእግዚአብሔር መንጋ

ውስጥ ብዙ ሩሲያኖች ይገኛሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ነገር ግን ይህ የሩሲያን መንግስት፣ ቤተ ክርስቲያንና የማጎግን ምድር ጎግን አመጸኛ ባሕርይ አይለውጠውም። አስቀድሞ በሃይማኖት ሽፋን ስር የነበረው ባሕርዩ ዛሬ የበለጠ ግልጽ የሆነና የሚታይ ሆኗል። የማጎግ ጎግ ለምን ወደ እስራኤል ምድር ለምርኮና ለብዝበዛ እንደሚመጣ ባለው ዋና ምኞት ላይ በተመለከተ *(ሕዝ.38:12)* ቡሶሚር የሚያስደንቅ አመለካከት ስለ ሩሲያ አድርጓል። «የጎግ ዓላማዎች፣ ብዝበዛና ምርኮ» በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለውን ጽፏል። ነቢዩ ሀሳባችንን የሚስቡ ብዙ የጎግን ባህርያት ይገልጻል። ከአላማዎቹ አንዱ ሰራዊቱን ለመቆጣጠር ያለው ግፊት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ስለ ብዝበዛ ያለው ምኞትና ስግብግብነት ነው። ጎግ ሚለው ስም ትርጓሜው «ከፍ የተደረገው፣ መሪ፣ ገዢና ኃይል የተሞላ» ማለት ነው። እንዲህ ያለውን በትዕቢት የተሞላ የምናለብኝ ድንፋታን እንደ ሩሲያ ያስተጋባ በዓለም ላይ ሌላ መንግሥት አለን? ምንም እንኳን ዳንኤል ሌሎቹን መንግስታት ለአደን እንደተጠሙ አራዊቶች ቢመስላቸውም፣ ከሩሲያ በስተቀር የሕዝብን ብዛት እንደ ዳምጠ (መንገድ የሚደለድል መኪና) መጠቀሚያ ያደረገ መንግስት የለም። ሩሲያ ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች ያላት ምድር ናት። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ብዙ ሠራዊት ያሰለፈች እርሷ ነበረች። በ1914 ዓ.ም የጀርመን ጠላቶች የዚህ ሠራዊት ብዛት መላ ጀርመንን ይደመስሳል በሚል ሀሳብ ተወስደው ነበር። ዛሬም ቢሆን ሶቪየቶች በህዝብ ብዛትና በዓለም አመጽ ዓለምን ለመቆጣጠር ይመኛሉ። *በሕዝ.38* በሌላ መልኩ ይገለጽ እንጂ የጎግም መንፈስ ተመሳሳይ ነው። (*በሕዝ.38:4-6)* ያለው ክፍል በ1914 ብዛት ያለው ከፍተኛ ሠራዊት የፕሩሲያን ምስራቃዊ ድንበርን መውረሩን (መደምሰሱን) ያስታውሰናል? በማሱረን የሩሲያ ሠራዊቶች የተቀበሩባቸው መቃብሮች በሙት ባሕር በስተ ምስራቅ ያለው «የሐምንጎግን» ሸለቆ እያስታውሱንምን? *(ሕዝ.39:16)*

ሌሎች የስግብግብነትና የስስት ባሕርያት በሩሲያ የሚታዩ ናቸው። (*በሕዝ.38:12-14)* ይህ ለሀብት ያለው መሻት ጎግን የሚገፋፋው ግፊት እንደሆነ እናነባለን። ይህ የሩሲያ ደካማ ጎን መሆኑን ሁልጊዜ መጥቀስ የሚያስፈልገን አይደለም። ጎለኝነት፣ በወንጀል አታልሎ ገንዘብ መውሰድ፣ ሌብነት ለሶሺያል ክፍሎች የየለቱ ትዕዛዝ ነበር። በከፍተኛ ደረጃ የነበሩት ከድሀው ወይም ከመንግስቱ በበዘበዙት ይደለቱ ነበር። ፈረንሳይ የሶቪየትን ወዳጅነት ለማግኘት በ1893 ዓ.ም. የላከችው በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወደ መላፍንቱ ኪስ የገባ ነበር። በሩሲያ ጃፓን





ጦርነት ጊዜ የሩሲያ የጦር መኮንኖች ለራሳቸው ሠራዊት የተገባውን ብዙ ገንዘብ ለራሳቸው ዘርፈው ወስደዋል። የሩሲያ ሕዝብ በዓለም ጦርነት የተሰለፉበት ዋናው ምክንያት ሀብት ለማትረፍና ምድር ለመያዝ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ነበር። ዛሬስ በሩሲያ ከዚህ የተለየ የሚታይ ነገር አለን? እንደምንመለከተው ተቀባይነትን ለማግኘት በጣም እየጣሩ ናቸው። በነገስታት ዘመን እንደነበሩት ጨካኞችና ሌቦች ሆነው መታየትን አይፈልጉም። ነገር ግን እሁንም ቢሆን የሚያምናቸው የለም። የሩሲያ ሕዝቦች ሁሉም ነገር የተወሰደባቸውና ለራሳቸው ምንም ነገር እንዲያኖሩ ያልተፈቀደላቸው ናቸው። የሩሲያ መሪዎች የራሳቸውን ኪሶች ለመሙላት ወደ ኋላ ብለዋል ብሎ የሚያስብ ያለ ይመስላልን? እኛም አናስብምም፣ ትኩረታችንም (ጥናታችን) ይህን ያረጋግጥልናል።

ተራው ሕዝብ በሰልፍ ሲቆም (እቃ ለመግዛት) የእነርሱ ፓርቲ አባል ያልሆነ ለውድቀትና ለሞት ሲዳረግ እነርሱ ግን በምቾትና በድሎት ይኖራሉ። ኮሚዩኒዝም ሩሲያን ባለጠጋ አያደርጋትም የኮሚዩኒዝም ልምምዶቹ (የሥራ ልምምዶች) ምንም ውጤት አምጥተው አያውቁም። ጎግ ሀብትን ለመሰብሰብ ካለው ስግብግብነት የተነሳ አንድ ቀን የከንዓንን ሀብት ለመበዝበዝና ለመዝረፍ ያስብና ያለውን የጦር ኃይል ሁሉ ለጦርነት ያዝዛል። ነገር ግን ጎግ አይሳካለትም።

ስሮሽ፣ ለምላህና ለቶቤል አለቃ ስለሚሆናቸው የማጎግ ምድር ጎግ ሩሲያ ስለ መሆኑ ግምታችን ትክክል ከሆነ «ስለ ሩሲያ የትንቢት ቃል ምን ይላል?» ለሚለው ጥያቄ እንደሚከተለው መልስ መስጠት እንችላለን።

ሩሲያ የዓመጸኛ ኃይል መቀመጫ ከፍተኛ የጥፋት ታሪክ ያላት ናት። ይህ ኃይል በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔር ጠላት ይሆናል። የተመረጠውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከመንፈሳዊ ነገሯ ይልቅ ስለ ምድራዊ ሀብቷ ይወራራታል። ነገር ግን ከፍተኛ ዘመቻው ተወዳዳሪ በሌለው በእግዚአብሔር ፍርድ ወደ ፍጻሜው ይደርሳል። ጎግ (ሩሲያ) በዓለም ሕዝብ መካከል ላለው የክርስትና ተቃውሞ ሕብረትና ለአስቃቂ ጥፋታቸው ምሳሌ ነው። የዚህ ሕብረት ኃይልና ዕድገት የክርስቶስ ተቃዋሚ ከመነሳቱ በፊት ያደገ ይሆናል። ነገር ግን ከክርስቶስ ተቃዋሚ በፊት በእግዚአብሔር የፍርድ እሳት የተደመሰሰ ይሆናል። ሆኖም በኋላ የሚነሳው የክርስቶስ ተቃዋሚ በጎግ ላይ የወረደውን ማስጠንቀቂያ ምሳሌ ለሆነው ለእግዚአብሔር ፍርድ ቦታ የማይሰጥ ወይም ወደ ኋላ የማይመለስ ይሆናል ። ስለሆነም በተመሳሳይ የጥፋት መንገድ በመሄድ የባስ እድል ያገኘዋል። ምክንያቱም በመጀመሪያ ወደ እሳት ባሕር የሚጣለው እርሱ ስለሚሆን ነው። (*ራዕ. 19:20)*

በዚህ ትንቢት ብርሃን በሩሲያ ያለውን የአሁኑን እድገት ልንገመግም እንችላለን:: በታላቁ የመከራ ዘመን በምንም ነገር ይህች ሀገር የመሸሸጊያ ሀገር አትሆንም ነገር ግን ከሌሎች መንግስታት በፊት ወደ ጥፋት የምትሄድ ትሆናለች:: የጉበኛው ቃል «ወደዚያ እንሒድ» የሚል ሳይሆን «ከዚያ እንውጣ» የሚል ነው::

በመጨረሻም ቡስሚር በራዕ. 20 የተጠቀሰው «ጎግ» *በሕዝ.38 እና 39* ከተጠቀሰው «የማጎግ ምድር ጎግ» ጋር ስላለው ግንኙነት አስተያየት ሰጥቷል:: *በሕዝ.38-39* እና *በራዕይ 20* መካከል ያለው ግንኙነት በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለውን ገለጻ ይሰጣል::

*በሕዝ. 38 እና 39* የተጠቀሱት ስሞች በራዕይ ላይ ተጠቅሰው ይገኛሉ:: ከክርስቶስ 1000 ዓመታት አገዛዝ በኋላ የማጎግ ጎግ በሰይጣን መሪነት የሰውን ዘር በሙሉ በእግዚአብሔርና በቅዱሳኑ ላይ ወዳለው የመጨረሻ ከፍተኛ ተቃውሞ ያመራል:: *በሕዝ. 38 እና 39* የተጠቀሰው ሁኔታ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነውን? ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ሁለቱን ክፍሎች ቢያያይዟቸውም እኛ ግን በነገሩ አንስማማም:: *የራዕዩ 20* የማጎግ ጎግ፣ ለሮሽ፣ ለምሳህና ለቶቤል ዋና አለቃ ከሚሆናቸው የማጎግ ምድር ጎግ ጋር አንድ አይደለም:: የስማቸው ልዩነት አንዱን ከሌላው ጋር እንዳናዛምዳቸው ማስጠንቀቂያ ነው:: ከሺው አመት የክርስቶስ አገዛዝ በኋላ የመጨረሻው ፍርድና የመጨረሻው ቀን እንደሚመጣ (*በራዕይ 20*) እናነባለን:: ሰይጣን አውሬውና ሀሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት የእሳት ባሕር ይጣላል:: ዓለምም ይፈረድበታል፣ ለሰማይና ለምድርም ቦታ አይገኝላቸውም (ይጠፋሉ) :: ሙታን በሙሉ በታላቁ የነጩ ዙፋን ፊት ይቀርባሉ:: *በሕዝ.38 እና 39* የጎግ ጥፋት እንደሚከተልና *በኢዩ.2 እና 3* የሰሜን ምድር ጥፋት እንደሚከተል በተጠቀሰው መሠረት ለእስራኤል የመዳን ጊዜ ስለ መኖሩ ለመገመት አያዳግትም:: የጎግ ሙታን (ሬሳ) ለመቅበር የሰባቱ ወራት ጊዜ አይበቃም:: (መዝ. 39:12) ወይም ከሠራዊቱ በግፍ ተወስዶ የነበረውን ንብረት ለማጥፋት ያለው ሰባት ዓመት የለም:: ይህን ችግር እንዴት እንፈታዋለን? ነቢዩ ዮሐንስ ሕዝቅኤልንና ትንቢቱን የተረዳ አልነበረም በማለት አንዘጋም:: የትንቢትን ቃል በጣም ያጠናውን የምሁሩን አውበርሊንን ሀሳብ በቀላሉ እንከተላለን ጎግና ማጎግ የተባሉት ስሞች ቋሚ ስሞች መሆናቸውን ይደግፋል:: የተለየ ሕዝብን የሚገልጹ ሳይሆን ሁኔታን (ታሪክን) የሚገልጹ ናቸው (*በራዕ. 20:8*): የተገለጹት በዚህ ሁኔታ ነው ነገር ግን ይህን ሁኔታ በሌላ አቅጣጫ እንመለከተዋለን:: የጎግ ሠራዊት በእስራኤል ላይ





በሚያደርገው ዘመቻ መላ ሠራዊቱ በሙሉ ያልቃሉ:: ነገር ግን ሴቶችና ሕፃናት በጎግ ሠራዊት ውስጥ አይሠለፉም ብለን ከገመትን ሰራዊቱ ወንዶች ብቻ ናቸው ማለት ነው:: (ዛሬ የሩሱያ ሴቶች በሩሲያ ሠራዊት ውስጥ ያገለግላሉ) ስለሆነም የጎግ፣ የሮሽ፣ የምሳህ፣ የቶቤል፣ የጎሜርና የቶጋርማ ሕዝቦች (ነገዶች) ይኖራሉ ብለን እንገምታለን:: እነዚህ ሕዝቦች በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሱት ከከንዓን ሕዝቦች ጋር አወዳድሩት:: የሚጠፉ የሚደመሰሱም ነበሩ:: ነገር ግን ቢመቱም እስከ አሁን ድረስ አሉ:: በመጽሐፈ አስቴር የተጠቀሰው የእስራኤል ጠላት የሆነው ሐማ አማሌቃዊ የሆነው የአጋግ ትውልድ ዝርያ አጋጋዊ ነበር:: ይህ የአጋግ ንጉሥ ሳኦል ሕይወቱን ያተረፈው፣ ነገር ግን በሳሙኤል የተገደለው ነበር::

በቤተ ልሔም ሕፃናትን የገደለው ሄሮድስ የኤሳው ትውልድ የሆነ ኤዶማዊ ነበር:: ከዚህ በመነሳት የጎግ ሕዝቦች ወደ ፊት የሚኖሩና እንደገና ተጠናክረው የሚያድጉ እንደሆነ ለመገመት እንችላለን:: የ1000 ዓመት መንግስት ይመጣል:: የሰው ልጆች የሚበዙበትና ከዚህ በፊት ከቶ ባልሆነ ሁኔታ ምድርን የሚሞሉበትና ሊገመት የማይቻል የበረከት ጊዜ ይሆናል:: ይህ ጊዜ ከጎግ ጋር ሕብረት ላደረጉት መንግስታት ጥሩ ጊዜ ይሆንላቸዋል:: የጎግ ቤት እንኳን በራሱ ምድር ታላቅ ሕዝብ ይሆናል (*በራዕ.20:8*): «ጎግና ማጎግን እንዲያሳስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል» የሚለው ስለዚህ ነው:: ይህም ማለት ከሰሜን እስከ ደቡብ ያሉትን ሕዝቦች የሚያመለክት ነው ማለት ነው:: ይህ የምድሩን አቀማመጥ የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን የውስጣቸውንም ባሕርይ የሚያሳይ ነው:: ከጽዮን መንፈሳዊ ነገርና ከደህንነትዋ ከመለየታቸው ምክንያቱም ጽዮን *በሕዝ.38:12* እንደምናነበው የዓለም ደህንነትና ታሪክ ማዕከል ስለሆነች ነው:: የበረከት ዘመን በሆነው በክርስቶስ መንግስት ጊዜ እንኳን ጎግና ማጎግ በሞኝነት ራሱን የለየ ይሆናል:: በሐሞን ጎግ ሸለቆ ያለውን መቃብር ብዛት በሙሉ ንቃት ያስታውሱት ይሆንን? በቀል ለመውሰድ ይፈልጋሉን?

ምንም እንኳን እመጸኛው ሰይጣን በሺሁ ዓመት ጊዜ ስለታሰረ ባይኖርም በ1000 ዓመታት በፊት የጎግና የማጎግ ወላጆች በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳደረጉት ሁሉ የመጨረሻም ጊዜው በእግዚአብሔር ላይ በጥላቻ የሚነሱት መጨረሻዎቹ የሚሆኑት ከዚህ የተነሳ ነው:: ለሰይጣን አመፂ በመሆን እርዳታ የሚሰጡት ቀዳሚዎቹ እነርሱ ይሆናሉ:: ከሰይጣን ጋር በመሆን የመጨረሻውን ጦርነት ለማድረግ ይደፍራሉ:: አለቃቸው በአባቶቻቸው ዘመን ከነበረው መሪ የባሰ

ክፉ ይሆናል:: ሰይጣን ራሱ መንገዱን ይመራል:: ነገር ግን በእርሱና በእነርሱ ላይየሚወርደው ፍርድ በሌሎቹ ላይ ከወረደው የከፋ ይሆናል:: በዚህ የዓለም ታሪክ ወደ ፍጻሜው ይመጣል፣ ምክንያቱም የጎግና የማጎግ ጦርነት የሰው ዘር ድጋፍ ሲገኝ እንደማይችል ያረጋግጣል:: በ1000 የበረከት ዓመታት ጊዜ የሰው ዘር ኃጢአተኛ በመሆን ይቀጥላል (ይቆያል):: እግዚአብሔር ዓለምን በእሳት በማጥፋት አዲስ የከበረ ዓለም በመፍጠር ከሰው ጋር ያለውን የመጨረሻውን ግቦች የሚፈጽመው በዚህ መንገድ ብቻ ነው:: ይህን አዲሱን ዓለም የሚፈጥረው

«እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ!» ባለው መሰረት ነው::





የሦስቱ የዋናዎቹ መዋጀት መያያዝ የጋራ ግብ

## የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት

በመጀመሪያው ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ሶስት ሕዝቦችን ለይቶ ማሳየቱን አግኝተናል:: (*1ቆሮ.10:31-32*) እነርሱም:-

1. የዓለም ሕዝቦች (አሕዛብ)

2. የእስራኤል ሕዝብ

3. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው::

በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እነዚህ ሦስት ሕዝቦች በሦስት ወፋፍራም መስመሮች፣ እያንዳንዱ የራሱን ዓላማ በመያዝ እንደሚሄድ ተመልክተዋል:: ነገር ግን በመጨረሻ ሁሉም በዓለም ወደማይናወጠው ሁኔታና የደህንነት ታሪክ ያመራሉ:: እርሱም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው:: ይህም ሰው ቢገነዘበውም ባይገነዘበውም ይሆናል::

የሦስቱን የዋናዎቹን የመዋጀት ታሪክ መያያዝ ስናጠና ሦስት አመለካከቶች እንዳሉ ልንረዳ ያሻል:: ይኸውም:-

1. አህዛብ እንደሚዋረዱ (ዝቅ እንደሚሉ)

2. የእስራኤል ሕዝብ ክፍ እንደሚሉ

3. የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤቷ (መንግሥተ ሰማይ) እንደምትሔድ::

እነዚህ ሦስቱ ሕዝቦች ከሚመጣው ንጉስ (ከጌታ ኢየሱስ) ታሪክ ጋር የሚያያዙት እንዴት ነው? በዚህ ጥያቄ ላይ እንወያያለን:: ቅርብ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ስላለው ስለ ራሳችን አቋም እንደገና ለመመርመር እድል ይኖረናል::